ጸሎት ንስሓና ተመስጠ



የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
ፓትርያርክ ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ
የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
አባት መነኮስ ሙሴ፡
የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
ድረ ገጽ እንደጸፉት።

አያሌው ዘኢየሱስ እንደተረጎመው
ስኔሽ ፻፫ዓ.ም.
አዳስ አበባ

ጸሎት፣ ንስሓና ተመስጦ

የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ
ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ሣልሣዊ፣
የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
አባት መነኮስ ሙሴ፣
የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
ድረ ገጽ እንደጻፉት፡-

አያሌው ዘኢየሱስ እንደተረጎመው

ሰኔ 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

ምስጋና

❖ የትርጉሙን ረቂቅ ውድ ጊዜያቸውን መሥዋዕት በማድረግ አንብበው ገንቢ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ ለአባ ዘኢየሱስ፣ ለቀሲስ ጌታቸው ደጀኔ፣ ለዲያቆን ጥላሁን ደሲሳ፣ ለወንድሜ ዮሴፍ አረጋና ለወንድሜ አስክሬር ብዙአየሁ፣

❖ መጽሐፉ ተተርጉሞ እንዲወጣ በተለያየ መንገድ ለረዳችኝ እኅቴ ዕሌኒ በርሔ እና ለሌሎችም ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ በመሉ መንፈሳዊ ምስጋናዬን አቅርቤላቸዋለሁ።

የመጻሕፍቱ የእንግሊዘኛ አርዕስት፡-

- "Prayer as an Important Aspect of Our Spiritual Life."
- "If We Confess Our Sins, He is Faithful and Just to Forgive Us Our Sins and to Cleans Us from All Unrighteousness. 1 John 1:9. "
- O Lord, Do Not Rebuke Me in Your Anger (Contemplation on Psalm 6)

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን
ደንብና ሥርዓት ጠብቆ የተዘጋጀ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

አድራሻ፡- ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን
ወይም
በስልክ ቁጥሮች፡- 0911 15 75 96 0911 61 59 15

መግቢያ

(ይህ መግቢያ «ጸሎት» እና «ንስሓ» የተባሉት ሁለት አጫጭር መንፈሳዊ ጽሑፎች መግቢያ ነው።)

«ጸሎት» እና «ንስሓ» በሚል ርዕስ የተረጎምኋቸው ሁለት አጫጭር መንፈሳዊ ጽሑፎች የእንግሊዘኛ አርእስት «Prayer as an Important Aspect of Our Spiritual Life.» እና «If We Confess Our Sins, He is Faithful and Just to Forgive Us Our Sins and to Cleans Us from All Unrighteousness. 1 John 1:9.» የሚሉት ናቸው። እንደ ተመለከታችሁት ሁለቱም የእንግሊዘኛ ጽሑፎች አርእስት ረዣዥም ከመሆናቸው የተነሣ ለመጽሐፍ አርእስትነት ስለማይመቹና የሁለቱም አርእስት መሠረታዊ ጉዳዮች ስለ «ጸሎት» እና ስለ «ንስሓ» ብቻ የሚናገሩ ስለሆኑ፣ በእነዚህ ነጠላ ቃላት እንዲጠሩ ፈቅጀያለሁ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ሦስት አጫጭር ጽሑፎች («ተመስጦ» የሚለውን ጨምሮ) በመጽሐፍ ይዘት ታትመው ሲወጡ የትርጉም መጻሕፍቱን ቁጥር ወደ 26 ከፍ ስለሚያደርገው በደሉን ይቅር ብሎ ዕድሜና ጤና፣ብርታትና እውቀት በመክጠት ለዚህ መንፈሳዊ ሥራ ያበቃኝ አምላኬን ዘወትር አመሰግነዋለሁ።

ጸሎት።

«ጸሎት» የሚለውን ጽሑፍ ያዘጋጁት የግብጽ አባት መነኮስ ሙሴ ሲሆኑ በዚህ ጽሑፋቸው ውስጥ ስለ ጸሎት ጥቅም፣ ስለ ጸሎት ጠባይ፣ እንዴት መጸለይ እንዳለብን፣ የጸሎት እንቅፋቶች፣ ለጸሎታችን የሚሆን መልስ፣ መጸሎት ውስጥ ስላለ ፀፀት፣ ስለማያቋርጥ የልብ ጸሎትና በጸሎት ላይ ስል ተሰጡ አስተያየቶች አጥር ምጥን ባለና ግልጽ በሆነ መልኩ በማቅረብ ያስነብቡናል። መነኮስ ሙሴ ባቀረቡት በዚህ አጭር ጽሑፋቸው ውስጥ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች (ቅዱስ ኤፍሬም ሶሪያዊ፣ የሥነ መለኮት ሲቅ ቅዱስ ስምዖን፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ የሲናው ቅዱስ ጎርጎርዮስ፣ ግብጻዊው አባ መቃርስ፣ . . . ወዘተ) ስለ ጸሎት የተናገሯቸውን ዐበይት ቃላት በማንተራስ ነው የጻፉት። ይህ በመሆኑም በጽሑፉ ውስጥ ምንም ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የለም። ይህ ይሁን እንጂ እነዚህ ታላላቅ አባቶች የተናገሯቸው ቃላት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው። ጽሑፉን ያገኘሁት ከግብጻውያን መንፈሳዊ ድረ ገጽ ውስጥ ነው።

«ንስሓ»

«ንስሓ» የሚለውን ሌላ አጭር ጽሑፍ ያገኘሁት እንደዚሁ ከግብጻውያን መንፈሳዊ ድረ ገጽ ውስጥ ነው። ጽሑፉ በ1ኛ ዮሐ 1:9 ላይ «በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።» ተብሎ የተጠቀሰውን የእግዚአብሔር ቃል መነሻ በማድረግ ስለ ምስጢረ ንስሓ የሚያትት

ጽሑፍ ነው:: በመሆኑም ጽሑፉ ንስሓ ለመግባት ስለሚያስፈለገው ትክክለኛ ዕድሜ፣ ስለ ንስሓ አባት ኃላፊነት፣ ንስሓን ለንስሓ አባት ስለ መናገር አስፈላጊነት፣ ንስሓ በብሉይና በአዲስ ኪዳን፣ ተቀባይነት ስላለው ንስሓ አስፈላጊ ደረጃዎች፣ ለንስሓ አባት አስፈላጊ ስለሆኑ ሁኔታዎች፣ ተነሣሒው ንስሓ የሚገባው በማን ፊት ነው? እንዲሁም ስለ ምሥጢረ ንስሓ የአፈጻጸም ሥርዓቶች በዝርዝር ያስረዳል:: በእርግጥ በግብጻውያን ዘንድ ያለውና በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ የተገለጸው የምሥጢረ ንስሓ ሥርዓት አፈጻጸም በእኛ ዘንድ ካለው የምሥጢረ ንስሓ ሥርዓት አፈጻጸም ጋር እንደ ሥርዓትነቱ በመጠኑ ሊለያይ ቢችልም ዋና በሆነው የምሥጢረ ንስሓ ዓላማና ግብ ሁለቱም ፍጹም ተመሳሳይነት ነው ያላቸው:: ጽሑፉን ከግብጻውያን መንፈሳዊ ድራ ገጽ ውስጥ ላግኘው እንጂ በጽሑፉ ውስጥ የጸሐፊው ስም ስላልተጠቀሰ እኔም የጸሐፊውን ስም አልጠቀስሁም::

«ጸሎት» እና «ንስሓ»

«ጸሎት» እና «ንስሓ» የሚሉትን ሁለት መንፈሳዊና ኦርቶዶክሳዊ ጽሑፎች «ተመስጦ» ከሚለው የአቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ አነስተኛ መጽሐፍ ጋር በአንድ ላይ ያወጣሁት ጸሎት ከንስሓና ከተመስጦ ጋር ስለሚሄድ፣ንስሓም ከጸሎትና ከተመስጦ ጋር ስለሚዛመድ እንዲሁም ተመስጦ ከጸሎትና ከንስሓ ጋር ስለሚገናኝ ነው:: ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ አርእስት ያላቸው አጫጭር መንፈሳዊ መጻሕፍትን ሁለት ወይም ሦስት በአንድ አድርጌ ማውጣት የጀመርሁት ዛሬ አለመሆኑን አንባብያን ወገኖቼ ይረዱልኛል ብዬ አምናለሁ፣ጥቅሙንም እንዲሁ::

ጸሎት፣ ንስሓና ተመስጦ ለሕይወታችን እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የጽድቅና የእምነት ፍሬዎች ስለሆኑ ሁላችንም በየዕለቱ ልናከናውናቸው የሚገቡን ተግባራት ናቸው፣በተለይም ጸሎትና ንስሓ:: የማይጸልይ ሰው ንስሓ ሊገባ አይችልም፣ንስሓ ከመግባቱ በፊትም ሆነ በኋላ መጸለይ ግዴታው ነውና:: ንስሓ ለመግባት ሲያስብ ይህን ንስሓውን ለመናዘዝ የሚያስችለው የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ ይህንኑ ፈቃድ ከእርሱ በጸሎት ይጠይቃል:: በንስሓው ውስጥም የንስሓ አባቱ እግዚአብሔር በደሉን ይቅር ይለው ዘንድ አብዝቶ እንዲጸልይ መመሪያ ስለሚሰጡት ይጸልያል፣እርሳቸውም ይጸልዩለታል:: ከንስሓው በኋላም ዳግመኛ በኃጢአት እንዳይወድቅ አጥብቆ ይጸልያል:: በዚህ መሠረት ጸሎትና ንሥሓ አይነጣጠሉም:: እኛም ሳንጸልይ ለንስሓ፣ንስሓም ሳንገባ ወደ ዘላለማዊቷ የእግዚአብሔር መንግሥት ፈጽሞ ልንገባ እንደማንችል አውቀን ለዚሁ የተዘጋጀን ሰዎች እንሁን::

ይቆየን::

አያሌው ዘኢየሱስ
ኅዳር 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

ማውጫ
(ለጸሎት)

- ጸሎት፣ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚበጅ ጠቃሚ ነገር:: 7
- የጸሎት ጠባይ:: 11
- እንዴት እንጸልይ? 14
- የጸሎት እንቅፋቶች::. 17
- ለጸሎታችን የሚሆን መልስ:: 19
- በጸሎት ውስጥ ያለ ፀፀት:: 21
- የማያቋርጥ የልብ ጸሎት:: 22
- በጸሎት ላይ የተሰጡ ማጠቃለያ አስተያየቶች::. 25

ማውጫ
(ለንስሓ)

- የንስሓ ሁኔታዎች 27
- ለንስሓ የሚሆን ትክክለኛ ዕድሜ 27
- የጠባቂን ኃላፊነት መረዳት 28
- ለካህን ንስሓ የመግባት አስፈላጊነት 29
- ማስታወሻዎች 31
- ተቀባይነት ያለው ንስሓ ለመግባት የሚወሰዱ አስፈላጊ ነጥቦች 34
- ለንስሓ አባት የሚበጁ አስፈላጊ ሁኔታዎች 37
- በምስጢረ ንስሓ ውስጥ ካህኑ አባት፣ ፈራጅና መምህር ነው.....39
- ምሥጢረ ንስሓን ተግባራዊ የማድረግ ሥርዓት 41
- ማስታወሻዎች 45
- ስርየት መቀበል ይቻል ዘንድ ንስሓ በሚገባው ሰው ሊደገሙ የሚገባቸው ጸሎቶች. 46
- ከንስሓ በኋላ 50
- አንድ ካህን ለሌላ ካህን የሚገባው የንስሓ ሥርዓት 51
- ማስታወሻዎች 52
- ለከሃድያን የሚደረግ ጸሎት 52
- ለከሃድያን የሚደረግ ጸሎትና ሥርዓቱ 52
- መንፈሳዊ ልምምዶች 58
- ጥቂት የመንፈሳዊ ልምምድ ምሳሌዎች 59
- ለመንፈሳዊ ልምምዶች ስኬታማነት የሚጠቅሙ ሁኔታዎች.....64

ጸሎት

ጸሎት፣ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚበጅ ጠቃሚ ነገር::

አዘጋጅ:- የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባት መነኮስ ሙሴ::

ጸሎት፣ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚበጅ ጠቃሚ ነገር::

አሁን የምንወያይበት የጸሎት ሕይወት የአንድ በጣም ሰፊ የትምህርት ዓይነት አንዱ አነስተኛ ክፍል ነው:: መንፈሳዊ ሕይወት በአጠቃላይ በኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ሕይወት፣ መንፈሳዊ ዕድገትና ወደ ቅድስና እና እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የሚመራ መንገድ ነው:: ከሰው የግል ውሳጣዊ መንጻትና ከመደበኛ የምሥጢራት ሕይወት ጋር ተቀናጅቶ ስንመለከተው የጸሎት ሕይወት አሁን እኛ በምንኖርበት በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ውስጥ አማኙን ሰው እንደገና በብቃት እንዲያቆጠቁጥ የሚረዳ መንገድ ነው::

የዚህ ውይይት ማውጫ የደራሲው ንብረት አይደለም:: ውይይቱ በመጀመሪያ ደረጃ በውስጡ ያቀፈው ስፋት ካላቸው ምንጮች የተበደራቸውን ጽሑፎች ቅዱሳን አባቶቻችን ለእኛ በውርስ መልክ ያስረከቡን መሆኑን የሚገልጥ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ እጅግ ውድ የሆኑት ቁርስራሾች በጉጉት የተሰበሰቡት በዘመናችን ከሚገኙና በአጦስ ተራራ ላይ ከሚኖሩት አባቶች መንፈሳዊ የምግብ ብፌ ላይ ነው::

በጸሎት ለተሞላ መንፈሳዊ ዕድገት በሚደረግ ጉዞ ውስጥ ብዛት ያላቸው ጣቢያዎች ወይም ደረጃዎች አሉ:: እኛ አሁን የምንመለከተው ከእኛ ርዕስ ጋር ይበልጥ ይዛመዳሉ የምንላቸውን ጠቃሚ ነጥቦች ነው::

ከምንም በላይ ጠቃሚ ናቸው ከምንላቸው ቀዳሚ ነጥቦች መካከል አንዱና ዋነኛው ጥናት ነው:: በቅዱስ ጳጉሚስ (Pachomios) ጥብቅ ገዳማዊ መመሪያዎች ውስጥ አንዱና ማንኛውም ትጉህ መነኮስ ከእርሱ በሚበልጡ አረጋውያን መነኮሳት ማንበብና መጻፍ እንዲማር መደረጉ ነው፣ይህ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማጥናት ያግዛቸዋልና:: የቅዱስ ጳጉሚስ ረድዕ የነበረው የኖእ አሞኑ አባ ቴዎድሮስ (Theodoros) ስለ ምንኩስና ሕይወቱ የተገነዘበውን እንደሚከተለው ገልጦታል:-

> «ከእግዚአብሔር ቃል በስተቀር በልባችንም ሆነ በአንደበታችን ውስጥ ሌላ ምንም ነገር የለም:: በመሆኑም በገነት የምንደሰት እንጂ በምድር ላይ የምንኖር መሆናችን አይታወቀንም::»

ባተሌ የሆነው አእምሮ በምን እንደሚጠመድ ያውቃል:: አንድ ሰው ቀኑን ሙሉ በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ ራሱን ባተሌ አድርጎ የሚውል ከሆነ ለራሱ የሚያተርፈው ምንም ዓይነት ጥቅም አይኖረውም:: በማይለጎም የማወቅ ጉጉት እና አስልቺ ውይይት በተለይም የሌሎች ሰዎችን ኃጢአቶች በመርካትና በመደሰት እያነሣን የምናወራ ከሆነ የምናነሣሣውና የምንቀሰቅሰው የራሳችንን ኃጢአት

ነው፡፡ ሀሜተኞች፣ አሰብልተኞችና ሌሎች ሰዎችን በመወንጀል የራሳቸውን ሞራል የሚያስጠብቁ ሰዎች እጅግ በጣም ከባድ የሆኑ ችግሮች እነርሱ ራሳቸውን እንደሚያጋጥሟቸው በግልጽ የታየ ነገር ነው፡፡ ከንቱ በሆኑ ነገሮችና በተንኮል አዘል በሆኑ ውይይቶች ባተሌ መሆን መወገድ አለባቸው፤እነዚህ መጥፎ ነገሮች ሙሉ ለሙሉ የጸሎትን መንፈስ ያግዳሉና፡፡

ጥናት የእኛን የተረሱ ኃይሎች በማነሣሣት፣ በማጠናከርና በማበረታታት እንድንጸልይ ይረዳናል፡፡ በዚህ ስሜት ውስጥ መመሪያ የሚሰጠን አባ ኢሳይያስ ነው፡-

> «ጠዋት ከእንቅልፍህ ተነሥተህ ሥራህን ከመጀመርህ በፊት የእግዚአብሔርን ቃል አጥና፡፡ አንተ የእግዚአብሔርን ቃል የዘወትር ወዳጅህ አድርገህ የምትይዘው ከሆንህ በዓለማዊ ነገሮች ባተሌ አትሆንም፣ አትታወክም፣ ኃጢአትም አትሠራም፡፡»

የኒሳው ቅዱስ ጎርጎርዮስ (St. Gregory of Nyssa) ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደ ራሱ ምግብ አድርጎ የወሰደውን ሶሪያዊው ቅዱስ ኤፍሬምን ሲገልጸው እንዲህ ብሎ ነበር፡-

> «የእግዚአብሔር ቃላት የነፍስን ሙቀት ያድሳሉ፡፡ እንድታድግ ከፈለግህ የእግዚአብሔርን ቃላት እንደ ሕፃን ልጅ መጥባት አለብህ፡፡»

በጸሎት ሕይወት ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ሰው በየዕለቱ ከቅዱሳት መጻሕፍት ላይ መመገቡ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የምናጠናው እግዚአብሔር በእኛ ሕይወት መካከል መግባቱን ያፋጥነዋል፡፡ ከዚህ ሌላ እንዲህ ያለው ጥናት ጸሎትን መቀጠል በማስቻሉ መልካም ነው፡፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት በተለይም ከመዝሙራት መጽሐፍ በተጨማሪ በዕለቱ የሚታሰበው የቅዱስ ሰው ሕይወት እና ከአባቶች የሚገኝ የተመረጡ የምናኔ ጽሑፎች ለቀኑ ሽብርና ጭንቀት ሁነኛ መረጋጋትን ያድላሉ፤ እኛንም እጃችንን ለእግዚአብሔር እንድንሰጥ ያዘጋጁናል፡፡ እዚህ ላይ አስረግጠን ልንናገረው የምንፈልገው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር በቀን ውስጥ ከሚገኙት ሃያ አራት ሰዓታት ውስጥ በጥቂት ደቂቃዎች ብቻ የሚመለክ አምላክ አለመሆኑን ነው፡፡ እግዚአብሔር የሙሉው ቀን አምላክ ነው፡፡ እርሱ ለረዥም ጊዜ እኛን የሚያጅበን ከሆነ እኛ እርሱን ስንይዝ እንቅስቃሴዎቻችን በሙሉ ለተቀደሱት ሰዓታት የዝግጅት ጊዜዎች ነው የሚሆኑት፡፡ የዚህ ግልባጩም እነዚህ የተቀደሱ የጸሎት ሰዓታት ለቀጣዩ ትግል የሚያጠናክሩን መሆናቸው ነው፡፡

ማንኛውም ነገር በእርጋታ የሚፈስሰው እኛን በሚባርከንና በሚቀድሰን በእግዚአብሔር ንቁ ዐይኖች ፊት ነው፡፡ እኛ የምንተላለፍ ከሆነ እኛን ወደ ሕሊናዎቻችን ለመመለስ በመካከል ይገባል፡፡ ስለዚህም እኛ ሁላችን እርሱን ሁልጊዜ እናስታውሰው፡፡

የቅዳሴ መጻሕፍት የተዘጋጁት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኝ አትሮንስ ብቻ ሳይሆን በቤታችን ውስጥ ለሚገኝ ጸሎትም ጭምር ነው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ታላቅ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ አንድ ሰው እነዚህን መጻሕፍት ወደ መውደድ ሲደርስና ከመጻሕፍቱ ውስጥ ካሉት የሰርክ፣ የምሽትና የነግህ ጸሎቶች ዜማዎች እንዲሁም ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ከሚቀርቡት ሰላምታዎች መካከል ጥቂቶቹን የዕለት ተዕለት ወዳጆቻቸው ቢያደርጓቸው ይህ ድንቅ ነገር ይሆን ነበር፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሕይወታችን ውስጥ ጠቃሚ ሁኔታዎች ለሚፈጸሙባቸው ቀናት ማለትም ለልደት፣ ለህመም፣ ለቀለበት፣ ለጋብቻ፣ ለሞት እንዲሁም ለሌሎች ለተለያዩ አዲስ ነገሮች ማለትም አዲስ ቤት ሲሠራ፣ አዲስ ሥራ ሲጀመር፣ አዲስ ሙያዊ ሥራ ሲያዝ የምታደርሳቸውን የተለዩ ጸሎቶች አስቀድማ አዘጋጅታለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በቀን ውስጥ እንዲጸለዩ ለታዘዙት ጸሎቶችም ስም ሰጥታ አዘጋጅታቸዋለች፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ከምግብ በፊትና ከምግብ በኋላ የሚጸለዩ ጸሎቶች ለምን እንደሚጸለዩ ከሰጣቸው ምክንያታዊ አስተያየቶች መካከል ጥቂቶቹ፡- የነፍስን መመገብ እንድናስታውስ ያደርጉናል፤ከመጠን በላይ መመገብንና በመጠጥ መስከርን እንድናስወግድ ያግዙናል፤መመጠንን ለይተን እንድናዳብር ይረዱናል፤ እግዚአብሔርን ለሰጠን ስጦታዎቹ እንድናመሰግነውም ያደርጉናል . . . የሚሉት ናቸው፡፡

በታዘዙት ሰዓታት ውስጥ ሰዎች በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለጋራ ጸሎትና ለአምልኮ ይሰባሰባሉ፡፡ ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል ብዛት ያላቸው ታማኝ ጸሎተኞች ጸሎት ወዲያውኑ ተቀባይ ያገኛሉ በእግዚአብሔርም ይደመጣሉ፤እርሱ በተለየ መልኩ እንደነዚህ ያሉ ልመናዎችን ይቀበላልና፡፡ የመንፈሳዊ ስብስቦችን ሙሉ ጥቅም ለመቀበል ይረዳን ዘንድ አዲሱ የሥነ መለኮት ሲቅ ቅዱስ ስምዖን ለተናገራቸው ጥልቀት ያላቸውን ቃላት እንመልከት፡-

> «በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስትቆም ከቅዱሳን መላእክት ጋር በገነት እንዳለህ ቁጠርና ከወንድሞችህ ጋር አብረህ መጸለይህ የማይገባህ አድርገህ በማሰብ ራስህን አዋርድ፡፡ ወንድሞችህ እንዴት እንደ ቆሙ ወይም እንዴት

> እንደሚያዜሙ ለመመልከት ወደ ፊት እና ወደ ኋላ እንዳትገላመጥ በንቃት ቁም፡፡ ይልቁንም ራስህን፣ ዜማህንና ኃጢአቶችህን ብቻ ተመልከት፡፡»

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደስ ያለው ይዘምር ብሏል፡፡ መንፈሳዊ መዝሙር የሚውለው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ አይደለም፤ማናቸውም ሁኔታዎች በሚፈቅዱት ቦታ ላይ ሁሉ እንጂ፡፡ ድምፃችንን አውጥተንም ሆነ ሳናወጣ፤ለብቻችንም ሆነ በጋራ ሆነን፤ ከጸሎት በፊትም ሆነ በኋላ፤ሌላው ቢቀር በዕረፍት ጊዜ ሁሉ መዘመር እንችላለን፡፡

እንደ ፎጢኪው (Photiki) ጳጳስ እንደ ዲያዶኮስ (Diadochos) ከሆነ ከሚታወቁትና ከተለመዱት መንፈሳዊ መዝሙራት በተጨማሪ ከመጠን ባለፈ ደስታ፤ኃይል ባለው እንቅስቃሴና በጸሎት ጠባይ የሚዘመር መዝሙር አለ፡፡ ይህ መዝሙር በመንፈስ ውስጥን ሲያንቀሳቅስ በልብ ሐሴት፣ በመንፈሳዊ ዕንባና በሚያስደንቅ ደስታ ይታጀባል፡፡

ወደ ጸሎት የዝግጅት ሁኔታዎች ስንመለስ ቅዱስ አትናቴዎስ ድንግልናን አስመልክቶ በደረሰው ጽሑፉ ውስጥ የተናገራቸውን ቃላት ልብ ብለን እንመልከታቸው፡- «ለእግዚአብሔር ራሱን የሰጠ ሰው ፀሐይ ንጋት ላይ ስትወጣ በእጆቹ ላይ መጽሐፍ መገኘት አለበት፡፡» ከዚህ በተጨማሪ ለቀኑና ለሌሊቱ ሰዓታት መመሪያዎች ማውጣት አለበት፤በእግዚአብሔር ፊት ሲቆምም እንዴት ታማኝ ሆኖ መቆም እንዲገባውም ማወቅ አለበት፡፡

መጻሕፍት ጠቃሚ መሆናቸው በሚገባ ቢታወቅም ሁሉም መጻሕፍት ግን ወደ ጸሎት አይመሩም፡፡ እዚህ ላይ በሚገባ ሊታወቅ የሚገባው ነገር ቢኖር ከመጻሕፍት የሚበልጠው ታላቅ መምህር ጸሎት ራሱ መሆኑን ማወቅ ነው፡፡ እጅግ በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸው መናንያን ያለ ምንም መጻሕፍት ጸሎት መጸለይን ለራሳቸው አስተምረዋል፡፡ መጻሕፍትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረጉ ጉባኤዎች ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ሊኖሩ አይችሉም፡፡ ይሁን እንጂ በማንኛውም ጊዜ ከእኛ ጋር በሚኖረው ውሳጣዊ የጸሎት ሥራ ግን ጸሎትን መማር እንችላለን፡፡ በእውነት የሚጸልዩ ሰዎች ነፍሳት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና የመሥዋዕት ቅዱስ ስፍራ ይሆናል፡፡ ሁሉም ጸሎቶች በጥንቃቄና በአትኩሮት ከተገበሩ መልካም የሚደመጡ ጸሎቶች፣ የመጻሕፍት ጸሎቶች፣ የሕዝብ ጸሎቶችና ድምፅ አልባ የልብ ጸሎቶች መሆን ይችላሉ፡፡

ሥር ሳይኖረው መልካም ተክል ሊኖር እንደማይችል ሁሉ ያለ ምሥጢራት ሊኖር የሚችልም ጸሎት የለም፤በተለይም ያለ ቅዱስ ቁርባን፡፡ አባ አጵሎስ በአንድ ወቅት እንዲህ በማለት ተናግሯል፡-

> «መነኮሳት በበአቶቻቸው ውስጥ የጀመሯቸውን ጸሎቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲሰባሰቡ ማጠናቀቃቸው የተለመደ ነገር ነው፡፡ የጋራ (የማሕበር) የሆኑትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተጀመሩት ጸሎቶችም በበአት ውስጥ መጠናቀቃቸውም እንዲሁ፡፡ በቅዳሴ ላይ ተገኝተው የሚቀበሉት የቅዱስ ቁርባን ምሥጢር ግን ያለ ማቋረጥ በልባቸው ጽላት ላይ መቅረቡን ይቀጥላል፡፡»

የጸሎት ጠባይ፡፡

ከምንም ነገር በላይ የጸሎት ጠባይ ማለት ምንድር ነው? ለጸሎት ድካም፣ ትኩረትና ጥረት ማውጣት ተገቢ ነገር ነው? ለማገናዘቢያ ይረዳን ዘንድ እስቲ የቅዱሳን አባቶችን ቃላት (ብሒል) እንመርምር፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ ብሏል፡-

> «ጸሎት በሕይወት ማዕበል ውስጥ መጠጊያ ወደብ፤ ማዕበል ለሚያንገላታቸው መልሕቅ፣ የድህው ሀብት፣ የባለጸጋው ደኅንነት፣ የታማሚው መዳኛ ወይም ጤና ማግኛ ነው፡፡ ጸሎት መጥፎ ነገሮችን ያስወግዳል፤ መልካሙን ግን ይጠብቃል፡፡»

ይኸው እግዚአብሔርን የያዘ መንፈሳዊ አባት በዚያው አስከትሎ ሲናገርም እንዲህ ብሏል፡-

> «ጸሎት የነፍስን ተራ ስሜቶች ፀጥ ያደርጋል፤ የቁጣን ዓመጽ ያበርዳል፤ቅናትን ያጠፋል፤ክፉ ፍላጎቶችን ይበትናል፤የዓለማዊ ነገሮችን ፍቅር ያመነምናል፤ለነፍስም ታላቅ ሰላምና እርጋታን ያመጣል፡፡»

የጸሎት ጠባይ ከሚሰጠው ነገር ግልጽ እየሆነ ይመጣል፡፡ ባለ መሰላሉ ቅዱስ ዮሐንስ (St. John of the Ladder) ጸሎት ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ መንገድ ነው ብሏል፡፡ ለእያንዳንዱ ሰው የጸሎትን ጥቅም ለማስተማር ሲል ዓለሙን አቋርጦ ለመሄድ ይፈልግ የነበረውና በጥብቅ የምናኔ ሕይወቱ የሚታወቀው የሲናው ቅዱስ ጎርጎርዮስም (St. Gregory of Sinai) እንዲህ በማለት ተናግሮ ነበር፡-

«ጸሎት ለጀማሪ ሰዎች መልካም እሳት ሲሆን ቀድመው ለጀመሩት ደግሞ በተቀጣጠሰ ጊዜ መልካም መዓዛ የሚያወጣ እሳት ነው። ጸሎት ሰልብ እንዲህ አያሰ ይነግረዋል፦ ጸሎት የድኅነት ተስፋ፣የመንጻት ምልክት፣ የቅድስና ምሳሌ፣የእግዚአብሔር እውቀት፣የመንፈስ ቅዱስ አንድነት፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ደስታ፣የነፍስ ተድላ፣የእግዚአብሔር ምሕረት፣የእርቅ ምልክት፣ የክርስቶስ ማኅተም፣ጎልቶ የሚታይ የፀሐይ ጨረር፣ የክርስትና እምነት ማረጋገጫና የመላእክት ሕይወት መስረጃ ነው።»

ለጸሎት ጥብቅ እንቅፋቶች እጅግ የበዛ እንቅልፍ፣ እጅግ የበዛ ምግብ፣ እጅግ የበዛ ወሬ እና እጅግ የበዛ ምኞት ናቸው። እነዚህ እንቅፋቶች እግዚአብሔርን ለማስረሳትና ለውነትን ልፍስፍስ ለማድረግ የበኩሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፤ነፍስ ንቁ በመሆን መንፈሳዊ ሐሴት እንዳያደርግም ነገሮችን አስቸጋሪ ያደርጋሉ። ራስን ለማጥራት አይረዱም፤በጸሎት ጊዜ የተፈጋጉ፣ ሰላማዊና ፀጥ ማለት የሚገባቸው ሕሊናን፣ ልብንና ፍተሕን ግራ ያጋባሉ።

መጸለይ የሚገባኝ እንዴት ነው? መጸለይ የሚገባኝ መቼ ነው? ጸሎቴ እስከ ምን ድረስ ነው መሰፋትና መርዘም ያለበት? እንደነዚህ ያሉ ጥያቄዎች የሚገልጡት የጋሰና የማያቋርጥ ጸሎት አሰመኖሩን ነው። በጋለ ስሜት መጸለይን ለሚወድ ሰው ምንም ዓይነት ገደብ አይኖረውም። አርሱ በማንኛውም አጋጣሚ መጸለይ ይችላል። የዛሬ ጸሎቱ የትናንት ተተጽኖ ነው። የዛሬ ጸሎቱም ነገ ይቀጥላል። እንዲህ ተብሎ ተነግሯል፦ ቅዱስ ሰው (እንደ ቅዱሳን አባቶቻችን) ፈጽሞ ጸሎቱን አያቋርጥም፤የእርሱ የጸሎት ሕይወት ማብቂያ የለውም።

ጸሎትን የዕለት ተዕለት ልምዳችን ለማድረግ ያስቸገረን በመንፈሳዊ ሕይወታችን ውስጥ ያለው ጥብቅ የድካም (የስንፍና) መታወቂያችን ነው። ይህን ድካም በማወቃችንና በመረዳታችን ግን ተስፋ መቁረጥ የለብንም። ይልቁንም ይህን ጉዳይ ጥረቶቻችንን ለማበርታትና ይበልጥ ቀጣይ ለማድረግ የሚያነሣሣ እንዲሆን መሥራት አለብን። በማንኛውም ቦታ ላይ ስንሆንና ባሰብነው ጊዜ ሁሉ መጸለይ እንደምንችል መማር እንችላለን። ይሁን እንጂ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች በተጨማሪ ከግል ጸሎቶቻችን ጋር የምንገናኝባቸው ልዩ ጊዜዎች ሊኖሩን ይገባናል። አባ ይስሐቅ እያንዳንዱ መነኩሴ በዘኩቱ ውስጥ እንዲጸልይ እንደ መከረ እኛም ጸሎቶቻችንን ለማድረስ የሚመች እጅግ ፀጥ ያለ ስፍራ ያስፈልገናል።

በአንድ ወቅት ግብጻዊው አባ መቃርስን እንዴት ነው መጸለይ የምንችለው ብለው በጠየቁት ጊዜ እንዲህ የሚል መልስ ሰጥቶአቸው ነበር፦

«እጅግ ለረዥም ጊዜ ባላዋቂነት ማጉረምረም ጠቃሚ ነገር አይደለም። አጀቻችሁን ወደ ሰማይ ዘርግታችሁ 'ጌታዬ ሆይ፦ ለእኔ የሚሻለውንና የሚበልጠውን አንተ ታውቃለህና እኔን ይቅር በለኝ።' በሉት። ይህን በምትሰብት ጊዜ ውጊያ የሚከፈትባችሁ ከሆንም 'ጌታ ሆይ፦ እርዳኝ!' በሉት፤እርሱ ለእኛ ይበልጥ የሚበጀውን ነገር ያውቃል፤ምሕረቱንም ያደርግልናል።»

በቃላት የምናደርሳቸው ጸሎቶች አሉ። መሳ ሕይወታችንን ጸሎት ማድረግ የምንችልበትና ይህንንም ለእግዚአብሔር የተቀደሰ መሥዋዕት አድርገን ማቅረብ የምንችልበት ጸሎት አለ። ከሁሉም ብርቱውና ቃላቱ ጸሎት ደግሞ ያለ ቃላት የሚደርስ ጸሎት ነው። አስቲ በትዕግሥትና ያለ ድካም እግዚአብሔር ሲናገር የምናዳምጥ ቋሚ ደቀ መዛሙርት ሆነን እንተመጥ። የማናውቅ፣ የዋሃን፣ ትሑታን፣ ድሆችና የማንናገር ሆነን ሁሉንም መሐሪ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት አንወደቅና ምሕረቱን፣ ድኅነቱንና ጠቃሚ አርዳታውን መግሰጫ ቃል በሴለው ማቃለት እንሰምነው። እኛ፣ ፀጥ ያለ የትሕትና ጸሎት በመጸለይ እግዚአብሔር አምላክ በሕይወታችን ውስጥ እንዲናገር እንፍቀድ። አርሱ ከእኛ ጋር ለመሥራት የሚፈልጋቸውን ነገሮች እንዲሠራ የምንፈቅድለት ከሆነ እስከ ዘለዓለም ድረስ ለእርሱ ታዛዥና ልጆች የሆኑትን ቅዱሳን እንመስላቸዋለን፤በዚህ ጊዜ ወደ ነበረን ወደ መጀመሪያው ወብታችን ሰለምንመለስም የእርሱን ሕይወት በእውነት የራሳችን ሕይወት እናደርገዋለን።

አባ ይስሐቅ እንዲህ ብሏል፦

«ጸሎት ለማድረግ ወደ እግዚአብሔር ስትቀርቡ ራሳችሁን እንደ እንድ አነስተኛ ጉንዳን፣ እንደ እንድ በምድር ላይ እንደሚሳብ እነስተኛ ፍጥረት፣ እንደ እንድ ደቃቃ አልቅትና እንደ እንድ ተብታባ ሕፃን ቁጠሩ።»

አባ ሰራጲዮን ለጸሎት የሚቆሙ ሰዎች አቋቋም ልክ ለድንገተኛ አደጋና በድፍረት ለተሞላ ዝግጁነት እንደሚቆሙ ወታደሮች ያለ ማቋረጥና በትጋት መሆን አለበት ብሏል።

ታላቁ የጸሎት መምህርና መላ ሕይወቱ በጸሎት የተሞላው ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ በማለት ተናግሯል፦

«ዘወትር ንቁ በሆነ ትኩረት መጸለይ አለብን። ይህ ሊሆን የሚችለው ከማን ጋር እየተነጋገርን እንደ ሆነ በሚገባ ስናውቅና በዚህ ጊዜ ውስጥ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የምናቀርብ ባሪያዎቹ መሆናችንን ስንጠነቅት ነው። ስንጸልይም በፀፀት፣ በዕንባ፣ በክብር፣ በመንፈስ እርጋታና በታላቅ እርምም መጸለይ አለብን። ኃጢአቶቻችን እኛን ከጸሎት ሲገድቡን አይገባቸውም። ስለ ኃጢአቶቻችን ማፈር አለብን እንጂ ኃጢአቶቻችን እኛን ከጸሎት መገደብ የለባቸውም። አንተ ኃጢአተኛ ሰው ብትሆንም ከእርሱ ጋር መታረቅ እንድትችል እግዚአብሔርን በጸሎት ቅረበው፤እርሱ ኃጢአትህን ይቅር እንዲልህም ዕድሱን ስጠው። በዚህ ጊዜ እርሱ ይህን ያደርገዋል፤ ለለው ልጆች ያለውን ፍቅር የሚገልጠው በዚህ ነውና።»

ይኸው ቅዱስ አባት በዚያው ቀጥሎ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦

«ኃጢአቶችህን ምክንያት በማድረግ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የምትፈራ ከሆነ ለእርሱ አንቅፋት ስለምትሆንበት ቢያንስ-ቢያንስ የተወሰነ ያህል የእርሱን ቸርነትና አባታዊ ፈቃድ ከመግለጽ በመቆጠብ በራስህ ማስተዋል ጀምረሃል ማለት ነው። ስለሆነም በኃጢአት ምክንያት ይቀራል ስለምትለው ጸሎት ያለህን ማንኛ ውንም ዓይነት ጥርጥርና ማመንታት ከእንተ ዘንድ አርቅ።»

እንዴት እንጸልይ?

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ስለ ጸሎት በሰበካቸው ድንቅና ሰፊ ስብከቶቹ መካከል ለሚጸልየው ሰው ይረዱት ዘንድ ከዚህ የሚከተሉትን እንኳር ነጥቦች እናቀርብለታለን። ጸሎት በሕይወታችን ውስጥ ደንብና መደበኛ ልምድ መሆን አለበት፤ይህም በጽድቅና በእከብሮታዊ አቋቋም እንዲሁም ፍጹም በሆነ ትኩረት ሊከናወን ያስፈልጋል። በጸሎት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ስንነጋገር ለእርሱ የሚገባውን ተገቢ ክብር መስጠት አለብን፤የጸሎትን ታሳቅ ጥቅም ማወቅ አለብን፤በግላችንም የተለዩ ምላሾች መኖራቸውን መገንዘብም አለብን። ጸሎቱ ከእግዚአብሔር ጋር በእውነት የመነጋገር ያህል የሆነለት ሰው ምድራዊ መልአክ ሆኖ ተለውጧል ማለት ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ከእርሱ ጋር ስንነጋገር የተዋበ ቃላትን እንድንጠቀም አይጠይቀንም። ይሁን እንጂ የምንናገራቸው ቃላት ከተዋበች ነፍሳችን ተፈጋጥተው መውጣት አለባቸው። ጸሎት በተመደበለት ሰዓት ሲቀርብ ሽምጋዮችን፣ ሥርዓቶችን ወይም ቀጠሮዎችን አይሻም። የእግዚአብሔር ደጆች ዘወትር ክፍት ስለሆኑ እርሱ እኛን ይጠብቀናል። ራሳችንን ከእግዚአብሔር የምናርቅ ወይም የምናገል ከሆንን መሐ ለመሐ በራሳችን አባብ መደገፍ ጀምረናል ማለት ነው። እርሱ ዘወትር ቅርብ ነው። በተለየ ሁኔታ አንደበተ ርቱዕ መሆን አያስፈልገንም። እኛ የተፈለገውን ያህል ድምፆቻችንን ዝግ አድርገን ብንናገር እንኳ እርሱ ይሰማናል። እኛ ጥቂት ብንናገር እንኳ እርሱ መሐ ለመሐ ይረዳናል። ማናቸውም ሰዓታትና ማናቸውም ቦታዎች መልካም ናቸው። በጸሎት ጥብብ ውስጥ የተራዘመ መመሪያዎችን ማስቀመጥ አስፈላጊ አይደለም። ለመጸለይ መፈለጋችን በራሱ በቂ ነው፤ከዚህ በኋላ መማር ፈጣንና ጥረት የማይጠይ ይሆናል።

በቂው ነገር የጸሎት ዘዴ ነው። እኛ መጸለይ ያለብን ከልባችን ሆነን፣ መንፈሳዊ ዕድገት በሚሻ ፀፀት ውስጥ ሆነን፣ ሌሎች ሰዎችን ይቅር በማለትና የእነርሱን ይቅርታ በመጠየቅ እንዲሁም በእውነት ትሑታን ሰዎች በመሆን ነው። እግዚአብሔር እንደሚፈልገን ሆንን የምንጸልይ ከሆነ፣ ጸሎቶቻችንን ባለ መታከት የምናቀርብ ከሆነ፣ በጸሎቶቻችን ውስጥ ለእኛም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ነፍሳት ጥቅምን የምንሻ ከሆነ፣ መነሣሣታችን ንጹሕ ከሆነና ሙሉ ለሙሉ በምድራዊ ጉዳዮች ላይ የማናተኩር ከሆንን ጸሎቶቻችን አድማጭም ሆነ ተቀባይ ያገኛሉ። ነቢዩ መሴና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ካቀረቧቸው ጸሎቶች መካከል በእግዚአብሔር ያልተደመጡ ጸሎቶች ነበሩ፤ሁሉም የእነርሱ ጸሎቶች ምቹ አልነበሩምና።

በምንጸልይበት ጊዜ ጸሎታችን መጋነን የለበትም፤ ጥረቶቻችንም ሙሉ ለሙሉ በመቀበል አባብ ላይ ብቻ ማተኮር የለባቸውም። ዋናው ዓላማችንና አስፈላጊው ነገር ነፍሳችንን የተሻለች ማድረግ ነው፤ይህም ሊሆን የሚችለው በጸሎት አማካይነት ነው። ይህን ጉዳይ ዓላማው አድርጎ የሚጸልይ ሰው ከዓለማዊ ነገሮች ኃይል ይበልጥ ብርቱ ይሆናል፤ከእነርሱ ሁሉ በላይም ከፍ ብሎ ሊከንፍ ይችላል።

አስቀድመን ለጸሎት እንቅፋት የሆኑት ነገሮች አብዝቶ መተኛት፣ አብዝቶ መብላት፣ አብዝቶ መጠጣት፣ አብዝቶ ማውራትና አብዝቶ መደሳደል መሆናቸውን ተነጋግረናል። እነዚህ ነገሮች ውጤታማ ለሆነ ጸሎት እንቅፋቶች ከሆኑ ጉቃት፣ ጾም፣ አርምሞ፣ ፀጥታና ምናኔ ጸሎቶቻችን ከፍ ብለው እንዲከንፉ የሚያደርጉ አክናፋት መሆናቸው እርግጥ ነው።

ንቃት ከጸሎት ሕይወት ጋር ሊነጣጠል አይችልም:: ክንፍ የሌላት ወፍ እንደሌለች ሁሉ ያለ ንቃት የሚሆን የጸሎት ሕይወትም ሊኖር አይችልም:: እግዚአብሔር የማይታሰብበት ምሽት አበቦች እንደሌሉት መናፈሻ፣ ፍሬ እንደሌለው ዛፍ እና ጣራ እንደሌለው ቤት ነው:: በእግዚአብሔር ዘንድ ይበልጥ የሚወደዱት ጸሎቶች በሌሊት የሚጸለዩት ጸሎቶች ሲሆኑ አነርሱም ከመተኛታችን በፊት፣ ጥቂት ከተኛን በኋላ፣ ሌሊት የምንነሣበትና ከንጋት በፊት (ሊነጋጋ ሲል) የምንጸልያቸው ጸሎቶች ናቸው:: በዚህ ዓይነት መንገድ ምሽቱን የምናውሰው ለሥጋችን ዕረፍት ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ለነፍሳችን ደኅና መሆን ጭምር እንጂ:: ከእንቅልፋችን ጥቂቱን መሥዋዕት ስናደርግ የእኛ የሆነውን አንድ ነገር ለእኛ ኃጢአቶች መሥዋዕት ለሆነው ለእግዚአብሔር ልጅ እንሰጣለን ማለት ነው:: የምሽት ጸሎቶች እንቅልፋችንን ጣፋጭ ያደርጉታል፤ምክንያቱም የጸሎታችን ቃላት ሳይጠፉ በዚያው ስለሚቀጥሉ ድንቅ ሕልሞችን እንድናይ ያነሣሱልናልና:: ታላቁ ቅዱስ አርሳኔዎስ ዘወትር ቅዳሜ ምሽት ጸሎቱን የሚጀምረው ጀንበር በስተ ምዕራብ ስታዘቀዝቅ ሲሆን ጸሎቱን የሚያበቃውም ጀምበሯ እሑድ ጠዋት በፊቱ ላይ ስታንጸባርቅ ነበር:: እርሱ የጸሎቱን ጊዜ የሚለካው በዚህ ዓይነት መንገድ ነበር!

ቀላልና የተመጠነ የጾም ምግብ ለሕሊና ግልጽነትን ሲያድል ለነፍስ ደግሞ ንቃትን ያድላል:: እጅግ የጠገበ ሰው ሲጸልይ እንደማይችል ሁሉ እጅግ የተራበ ሰውም ሊጸልይ አይችልም:: ሰው መብላት ያለበት እንዳይራብ ያህል ወይም ከዚያ በታች መሆን አለበት::

አርምሞ ቃላቶቻቸውን የሚለኩና አንደበቶቻቸውን እንደ ገዳይ መሣሪያ የማይጠቀሙበት የእግዚአብሔር ልጆች ማጌጫ ነው:: ቃላትን እንዲሁ እንደ ዋዛ የሚጠቀምባቸው ሰው ውጤታማ ጸሎት ለመጸለይ ይቸገራል:: ልፍለፋ ግራ ያጋባል፣ ያደክማል፣ ለመረዳትም ያስቸግራል:: አርምሞ ሕሊናን እንዲያተኩር ያደርገዋል፣ ለመንፈስ እረፍት ይሰጣል፣ ያለ ማቋረጥ ዝግጁ ሆኖ እንዲቀጥልም ያደርገዋል:: መነኮሳት በአቶቻቸውን የሚቀልሱት እጅግ በጣም ፀጥ ያለውን ጥግ ሥፍራ ፈልገው ካገኙ በኋላ ነው:: የዚህ ዓላማም ውጪያዊው ፀጥታ ወደ ነፍስ ዘልቆ ስለሚገባ ነው:: ያለ ውስጣዊ ፀጥታና ሰላም ደግሞ ውጪያዊ ፀጥታ ምንም ዋጋ አይኖረውም:: የነፍስ እርጋታ እግዚአብሔርን በማመስገን የሚታጀብ ከሆነ ታላላቅ ውጤቶች ሊገኙ ይችላሉ::

እንደ ግብጻዊው ቅዱስ መቃርስ ከሆነ አሳቦቻችንን መጠበቅና በበዛ ፀጥታና ሰላም መጸለይ ለጸሎት መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው:: እንደ ሶሪያዊው ቅዱስ ኤፍሬም ከሆነ ደግሞ ንጹሕ ሆኖ የሚጸልይ ሰው ርኩሳን መናፍስትን ያጠፋቸዋል፤በግድ የለሽነት የሚጸልየው ሰው ግን የርኩሳን መናፍስት መሳለቂያ ሸቀጥ ነው የሚሆነው::

የጸሎት እንቅፋቶች::

አንድ የአጦስ ተራራ አረጋዊ መነኩሴ በሥሩ ላሉት ወጣት መነኮሳት አዘውትሮ እንዲህ ይላቸው ነበር:- «ከግዛ ራሳችሁ አሳቦችና በምናቦቻችሁ ከሚታዩአችሁ ነገሮች ጋር አትነጋገሩ::» ሌላው አረጋዊ መነኩሴ ደግሞ እንዲህ ብሏል:- «ከበአቱ በላይ ወፎች ይበርራሉ:: ይህን በማድረጋቸው ልከለክላቸው አልችልም:: እኔ እንዳያደርጉ የምከለክላቸው ጎጆዎቻቸውን በበአቱ ክዳን ላይ እንዳይቀልሱ ነው::» ባለ መሰላሉ ቅዱስ ዮሐንስ (St. John of the Ladder) እንዲህ በማለት ተናግሯል:- «በምትጸልዩበት ጊዜ አሳባችሁ በተደጋጋሚ የሚሰረቅባችሁ ቢሆንም እንኳ ይህንኑ ጸሎታችሁን በድጋሚ መልሳችሁ ለማምጣት ታገሉ:: በጸሎት ጊዜ ትኩረታችን ቢሰረቅብን ቅጣት አንቀበልም፤ ጸሎታችንን በድጋሚ መልሰን ማምጣት ካልቻልን ግን ቅጣታችን አይቀርልንም::»

በመጀመሪያው አረጋዊ መነኩሴ የተነገረላቸው «አሳቦችና የምናብ አይታዎች» ብዙዎቻችንን እጅግ የሚያስቸግሩን ታላላቅ ችግሮቻችንና በጸሎቶቻችን ላይ አደገኛ እንቅፋት የሚደነቅሩ ጉዳዮቻችን ናቸው:: እነዚህን ነገሮች ቆርጦ ለመጣል ረዥምና አስቸጋሪ ትግል ከእኛ ይጠበቃል:: ከብዙ ጉዳዮች አንጻር ስንመለከተው እነዚህ አሳቦቻችንና የምናብ አይታዎቻችን ለእኛ እውነተኛ ተፈጥሮ ባዕዳን ይሁኑ እንጂ በእኛ ዘንድ የተለመዱ ሁኔታዎች ሆነዋል:: እነርሱን ቆርጦ ለመጣል አስቸጋሪ የሚሆነውም ለዚህ ነው:: እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች (አሳቦቻችንና የምናብ አይታዎችን) በእኛ ውስጥ ዋሻዎቻቸውን መሥርተዋል:: ተለማምደናቸዋል፤ከጊዜ ርዝመት የተነሣም ፍጹም ተፈጥሮዎቻችን አድርገን እየቆጠርናቸው ነው:: ጸሎቶቻችንን ማወክ ሲጀምሩ ትኩረቶቻችን ፈጥነው ይጠፉብናል:: እነዚህ አሳቦቻችን በተለይም ከእኛ ቁጥጥር ውጪ ከሆኑት ፍላጎቶቻችን ጋር የሚጣጣሙና በፈቃዳችን ውስጥ ያለ ድካማችን ገላጭ ከሆኑ ከእኛ ዘንድ እንዲሄዱልን ብንፈልጋቸውም እንኳ አይለቁንም:: አስቀድመን እንደ ተናገርን ትግሉ ረዥምና አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል:: እስቲ ታማኞች፣ ለመሸሸግ የማንፈልግና ለድካማችን ምክንያቶች የምናቀርብ አንሁን::

ለጸሎት እንቅፋት የሚሆኑ ሌሎች ብዙና የተለያዩ ነገሮች አሉ:: በእኛ ዘንድ ሳይኖሩ ከእኛ ጋር የተዛመዱ እንደ ጥርጥር ወይም ጭንቀት ወይም ሕመም ያሉ ችግሮች አሉ:: ሌሎች ጤናማ ያልሆኑ ጠባያት፣ ረሃብ፣ ጥማት፣ እንቅልፋምነት፣ ትዕግሥት ማጣት፣ ትዝታዎችና መሰላቸቶችም አሉ:: ያሰብናቸውና ረስተናቸዋል ያልናቸውን (የስልክ ቁጥሮች፣ የታላላቆቻችን ብሒሎች፣ ባለፉት ጊዜያት የገጠሙን ንዴቶችና ቁጣዎች) ከነዝርዝሮቻቸው ይታወሱናል:: እነዚህ ሁሉ ለጀማሪዎች ችግሮች ሊሆኑ ይችላሉ:: ይሁን እንጂ እነዚህ

ሁሉ ተስፋ ሊያስቆርጡን አይገባቸውም:: ከእነዚህ ችግሮች በተጨማሪ ምትሐቶችና የርኩስ መንፈስ ማስፈራራቶች በጸሎቶቻቸው በመጠቁት ቅዱሳን ላይ በስፋት የሚቃጡ ችግሮች ሲሆኑ በጀማሪዎች ላይ የሚቃጡት ግን በመጠኑ ነው::

ይበልጥ መሠረታዊ የሆነው ችግር ግን ዲያብሎስ የእኛን ንዝህላልነትና ትኩረት አለመስጠት ተጠቅሞ ልባችን በጸሎት ሕይወት እንዳይነሣሣ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ከንቱ አሳቦችንና የምናብ አይታዎችን በማከታተል ከጸሎት ፍሬ ነገር እንድንርቅ የማድረጉ ጉዳይ ነው:: ይሁን እንጂ በጸሎተ ቅዳሴ ላይ «የጥበብ ደጆች ይጠበቁልን ዘንድ በእነርሱ ላይ እናተኩር::» ተብለው የሚነገሩትን ቃላት በሕሊናችን ውስጥ መጠበቅ አለብን:: የክፉ ነገሮች ሁሉ መገኛ የሆነው ዲያብሎስ እንዳይቆጣጠራቸውና እንደ ልቡ እንዳይገባባቸው የሕሊና እና የልብ ደጆች በሚገባ መጠበቅ አለባቸው::

አሳቦቻችንን መጠበቅና ከመጥፎ ንድፈ አሳብ፣ ከዲያብሎስ ማታለሎችና የተሳሳቱ ራእዮች መከላከልና መጠበቅ እጅግ አስቸጋሪ ነገር ነው:: እዚህ ላይ እጅግ ጥብቅ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው:: የጸሎት ዓላማ እግዚአብሔርን በራእይ መመልከት አይደለም፤ የሚፈስሰውን የእርሱን ምሕረት መመልከት እንጂ:: እግዚአብሔርን የመመልከት ከፍተኛ ፍላጎት የስሕተት መጀመሪያ ሲሆን ይችላል:: እስቲ እኛ የማይገባንና አቅሙ የሌለን (በእርግጥም ነን) ሰዎች ሆነን እንኑር:: እግዚአብሔር ለእኛ መገለጡ ግድ ቢሆን ግን ሁሉም ነገር ደኅና እና መልካም ይሆንልናል:: ይሁን እንጂ እኛ የምንፍጨረጨርበት ዋና ዓላማችን ይህ መሆን የለበትም::

በአንድ ወቅት በምድረ በዳ ውስጥ እየጸለየ ወደሚኖር ወደ አንድ መናኝ አንድ ፈተና ይረብሸው ዘንድ መጣበት:: መናኙ እንደ ተለመደው ራሱን በትሕትና ዝቅ ቢያደርግም ፈተናው የመጣበት በፊቱ በሚያበራ የሐሰት ብርሃን ነበር:: ይህን መለኮታዊ ብርሃን ቀና ብዬ መመልከት አይገባኝም በማለት ራሱን ስላሳመነ ፊቱን በአሸዋ ውስጥ ቀበረው:: ፈተናው ወዲያውኑ ስለ ጠፋለት ሊገለጽ የማይችል ሰላም የመናኙን ልብ ሞላው:: ይህ ታሪክ የሚገልጽልን ምን ያህል ንቁ እና የተረጋጋን መሆን እንዳለብን ነው::

ስለሆነም ማሰናከያ እንዳይጥለን እንጠባበቅ:: በመጸለይ ላይ ሳለ በእባብ ተነድፎ የነበረው መናኙ ቅዱስ ኔሎስ (St. Neilos the Ascetic) በድፍረት እንደ ቆመ እኛም እንደ እርሱ በድፍረት መቆም አለብን:: እርሱ የጀመረውን ጸሎት እስከሚያጠናቅቅ ድረስ ንቅንቅ አላለም ነበር:: ከራሱ ይበልጥ እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ምንም ዓይነት ጉዳት አይደርስበትም::

ፓላዲዮስ ስለ አንድ መነኩሴ የተናገረው ታሪክ ቀደም ሲል ከተመለከትነው ቅዱስ ሰው ጋር ተመሳሳይነት አለው:: ይኼኛው መነኩሴም በጸሎት ላይ ሳለ በጌንጥ ቢነደፍም ከጸሎት ቦታው ላይ ንቅንቅ አላለም ነበር::

በአንድ ነገር በቀላሉ የሚሸነፈው ዘመናዊው ሰው ግን ብርቱ የጥድፊያ ስሜትና ታላቅ ትዕግሥት ማጣት ይታይበታል:: እርሱ ብዙ ነገሮችን በፍጥነት ያለ ጥረት ማግኘትን ነው የሚጠብቀው:: በእርሱ ዘንድ ያለው ትዕግሥት ማጣት ጸሎቱን በፍጥነት እንዲፈጽም ያደርገዋል፤እዚህና አሁን ፈጣን ምላሽ እንዲጠብቅም ያደርገዋል:: እርሱ ምርቱን መሰብሰብ የሚሻው ገና ዘሩን ሳይዘራ ነው:: ያለ እንዲት የላብ ጠብታ ተአምራት፣ መገለጦችንና ራዕዮችን ማየት ይጠብቃል:: ይህ የዘመኑ ሰው ንጹሕና ገራገር ፍላጎቱ በየዋህነቱ እግዚአብሔርን ያለ ማቋረጥ ለመመልከት የሚያስችለው አድርጎ ስለሚያስመኘው በሚያስፈራና በአደገኛ ሁኔታ ብዛት ባላቸውና የበግ ለምድ ለብሰው በሚመጡ ተኩላዎች ይነጠቃሉ፤እነርሱ ስርገው የሚገቡት የክርስቶስን መንፈሳዊ ገጽታ በማስመሰል ነውና::

ለጸሎታችን የሚሆን መልስ::

በጸሎት የጠየቅናቸው ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት መዘግየታቸውን መመልከታችን (ጥያቄዎቻችን መመለሳቸውን ማረጋገጣችን) የጸሎት ሕይወታችን የሚፈተሽበት ሌላው ነጥብ ነው:: የጥያቄዎቻችን አለመመለስ ምክንያት እግዚአብሔር ጸሎቶቻችንን አለመስማቱ ወይም ለሚደርስብን መከራ ግድ ስለማይሰጠው አይደለም:: እግዚአብሔር አምላክ እኛ አንድንታወክ ወይም አንድንጨነቅ አይፈልግም፤በጋሉ ጸሎቶቻችን ከእርሱ ጋር ያለ ማቋረጥ አንድንገናኝ ወይም ጥያቄዎቻችን በፍጥነት ካልተመለሱ ጸሎቶቻችንን ይበልጥ እንድንጨምር እንጂ:: እግዚአብሔር አምላክ የጠየቅነውን ቢሰጠንም ሆነ ባይሰጠን ልናመሰግነው ይገባናል፤መስጠቱንም ሆነ አለመስጠቱን ለእኛ ሲል ለበጎ ስለሚያደርገው ነው:: በጸሎታችን ለጠየቅነው ጥያቄ መልስ ካገኘን ተስፋ መቁረጥ ወይም ግራ መጋባት የለብንም፤ምናልባት እግዚአብሔር ጽናታችንን እየፈተነ ሊሆን ይችላልና:: ስለዚህ በቀላሉ የምንደክም ሰዎች አንሁን::

የምንሻውን ነገር ካልተቀበልን ልክ ጥያቄዎቻችን መልስ እንዳገኙ አድርገን እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን፤በአሁኑ ስዓት ስላሉ እውነተኛ ፍላጎቶቻችን እኛ ከምናውቀው የበለጠ እርሱ ያውቃልና:: በዚህ ስዓት እኛ የምንሻው ነገር የሚያስፈልግ ካልሆነ ተስፋ ያደረግነው ነገር ተግባራዊ አይሆንም፤ለእኛ አስፈላጊ መስሎ ቢታየንም እንኳ:: የጠየቅነው ነገር በእውነት አስፈላጊያችን ከሆነ እግዚአብሔር ወዲያውኑ ነው የሚሰጠን:: ስለሆነም ጉዳያችን ግልጽ

ተቀባይነት ባያገኝም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳረጋገጠልን በዚህ ጉዳይ ላይ ስኬታማዎች ሆነናል ማለት ነው። በእርግጥም ሰሕይወታችን ጥቅም የሚሰጥ ውድቀት ስኬት እንጂ ውድቀት አይደለም።

ምናልባት እናንተ «አባቴ ሆይ፡- የምጠይቀው ለእኔ መልካም የሆኑትን ነገሮች ስለሆነ የማልቀበላቸው ለምንድር ነው?» በማለት ልትጠይቁ ትችሉ ይሆናል። መልሱ ምናልባት እናንተ ስእነዚህ ነገሮች ያላችሁ ቅንዓት በቂ ላይሆን ስለሚችል ይሆናል። ምናልባትም ጥያቄዎቻችሁ በእውነት ከእናንተ ልብ የመነጨ ሳይሆኑ ማለትም የምንጫቸው ወይም የእነሣሻችው አስገኚ ከሌላ ሊሆን ስለሚችል ነው። ወይም ደግሞ እናንተ የጠየቃችኋቸውን ጥያቄዎች ስመቀበል አይገባችሁ ይሆናል። እግዚአብሔር ስለማይ ወፎች፣ ስምድር እንስሳትና ተክሎች ያለው ጥበቃ ሰሰው ልጆች ያለው ርኅራኄ ከማንኛ ውም የወላጅና የዘመድ ጥብቅ ትስስር እጅግ ስለሚልቅ እኛን ያስ ምንም ምክንያት እንዲሁ አይተወንም።

የሚጫጫን ማፋሸክ ሲይዘን፣እያንዳንዱ ነገር እኛን ግራ የሚያጋባን ሆኖ ገና በመጀመሪያው ተስፋ መቁረጥ እንድንሸሽ ሊያደርገን፣ቸልተኝነታችን በጥርጥርና በግድ የለሽነት የሚታጀብ ከሆነ የመጨረሻ ድምዳሜያችን በግልጽ የሚጠቁመን የምንሻውንና የምንፈልገውን ነገር በተከክል ለይተን አለማወቃችንን ነው። ትናንትና የጠየቅነውን ጥያቄ ዛሬ የማንጠይቀው ከሆነ በእርግጥ የምንጸልይለትን ነገር በትክክል አለማወቃችን ግልጽ የሚሆንልን ከጊዜ በኋላ ይሆናል። በፍላጎቶቻችን ላይ በየጊዜው የምናመጣው የሚያቋርጥ ለውጥ በሽታ የእኛን የጸሎት ሕይወት ማቃወስና ችግር ውስጥ መከተቱ እንዲሁ በሥነ ልቦናችን የሚታወቅ ነገር ነው። እኛ የምንጸልየው የጸሎት አካሄድ ጠቃሚ ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው በረቀቀ መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር ከሚደረግ የግንኙነት ልምድ፣ ከመሰከያዊው አስትንፋስ፣ መንፈስ ቅዱስ በተሕትና ከሚያቀርበው ድንቅ ሽክሽክታ እንዲሁም ስላማዊ ከሆኑና መሪዳት ከሚችሉ ልቦናዎች ነው። ልባችን ሊሸሻል (ለውጥ ሊያመጣ) ለጸሎት ያለን አመለካከትም ለውጥ ያመጣል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ድንቅ የሆኑ ጥያቄዎችን ከጠየቀ በኋላ ጥያቄዎቹን በሚገባ ሊያጠቃልሰ የሚችሉ መልሶችን ይሰጣል፤እንዲህ በማለት፡-

> «በእርምሞና በመንፈስ እርጋታ ውስጥ ናችሁን? ከሆናችሁ እግዚአብሔር ይህን ቋሚ ደስታ በልባችሁ ውስጥ ይበልጥ ቋሚ ያደርግላችሁ ዘንድ ለምኑት። በመከራዎችና በችግሮች ከፍተኛ ጥቃት ትታወክላችሁ? እግዚአብሔር በሕይወታችሁ ውስጥ ያለውን ማዕበል

ፀጥ እንዲያደርግላችሁ ለምንት። ጸሎታችሁ ተሰምቶልን? እግዚአብሔርን አመሰግኑ። አልተደመጣችሁም? አስከምትደመጡ ድረስ በጸሎታችሁ በጽናት ቆዩ።»

በእኛ መንገድ ውስጥ ለሚመጡ አስደሳች ነገሮች በመሰሉ እግዚአብሔርን ማመስገን የተሰመደ ነገር ቢሆንም በሕይወታችን ውስጥ ሰሚገጥሙን አስደሳች ስላልሆኑ ነገሮች እግዚአብሔርን ማመስገን መቻል ግን አስደናቂ ነገር ነው። ይህ ነገር በእርግጥ በንጥመን ጊዜ እግዚአብሔርን አናስደስታለን ዲያብሎስን ግን እናሳፍረዋለን። ዝዘን ወደ መንፈሳዊ ደስታ ይቀየራል ማለት ነው። በመከራው ጊዜ እግዚአብሔርን ማመስገን ከሚችል ሰው የሚበልጥ ቅዱስ ሰው የለም።

ባለ መሰላሉ ቅዱስ ዮሐንስ (St. John of the Ladder) ሲናገር ውጤታማ ጸሎት በሁለት ዋና ዋና ነጥቦች ተለይቶ ይታወቃል፡- በጥብቅ ምስጋና እና በፀፀት በተሞላ ንስሓ። ይህ ቅዱስ ሰው በትክክል የሚነግረን አንዳንድ ጊዜ በጸሎት ውስጥ ያሉ ጥያቄዎቻችን ሲሟሉ የማይችሉት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ እንደ ሆነ ነው። ተገቢ ባልሆነው ሰዓት ስለማንጠይቅ ወይም የምንጠይቀው ጥያቄ ለእኛ የሚገባን ስላልሆነ ወይም የምንጠይቀው ስለ ከንቱ ውዳሴ ስንል ስለሆነ ነው። ሌላው ሊሆን የሚችለው ምክንያት እኛ ልናገኘው የምንጸልይበትን ነገር ከተቀበልን በኩራት ኃጢአት የምንወድቅ ከሆነ አይሰጠንም። ከዚህ በተጨማሪ የጠየቅነውን ነገር ከተቀበልን በኋላ በችልተኝነት ኃጢአት የምንወድቅ ከሆነም አይሰጠንም።

በጸሎት ውስጥ ያለ ፀፀት።

«መሰላሉ/The Ladder» የሚሰውን ታላቅ መንፈሳዊ መጽሐፍ የደረሰው ባለ መሰላሉ ቅዱስ ዮሐንስ (St. John of the Ladder) አውነተኛ ጸሎት የዕንባ እናትና ልጅ ነው በማለት ተናግሯል። ፀፀት የዕንባ ጥብቅ ወዳጅ ነው። በፀፀት የተሞላ ጸሎት የሚመሠረተው በሕይወታችን ውስጥ ዘወትር በሚገኘው በእግዚአብሔር መኖር፣ በልባችን ንጽሕና፣ በመንፈሳችን አውነተኛ ትሕትና እንዲሁም ዘወትር ልናስታውሰውና ልንመሰጥበት በሚገባን በሞት ሥጦቢራዊነት ሳይ ነው። እሳትና ውኃን በአንድነት ማስቀመጥ እንደማይቻል ሁሉ ፀፀትን ከቅንጦት ሕይወት ጋር መቀላቀልም እንዲሁ የማይቻል ነገር ነው። እኛ ንቃቶቻችንን ብዛት ወዳላቸው ወደ እግዚአብሔር ጠቃሚ ጣልቃ ገቢነት መምራት የምንችል ከሆነ ዓይኖቻችን ስለ እርሱ በረከት በደስታ ዕንባዎቻችን ይሞላሉ። ኦርቶዶክሳዊ ዝማሬዎች የሚዘጋጁት በእነዚህ ጣፋጭ የምስጋና እና በፀፀት በተሞሉ ዕንባዎች ነው። እንዲህ ያለው

ዕንባ በመናንያኑ ዘንድ የሚታወቀው «በደስታ የተሞላ ዝዘን» ተብሎ ነው።

ጸሎቶቻችን በእነዚህ ዕንባዎች መደገፍ የሚገባቸው ከሆነ ይህን በረከት በኩራታችን እንዳናጣው ጥንቃቄ እናድርግ። መናኙ ማርቆስ ያሳሰበን ክርስቶስ በእነዚህ ዕንባዎች እኛን መትብኘቱና ዐይኖቻችንን መክፈቱን ነው። ቅዱስ ባርሶናፍዮስ (St. Barsanophious) ፀፀት ወደ እኛ ሲመጣ የሚችለው እኛ ኢ-መንፈሳዊ የሆኑ መብቶቻችንን ማክዘንና ስንችል፣ ፈቃዳችንን ስንገራውና ለዓለማዊ ዝና ያለንን ፍቅር ስናጠፋው ነው። አውነተኛውን ፀፀት ከሞራዝ ነጠቁ! ከከንቱውና ከስሜታዊው ዕንባ መለየት መቻላችን ለእኛ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። ፀፀት ግድ የሰሽ ከሆነ እንደበት ተጠርጎ እንዳይወሰድ ጠንቃቆች መሆን አለብን። አፈጋዊው ኤልያስ «ፀፀት የሌለበት ጸሎት ጣዕም እንደሌለው ምግብ ነው።» በማለት ነግሮናል። ቅዱስ ቴዎግኖስጦስ (Theognostos) «ፀፀት በጸሎት ውስጥ ሊገኝ የሚችለው መጠንን በማወቅ፣ ነቅቶ በመጠባበቅና በትሕትና ነው።» በማለት ነግሮናል። ኒቅጣስ ቴጣጦስ (Niketas Stethatos) ደግሞ «ፀፀት ትሕትናን፣ትሕትናም ፀፀትን ያስከትላል።» በማለት ተናግሯል።

የማያቋርጥ የልብ ጸሎት።

ይህን ጽሑፍ ያዘጋጀው ሰው ስለማያቋርጠው የልብ መንፈሳዊ ጸሎት ስለሆነው ርዕሰ ጉዳይ ላይ በቂ ውይይት ማድረግ አይችልም፣እርሱ ራሱ ምንም ሳይወሳውል ወይም ሳያመነታ አቡነ ዘበሰማያትን (የጌታን ጸሎት) መጸለይ አይችልም፡፡ ስለ አትኩሮትና ዘበሰማያትን የጌታን ጸሎት) መጸለይ አይችልም፡፡ ስለ አትኩሮትና ስለ መንፈሳዊ ተመስጦና ስለ ድርጊቱ ስለ ንቃት እንዲሁም ስለ መንፈሳዊ ተመስጦና ስለ ድርጊቱ የሚናገረው ይህ ርዕሰ ጉዳይ (የጸሎት ዓይነት) በጣም የመጠቀና እጅግ አስቸጋሪ ነው። ስለሆነም እኔ አትሜን እዚህ ላይ እነድብና ከማያልቀው ከቅዱሳን አባቶች ሀብት ውስጥ ከሚገኙትና ተግባራዊ ሊሆኑ ከሚችሉት አሰቦች መካከል ጥቂቱን አካፍላችኋለሁ።

ባለ መሰላሉ ቅዱስ ዮሐንስ (St. John of the Ladder) መመሪያውን እንዲህ በማለት አስቀምጦልናል፡-

> «ልብ ከእንደበት ጋር አንድ ሆና ይህን ጸሎት ተግባራዊ ማድረግ የሚያቅተው ከሆነ ጸሎት ጸሎቱ በእንደበት ሊጸለይ ልብ የጸሎቱን ቃላት ለመያዝና ለመከታተል ይጣር። በልብ ጸሎት ውስጥ ያለ ምንም አንቅፋቶችና አሳብ ከሚሰርቁ አሳቦች ርቀን መጸለይ ስንችል እግዚአብሔር ለምላክ ውሱ አድሮ ይባርከናል።»

የዋሀና ትሑት ለሆንችው ነፍስ ሁሉም ዓይነት ግርማ እንደሚሰጣት ሁሉ ይኼኛውም ሞገስ ይሰጣታል፤ይህ የሚሆነውም መደላደል በሌለበትና ጥብቅ በሆነው መንፈሳዊ ሥርዓት ውስጥ ነው። በሁሉም ነገሮች ውስጥ የለከነ፣ የዋህና ትሑት ለሆነው ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ይህንን የልብ ጸሎት ያድሰዋል።

«አቡነ ዘበሰማያት» የተባለው የኢየሱስ ክርስቶስ ጸሎት «ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፡- እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ!. . .» ከሚለው ጸሎት ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ጥቂት የቃላት አጠቃቀም ልዩነት ቢኖረውም እንኳ። የዚህ ጸሎት ኃይል ወሰን የለውም። ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው የጌታ ስም ገና ሲጠራ ርኩሳን መናፍስት እንደ ጉም በነው እንደሚጠፉ ታላቁ አባ አባ አንጦንስ ነግሮናል። ይህ ጸሎትና የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብዙት ባላቸው ቅዱሳን ዘንድ ተደጋግሞ ይነሣል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ደግሞ እንዲህ ብሎናል፡-

> «የልብ ጸሎትን በአንድ ወይም በሁለት ቀናት ውስጥ ንዝዘብ ማድረግ አይቻልም፤ጠላት ተወግዶ ኢየሱስ ክርስቶስ በልባችን ውስጥ እስከሚያድር ድረስ ያለውን ረዥም ጊዜና ጥረት ይጠይቃልና።»

መናኙ ቅዱስ ኔሎስ (St. Neilos the Ascetic) እንዲህ በማለት ተናግሯል፡-

> «ጠላቶቻችንን የምንከላከልበት ዋነኛው መከላከያችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው።»

ጠላቶቻችን እነማን ናቸው? የሚቃጠሉ ፍላጎቶቻችን፣ የኃጢአት ደስታዎቻችን፣ የዲያብሎስ ዕቅዶችና እነዚህን የመሰሉት በመሉ ናቸው። «አቡነ ዘበሰማያት» የሚለውን ጸሎት እንዴት እንደሚገባን አድርገን መጸለይ እንዳለብን መመሪያ የሚሰጠን «Philokalia» የተባለ መጽሐፍ ሰለና ተመልከቱት።

የማያቋርጥ የልብ ጸሎት የሚመጣው ከታላቅ ፍቅር ነው። አንድ ሰው የማይከታተል፣ ሥራ ፈት እና ነቃፊ ከሆነ ይህን ጸሎት ንዝዘቡ ማድረግ እንደማይችል እርግጥ ነው። ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር የምንሠራው ሥራ ሊያገደው አይችልም። የእግዚአብሔር የሆነ ሰው (እርሱም ሆነ እርሷ) ምንም ያድርጉ ምን እግዚአብሔርን ያለ ማቋረጥ ያስታውሱታል፤የማያቋርጥ መዝሙር በእነርሱ ዘንድ አለ፤ የማያቋርጥ የምስጋና ጸሎትም እንዲሁ። እግዚአብሔር እምላክ ሁላችንንም ቢወደንም የሚወዱትን ደግሞ የበለጠ ይወዳቸዋል። ጸሎቶቻችን እኛ ለእርሱ ያለንን ፍቅር የምንለክቸው መሣሪያዎቻችን ናቸው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው የማይለካ ፍቅር ጸሎትን

ለግሶናል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው በሚያሻው ጊዜና በሕይወቱ ውስጥ በሚገኙት በሁሉም ቀናት ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ይችላል፡፡ ቅዱሳን ሰዎች በሙሉ የጸሎት ሕይወታቸውን የማያቋርጥ አድርገውታል፡፡

ታላቅ መንፈሳዊ ብቃት ያለው አባ ጴሜን (Abba Poimen) እንዲህ ብሏል፡-

> «እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎች አሉ፣ እነርሱም ፈሪሃ እግዚአብሔር፣ የማያቋርጥ ጸሎትና ባልንጀሮቻችንን መውደድ፡፡»

አባ ዶላስ (Abba Doulas) የተባለው የአባ ቤሳሬዎን (Abba Bessarion) ረድእ መምህሩ አባ ቤሳሬዎን በበእቱ ውስጥ እጆቹን ያለ ማቋረጥ ለ14 ቀናት ያህል ለጸሎት ዘርግቶ መቆሙን ተመልክቷል፡፡ ረድእ መምህሩን ያናገረው እጆቹን ካወረዳቸው በኋላ ነበር፡፡

ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስ ይህን ተናግሯል፡-

> «የማያቋርጥ ጸሎት ማለት ሁለንተናችሁን ለእርሱ በመስጠት ራሳችሁን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ማድረግ ማለት ነው፤በዚህ ጊዜ ሕይወታችሁ ሁሉ የማያቋርጥ ጸሎት ይሆናል፡፡»

አባ ይስሐቅ ደግሞ እንዲህ ብሏል፡-

> «መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ ካላደረ በዚህ ጸሎት ውስጥ ያለውን የፍጹምነት ደረጃ ልናገኝ አንችልም፡፡ መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ ካደረ ግን ጸሎታችን ሊቋረጥ አይችልም፤እንቅልፍ ቢወስደንም እንኳ፡፡»

ኒቅጣስ ቴጣጦስ (Niketas Stethatos) ደግሞ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡-

> «የማያቋርጥ ጸሎት እግዚአብሔርን በጽኑ ፀፀት ውስጥ ሆነን የምናስታውስበት መንፈሳዊ ነጸብራቅ ነው፡፡»

በአጦስ ተራራ ላይ ከሚኖሩት አባቶች መካከል አንዱ ከአንዲት ታናሽ ሴት የደረሰውን አንድ ደብዳቤ ከእኛ ሕይወት ጋር ማነጻጸሪያ ይሆን ዘንድ አቅርበነዋል፡፡ ሴቲቱ በደብዳቤዋ ውስጥ ከጻፈቻቸው ከሌሎች ቁም ነገሮች በተጨማሪ እንዲህ ብላ ጽፋለች፡-

> «አባቴ ሆይ፡- ሁለት ልጆቼን ለማሳደግ የምሠራ አንዲት መበለት ነኝ፤ጊዜ የሌለኝ ሰው ስለ ሆንሁ በቀን (በ24 ሰዓታት) ውስጥ የምጸልየው ለ8 ሰዓታት ብቻ ስለሆነ እባክዎ በጸሎትዎ ያስቡኝ፡፡»

አዎን፤ያነበባችሁት ለ8 ሰዓታት ነው የሚለው፤ እርሷ ግን ይህን ሰዓት በቂ እንዳልሆነ አድርጋ ነው የቆጠረችው፡፡ እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው አይለካም፣ አያሰላም፣ ለመቀበል ሲልም አይሰጥም፡፡ እርሱ ወይም እርሷ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ ስለ ሰጡ እግዚአብሔርም እርሱነቱን ለእነርሱ ሰጥቶአቸዋል፡፡

በጸሎት ላይ የተሰጡ ማጠቃለያ አስተያየቶች፡፡

ውድ ባልንጀሮቻችን፡- ጸሎታችን መደበኛ ይሁን እንጂ በልማድ የሚከናወን አይሁን፤በመርሐ ግብር ይከወን እንጂ ስለ መርሐ ግብር ሲባል አይከወን፡፡ ይህን የምናደርግ ከሆነ ጸሎታችን ጣፋጭ ግለት፣ የሚያነሣሣ ልዩነትና ጸጋ ይኖረዋል፡፡ ረቂቅ ነገር ግን እርግጠኛ በሆነ ከእግዚአብሔር ጋር በሚደረግ ግንኙነት ውስጥ አምላካችን ጸሎታችን እውነተኛና እርሱን ደስ በማሰኘት ልባችንን በሰላምና በደስታ የሚሞላ መሆኑን ለእኛ ይገልጥልናል፡፡ ብዛት ያላቸው ፈተናዎች፣ አስቸጋሪ ነገሮች፣ መከራዎች፣ አደጋዎች፣ ሞቶች ወደ ጸሎት የሚመሩ ማነሣሻ ጥበባት ናቸው፡፡ እነዚህ አስቸጋሪ ነገሮች ሰዎችን አስቀድመው በብርቱ ጽናት ወዳላገኟቸው ወደጋሉና ወደ በረቱ ጸሎቶች እንዲመሩ ይረዷቸዋል፤እነዚህ የቀደሙት ጸሎቶች በሙሉ ልብ አልተጸለዩም፤ እውነትም ይጎድላቸው ነበርና፡፡

እውነተኛውን የጸሎት ጥበብ ሰው እንዲማረው የሚደረገው እግዚአብሔር ራሱ እንዲጸልይ ባደረገው በዚያ ሰው ነው፡፡ በልማድ የሚደረግ ጸሎት ግን ያለ ፀፀት መንፈስ ስለሚቀርብ እግዚአብሔርን ደስ አያሰኘውም፡፡ እግዚአብሔርን የምትወድ ነፍስ ያለ ጸሎት ልትኖር አትችልም፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ነፍስን ወደ እርሱ የሚያቀርባት ለእርሱ በምታቀርበው ጸሎት አማካይነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ፍጹም የሆነውን የጸሎት ጥፍጥና የሚሰጠው ትሑት ለሆነው ሰው ብቻ ነው፡፡ ንጹሕ ሊሆን የሚችለው የትሑት ሰው ጸሎት ብቻ ነው፡፡

በማጠቃለያው ትንታኔ፡- ብርቱና ደካማ፣ የጋላችሁና የቀዘቀዛችሁ፣ ወጣቶችና አረጋውያን፣ የተማራችሁና መሃይማን፣ ባለጸጎችና ድሆች፣ ካህናትና ምዕመናን የሆናችሁ ውድ ወንድሞቼና እኅቶቼ በሙሉ፤የጸሎታችን አንዲት ቃል ከንቱ አንደማትጠፋ ላሳስባችሁ እወዳለሁ፡፡ የጸሎታችን ቃላት በሙሉ ይደመጣሉ፡፡ ይህ በመሆኑም በእነዚያ የተቀደሱ ሰዓታቶቻችሁ ውስጥ ዋጋ የለሽ ሰው የሆንሁ የእኔን ስም ለማሰብ አትርሱ፤እግዚአብሔር አምላክ ለሌሎች በተለይም እጅግ ለሚያስፈልጓቸው ሰዎች የሚደረጉ ጸሎቶችን ይወዳልና፡፡

በጎውን ሁሉ ለእኛ ያደረገና የሚያደርግ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን፡፡

ንስሓ

«በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡» 1ኛ ዮሐ 1:9፡፡

አዘጋጅ፡- ከግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ድረ ገጽ የተገኘ፡፡

«በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡» 1ኛ ዮሐ 1:9፡፡

ምሥጢረ ንስሓ ማለት ኃጢአተኛው ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ኃጢአቱን በካህኑ ፊት በመናዘዝ ለእርሱ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ሥልጣን አማካይነት የሚያስተሠርይበት ቅዱስ ምሥጢር ነው፡፡ በዚህ ማስተሥረይ ውስጥ ንስሓ የሚገባው ሰው ንስሓ የገባባቸው ኃጢአቶቹ በሙሉ ይቅርታ ያገኛሉ፡፡

ንስሓ ማለት አንድን ጉዳይ ማመንና መግለጥ ማለት ነው፡፡ ምሥጢረ ንስሓ ማለትም ሰውየው በእርሱ ለተፈጸሙት ኃጢአቶችና ስሕተቶች በካህኑ ፊት ስርየቱንና ይቅርታውን ለማግኘት ሲል በቃላት ኑዛዜ በትሕትና የሚገልጽበት ማለት ነው፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለንጹሐን ሐዋርያቱ «እውነት እላችኋለሁ፡- በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል፡፡» (ማቴ 18:18) በማለት በተናገረ ጊዜ ምሥጢረ ንስሓን መሥርቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከትንሣኤው በኋላ ጌታ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- «ኢየሱስም ዳግመኛ፡- ሰላም ለእናንተ ይሁን፤አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው፡፡ ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፡- መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡፡ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል. . .» ዮሐ 20:21-23፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን በማድረግም ኃጢአትን ይቅር የማለትና የመያዝ ሥልጣንን ንስሓ እንደሚገባው ሰው ፀፀት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ሰጥቶአቸዋል፡

የንስሓ ሁኔታዎች

እውነተኛ ንስሓ አራት ሁኔታዎች አሉት፡-

- ለቀደሙ ኃጢአቶች የሚሆን ያዘነና የተፀፀተ ልብ፡፡
- ሊሻሻል የሚችል ጽኑ አሳብ፡፡
- በክርስቶስ የሆነ ብርቱ እምነትና ይቅር በሚል በእርሱ ፍቅር ላይ የተመሠረተ ተስፋ፡፡
- ስለ ኃጢአቶች የሚደረግ የንግግር ንስሓ፡፡

ለንስሓ የሚሆን ትክክለኛ ዕድሜ

ወላጆች ለልጆቻቸው ስለ ምስጢረ ንስሓ ገና ከልጅነታቸው ዘመን አንሥቶ ማለትም ከአሥራ ሁለት ዓመታቸው ጀምሮ ሊያስተምሯቸው ይገባቸዋል:: ይህን በማድረጋቸውም ገና ልጆች ሳሉ ከዚህ ምሥጢር ጋር ይተዋወቃሉ ማለት ነው፤ምሳሌው:- «ልጆችን በልጅነት ሳሉ ማስተማር በድንጋይ ላይ እንደ መቅረጽ ነው::» እንዲል::

በጆን ቢን ኤልሳባ በተዘጋጀውና «ውዱ አልማዝ/The precious Diamond» በሚለው የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ውስጥ ከዚህ በታች የተጠቀሰው ጽሑፍ ተጽፎአል:: በዚህ ጊዜ የማይተውና እጅግ ጠቃሚ የሆኑትን ነጥቦች እንዳስሳለን:-

የጠባቂን ኃላፊነት መረዳት

አንድ ልጅ በክርስቲያናዊ የቅድስና ሥራዎች መካከል ሲያድግ ጠባቂው (የክርስትና አባቱ) ወይም ቤተ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር ቤት ይወስዱታል:: በዚያም ፈጣሪው እግዚአብሔር በጥምቀት ከካህኑ እጅ ካህኑ ባለበት ይቀበለዋል::

«ወንድ/ሴት ልጄ:- ለሰይጣን ልጅና ባሪያ በነበርህ ጊዜ ወላጆችህ አንተን በቅዱስ ጥምቀት ነጻ ሲያወጡህ ወደዱ:: በመሆኑም በዚህ በእግዚአብሔር ካህን ፊት እንዳሳድግህ የእኔን ድካም ጠይቀዋል:: እኔ አንተን ከእርሱ ተቀብዬ በአንተ ስም ሰይጣንንና ሥራዎቹን ክጀልሃለሁ፤ስለ አንተም ለጌታዬ ለኢየሱስ ክርስቶስ ንስሓ ገብቼልሃለሁ፤የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንድትሆንም የጌታዬን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ደም እንድትቀበል አድርጌሃለሁ::

አሁን አንተን በተቀበልሁበት በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ፊት ቆመሃልና ሰይጣንን ክዶ በእግዚአብሔር ያመነ ሰው የሰይጣን ሥራዎች የሆኑትን ትዕቢትን፣ ጥላቻን፣ ቁጣን፣ ግድያን፣ ዝሙትን፣ ውሸትን፣ መሐላን፣ ቤተ ክርስቲያን መሄድንና የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ሰነፍ መሆንን ማስወገድ አለብህ:: በኢየሱስ ክርስቶስ ስታምን የፍቅርን፣ የትሕትናንና የቅድስናን ሥራዎች ገንዘብህ ለማድረግ ትፈልጋለህ፤ያለ እነርሱ ማንም እግዚአብሔርን ሊያይ አይችልምና:: አንተን ከተቀበልሁበት ከዚህ ስፍራ አንተን ለራስና ለእግዚአብሔር አስረክባለሁ:: ከአሁን በኋላ ከእኔ ምንም ዓይነት ነገር አትጠይቅ፤ከአሁን በኋላ መልካምና መጥፎ የሆነውን ለመለየት አዋቂና በሳል ነህና::»

የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ከአንተ ጋር ይሁን፤ ልብህንም እስከ መጨረሻው ድረስ በኦርቶዶክስ የእምነት ጥላ ሥር አስጠልል፤አሜን::»

ከዚህ ሰዓት በኋላ ካህኑ ሕፃኑን ይቀበላል፤ስለ ንስሓም ያስተምራቸዋል:: በመሆኑም ካህኑ የንስሓ ምሥጢርን ተግባራዊ ማድረግ ለጀመረው ልጅ በቀጥታ አባትና መንፈሳዊ መሪ በመሆን ይመራዋል::

ለካህን ንስሓ የመግባት አስፈላጊነት

ለካህን በንግግር መናዘዝ ለኃጢአቶች ይቅርታ ለማግኘት አስፈላጊ ነገር ነው፤መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለንጹሐን ሐዋርያቱ «ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል. . .» (ዮሐ 20:23) ብሏቸዋልና::

እንዲያው ለነገሩ ካህናት አባቶች ኃጢአቶችን ሳያውቋቸው እንዴት ነው የሚፈቱትና የሚይዙት? አንድ ዳኛ ስለ ጉዳዩ በዝርዝር ሳይገነዘብ የሚፈርደውስ እንዴት ነው? ይህ ሲሆን ስለማይችል ነው ሐዋርያት አባቶቻችንና በእነርሱ እግር ለሚተኩት ሁሉ ኃጢአትን የማሰርና የመፍታት ሥልጣን የተሰጣቸው:: በመሆኑም በጉባኤ ላይ የሚቀመጡት ሰዎች ኃጢአትን በማሰርና በመፍታት ስርየት ለማስጠት ሥልጣኑ ባላቸው ሰዎች ፊት ኃጢአታቸውን ይናዘዙ ነበር::

በካህን ፊት ንስሓ መግባት ለኃጢአቶች ይቅርታ ለማግኘት አስፈላጊ ነገር ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች ጥቅሞች አሉት:- ከሰዎች አመለካከት አንጻር. . .

የሰው ልጆች በተፈጥሮአቸው መደላደልንና ብልኅ ምክርን ይሻሉ፤ስለ ችግሮቻቸው ወይም ስለ ጭንቀቶቻቸው ለሌላ ሰው መናገርም ይፈልጋሉ:: እነርሱ ደስታዎቻቸውንም ሆነ ኀዘኖቻቸውን አንድ ሌላ ሰው እንዲጋራቸው ይፈልጋሉ:: ይህን የሚያደርጉትም አንድን አንገብጋቢ ጉዳይ ካህን ለሆነ አንድ ሰው ወይም ለንስሓ አባት ወይም መምህር ወይም ጠባቂ ወይም ምሥጢር ለሚጠብቅ ሰው ወይም ለአሳዳጊ ገልጦ በመናገር ነው::

ከብሉይ ኪዳን አመለካከት አንጻር. . .

ንስሓ መግባት መሥዋዕት ለሚያቀርበው ኃጢአተኛ ሰው አስፈላጊ ነገር ነው፤እርሱ እጆቹን በመሥዋዕቱ ላይ በመጫን ኃጢአቱን በካህኑ ፊት ለእግዚአብሔር ይናዘዛልና:: በዚህ ጊዜ ካህኑ መሥዋዕቱን በመቀበል ይሰዋዋል፤ለኃጢአት ሥርየት ይሆን ዘንድም በመሰዊያው ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ ያቀርበዋል:: እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ ብሏል:- «ማናቸውም ሰው ሳይታወቀው ርኩስ ነገር ቢነኳ. . . በከንፈሩ ተናግሮ ቢምል. . . የሠራውን ኃጢአት ይናዘዛል:: ስለ

ሠራው ኃጢአት ለእግዚአብሔር የበደል መሥዋዕት ያመጣል. . . ካህኑም ስለ ኃጢአቱ ያስተሰርይለታል::» ዘሌ 5:1-6::

ይህ በመሆኑም ኃጢአተኛው ኃጢአቶቹን ሁሉ የመናዘዝ ግዴታ አለበት::

የዛራ ልጅ አካን በመስረቅ ኃጢአት በሠራ ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ልጆች ላይ ነድዳ ነበር:: ይህ በመሆኑም በጋይ ሰዎች ፊት በጦርነት ተመትተዋል:: በዚህ ጊዜ ኢያሱ የዛራ ልጅ የሆነውን አካን ወደ እርሱ ካስጠራው በኋላ እንዲህ ነበር ያለው:- «. . . ልጄ ሆይ:- ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፤ለእርሱም ተናዘዝ፤ያደረግኸውንም ንገረኝ አትሸሽገኝ. . .» በዚህ ጊዜ አካን ለኢያሱ «. . . በእውነት የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን በድያለሁ፤ እንዲህና እንዲህ አድርጌያለሁ::» (ኢያ 7:19-20) ነበር ያለው::

ዳዊት ዝሙት በመፈጸምና የመግደል ኃጢአት በፈጸመ ጊዜ ሕሊናው ሲወቅሰው ስላልቻለ እግዚአብሔር ነቢዩ ናታንን ወደ እርሱ በመላክ ኃጢአቱን እንዲህ በማለት እንዲናዘዝ አድርጎታል:- «. . . እግዚአብሔርን በድያለሁ አለው:: ናታንም ዳዊትን:- እግዚአብሔር ኃጢአትህን አርቆልሃል፤አትሞትም::» 2ኛ ሳሙ 12:13:: ከዚህ በኋላ ናታን ለዳዊት ኃጢአት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ቅጣት እንዲህ በማለት አረዳው:- «ነገር ግን በዚህ ነገር ለእግዚአብሔር ጠላቶች ታላቅ የስድብ ምክንያት አድርገሃልና ስለዚህ ደግሞ የተወለደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል. . .» 2ኛ ሳሙ 12:14:: ከዚህ በተጨማሪ ከቤቱ ሰይፍ እንደማይጠፋ፣ ከቤቱ ክፉ ነገር እንደሚነሣበት ሚስቶቹን ለዘመዶቹ እንደሚሰጥበትና በፀሐይ ፊት ከእነርሱ ጋር እንደሚተኙ ገልጦለታል:: 2ኛ ሳሙ 12::

በዚህ መሠረት የተወለደው የዳዊት ልጅ ሞተ፤አቤሴሎም በሕዝቡ ሁሉ ፊት ወደ አባቱ ቁባቶች ገባ፤እግዚአብሔር የተናገረውንም ሁሉ አደረገ:: 2ኛ ሳሙ 16:2-22::

ዳዊት በቤርሳቤህና በባሏ በኦርዮ ላይ የፈጸመው በደል በእግዚአብሔር ዘንድ በእርሱ ላይ እንደ ተፈጸመ ተደርጎ የተቆጠረ መሆኑን ጠቅሶ ማለፍ አስፈላጊ ነገር ነው:: ይህንንም ነቢዩ ናታን እንዲህ በማለት ገልጦታል:- «አሁንስ በፊቱ ክፉ ትሠራ ዘንድ የእግዚአብሔርን ነገር ለምን አቃለልህ? ኬጢያዊውን ኦርዮ በሰይፍ መትተሃል፤ሚስቱንም ለአንተ ሚስት ትሆን ዘንድ ወስደሃልና!. . .» 2ኛ ሳሙ 12:9::

ዳዊት ለነቢዩ ናታን ኃጢአቱን በተናዘዘ ጊዜ ኃጢአቱ እንደ ተወገደለትና በዚሁ ምክንያት ዘላለማዊ ሞትና ቅጣት እንደማይጠብቁት ቢያውቅም ለንስሓ የሚያበቁት እርግጠኛ ቅጣቶች እንደሚጣሉበት ግን

ተረድቷል:: ጠቢቡ ሰሎሞን እንዲህ ብሏል:- «ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል::» ምሳ 28:13::

ከአዲስ ኪዳን አመለካከት አንጻር. . .

መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ንስሓ ሲሰብክ እንዲህ ብሎ ነበር:-

«. . . መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ. . . ያን ጊዜ ኢየሩሳሌም፣ ይሁዳም ሁሉ፣ በዮርዳኖስም ዙሪያ ሁሉ ያለ አገር ወደ እርሱ ይወጡ ነበር፤ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር::» ማቴ 3:1-6::

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱና ለተከታዮቻቸው ሥልጣን የሰጣቸው «እውነት እላችኋለሁ:- በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈቱትም ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል»» (ማቴ 18:18) በማለት ነው:: ከትንሣኤው በኋላም እንዲህ በማለት ተናግሯል:- «ኢየሱስም ዳግመኛ:- ሰላም ለእናንተ ይሁን፤አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው:: ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና:- መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ:: ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል. . .» ዮሐ 20:21-23::

የጠፋው ልጅ ኃጢአቶቹን ሲገነዘብ ወደ አባቱ ተመልሶ እንዲህ በማለት ነው የተናገረው:- «. . . አባቴ ሆይ:- በሰማይና በፊትህ በደልሁ፤ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም. . .» ሉቃ 15:21::

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የሚነግረን በሐዋርያት ዘመን ምሥጢረ ንስሓ ተግባራዊ መሆኑን ነው:- «. . . አምነውም ከነበሩት እጅግ ሰዎች ያደረጉትን እየተናዘዙና እየተናገሩ ይመጡ ነበር::» ሐዋ 19:18::

መምህራችን ቅዱስ ያዕቆብም እ ንዲህ ነው ያለን:- «እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፤ትፈወሱም ዘንድ አያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ. . .» ያዕ 5:16::

በአንድ ወቅት አንድ ሰው ኃጢአቶቹን በሙሉ በካህኑ ፊት ሲናዘዝ ካህኑ የስርየት ጸሎት ያደርግለታል፣ እግዚአብሔር ኃጢአቶቹን ይቅር እንዲለው ይጠይቅለታል፣ ዳግመኛ ኃጢአት እንዳይሠራም እግዚአብሔር ይረዳው ዘንድ ይለምንለታል:: (ካህናትም ቢሆኑ ከእነርሱ በዕድሜም ሆነ በልምድ የሚበልጧቸው የንስሓ አባቶች አሏቸው::)

ማስታወሻዎች

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «. . . እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፤. . .» በማለት የተናገረው ተራው ሕዝብ ኃጢአቱን ለካህናቱ እንደሚናዘዘው ሁሉ ካህናቱም ኃጢአቶቻቸውን ለተራው ሰው ይናዘዙ ለማለት ፈልጎ አይደለም:: እርሱ ለመናገር የፈለገው:-

- የተማረው ያልተማረውን እንደሚያስተምረው እርስ በእርሳችሁ ተማማሩ
- ሀኪም በሽተኛውን እንደሚያክመውም እርስ በእርሳችሁ ተረዳዱ ለማለት ፈልጎ ነው::

ስለሆነም «. . . እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፤. . .» በማለት የተናገረው ጉባኤው ኃጢአትን ይቅር ለማለት ሥልጣኑ ላላቸው ሰዎች ኃጢአቱን መናዘዝ አለበት ለማለት ነው::

ፍቁረ እግዚእ ቅዱስ ዮሐንስም እንዲህ ብሎናል:- «በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው::» 1ኛ ዮሐ 1:9::

እኛ ካህኑ በተገኘበት በእግዚአብሔር ፊት በትሕትና እና በተፀፀተ ልብ ንስሓ ስንገባ እግዚአብሔር አምላክ ኃጢአቶቻችንን ይቅር በማለት ከዓመፃ ሁሉ ያነጻናል:: ቅዱስ አትናቴዎስ እንዲህ ብሏል:- «የተጠመቀ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እና በካህኑ አማካይነት ስለሚነሣሣ ንስሓ የሚገባው ሰው በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና በካህኑ አማካይነት ለኃጢአቱ ይቅርታ ያገኛል::»

ቅዱስ አውግስጦስም ይህን ብሏል:- «መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዋት ሲያስነሣው የተገነዘበትን ጨርቅ የፈቱለት በዙሪያው ያሉት (ደቀ መዛሙርቱ) ናቸው:: ሕይወትን የሚሰጠው አምላክ መግነዙን መፍታት ያቅተዋል እንዴ? ይሁን እንጂ ደቀ መዛሙርቱ መግነዙን በመፍታት ኢየሱስ ክርስቶስ ለእነርሱና ለተከታዮቻቸው የሰጣቸውን ኃጢአትን ይቅር የማለትና የማስተስረይ ሥልጣናቸውን ገልጠዋል::

የእንዚናዙ ጎርጎርዮስም እንዲህ ብሏል:- «የቤተ ክርስቲያኑን ካህን ለአንተ የተሰጠ መንፈሳዊ አባት አድርገህ ተመልከተው፤ ምሥጢራትህንም ለእርሱ በይፋ ግለጥለት:: አንድ በሽተኛ የተሸሸጉ ቁስሎቹን ለሀኪሙ በመግለጥ ከበሽታው እንደሚድን ትድናለህና::»

በሐዋርያት ቀኖና ውስጥ ደግሞ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል:- «የንስሓ አባቶች ከእግዚአብሔር ዘንድ በሕይወትና በሞት ላይ ሥልጣን ስለ ተሰጣቸው፣ በኃጢአተኞች ላይ የመፍረድና እነርሱን የመቅጣት

ሥልጣን ስለ ተሰጣቸውና የኃጢአተኞችን ኃጢአት የመፍታት ሥልጣን ስለ ተሰጣቸው እነርሱን የማክበር ግዴታ አለባችሁ::»

ሐዋርያዊቷ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ንስሓ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢር መሆኑን ታረጋግጣለች:: የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት በሙሉ የሚተገበሩት በካህኑ ብቻ ስለሆነም ይህ ምሥጢር ለካህኑ የማረሚያና የንስሓን አስፈላጊነት ማወቂያ ብርቱ ማረጋገጫ ነው::

ካህኑ የጌታ ሥጋና ደም በሚታደልበት በምሥጢረ ቁርባን ላይ የታመነ ስለሆነ ያለ እውነተኛ ንስሓ ለማንም ማቀበል እንደሌለበት ይጠነቅቃል:: አለበዚያ ስለ ቸልተኛነቱ በእግዚአብሔር ፊት በኃላፊነት ይጠየቃል፤ይፈረድበታልም:: አዲስ ካህን በሚሾምበት ሥርዓት ላይ ጳጳሱ ካህኑን እንዲህ የሚል ትእዛዝ ያዝዘዋል:- «ኪሩቤል የሕይወትን ዛፍ እንደሚጠብቃት አንተም ይህን ሀብትህን ጠብቀው:: ራስህን ከእነዚህ ምሥጢራት በማራቅ ኪሳራና ቅዣት ውስጥ እንዳትገባ ተጠንቀቅ:: ምሥጢራቱንም መልካም ጠባይና ንጹሕ ልብ ለሌላቸው ሰዎች አትስጥ:: አንተ በኃላፊነት ስለምትጠየቅ ኃጢአተኛው ዘላለማዊ ቅጣት እንዳይገጥመው ታደገው::»

እዚህ ላይ ካህኑ አንዱ ልበ ንጹሕ ሌላው ደግሞ ኃጢአተኛ ሆኖ ቅዱስ ቁርባን መቀበል የማይገባው ሰው መሆኑን ማወቅ የሚችለው እንዴት ነው ብለን በአግራሞት ልንጠይቅ እንችላለን::

ይህ የሚታወቀው በካህኑ ፊት በሚገባው ንስሓ አይደለምን? ካህኑ ምሥጢረ ንስሓን ተግባራዊ የማያደርገውን ሰው ምሥጢረ ቁርባንን እንዳይቀበልና ሌሎቹንም ምሥጢራት ተግባራዊ እንዳያደርግ የማገድ መብት አለው:: ይህንንም የሚያደርገው ልክ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለታመኑ ሐዋርያቱ እንደ ሰጠ ማለት ነው:: እርሱ እነርሱ ለቅዱስ ቁርባን የተገቡ ሰዎች መሆናቸውን በሚገባ ያውቅ ነበር:: በአንጻሩ ግን የአስቆሮቱ ይሁዳ ከፉና መጥፎ ሰው ስለ ነበር የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም አልተቀበለም::

ለካህናቱ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ንስሓ የተገባባቸው ኃጢአቶች ይቅርታ ስለሚያገኙ ለካህን ንስሓ መግባትና ስርየት ማግኘት ነፍስን ያጽናናል::

ለካህን ንስሓ መግባት ንስሓ የሚገባው ሰው ብልኅ ከሆነውና ልምድ ካለው ካህን መመሪያንና ምክርን ስለሚያስገኝለት ይጠቅመዋል:: ንስሓ የሚገባው ሰው የሚሰጠውን ምክር በታዛዥነት ተግባራዊ የሚያደርግ ከሆነ ኃጢአት ላለመፈጸም ከሰይጣን ጋር ከሚያደርገው ትግል ጥቅም ያገኛል::

ንስሓ ሲገባ ማፈር ነፍስ በኃጢአት ለመውደቋ የምትሸከመው ግድ የሆነ ቅጣት ነው:: ይሁን እንጂ በካህኑ የሚሰጠው ቀኖና በኃጢአቱ ላይ ተሣታፊዎች ለሆኑት ለነፍስና ለሥጋ የሚሰጥ የቤተ ክርስቲያን ቅጣት ነው::

ንስሓ የሚገቡ ብዛት ያላቸው ሰዎች በካህኑ ፊት ንስሓ ለመግባት በማፈር የሚሸሹት በቀጥታ የምንናዘዘው ለእግዚአብሔር ነው ስለሚሉ ነው:: ይሁን እንጂ ንስሓ በሚገባ ጊዜ ንስሓ የሚገባው ኃጢአተኛ ማፈርን መልመዱ እጅግ ይጠቅመዋል፤በእግዚአብሔር ፊት የሚሠራ ማንኛውም ኃጢአት ምንጊዜም ቢሆን አሳፋሪ ነውና:: በካህን ፊት ንስሓ ከመግባት ለመሸሽ ምክንያቶቹ ትዕቢትና ከንቱ ክብር ናቸው፤ ትዕቢተኞችና የሚኮሩ ሰዎች በካህኑ ፊት ራሳቸውን በትሕትና ዝቅ ማድረግ ለእነርሱ ከባድ ነገር ነውና::

ንስሓ የሚገቡ ሰዎች ንስሓ ሲገባ የሚሰጥ የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና በታዛዥነት የሚቀበሉ ከሆነ ንስሓቸው እውነተኛ ንስሓ መሆኑን በሚከተሉት ነጥቦች መመርመር አለባቸው:-

- መከልከል
- ለንስሓና ለትሕትና የሚደረግ ስግደት
- ለተቸገሩ ሰዎች ምጽዋት መስጠት
- ለ[illegible]ሱስ ቁርባን ለተወሰነ ጊዜ መታቀብ
- የተሰረቀ ወይም የተጭበረበረ ገንዘብን መመለስ
- የሰደብናቸውን ወይም ያስቀየምናቸውን ሰዎች ይቅርታ መጠየቅ::
- የእግዚአብሔርን ምሕረት ለመጠየቅ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ አብዝቶ መጸለይ

እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ቀኖናዎች (ቅጣቶች) የኃጢአተኛውን ቁስሎች የሚያክሙ ፍቱን መድኃኒቶች ናቸው፤በተነሳሒው ውስጥ ክብርንና መዋረድን ይተክላሉ፤ንቁ ሆነን እንድንዘልቅና ድጋሚ በኃጢአት እንዳንወድቅ የኃጢአት ጥላቻን በውስጣችን ያነሣሣል::

ተቀባይነት ያለው ንስሓ ለመግባት የሚወሰዱ አስፈላጊ ነጥቦች:-

- ቅጣትን በመፍራት የሚገባ ንስሓ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር የተነሣ የሚገባ እውነተኛ ንሥሓ:: እኛ ልናነጣጥር የሚገባን የእግዚአብሔርን የይቅርታ ጸጋ በምንቀበልበት መንፈሳዊ ድኅነት ላይ ሊሆን ይገባል::
- ያለ ምንም አድልዎ ለራሳችን ታማኞች መሆን:: ይህን በማድረግም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ነፍሱን የሚወድ

ያጠፋታል. . .» (ዮሐ 12:25) በማለት ከተናገረው ኃይል ቃል ሊርቅ ይችላል::

- ኃጢአትንና ምክንያቶቹን በማስወገድ ታማኝ አሳብንና ጽኑ ፈቃድን ገንዘብ ማድረግ::
- ሕሊናችንንና ራሳችንን በጥንቃቄ መመርመር:: ይህን በማድረግም በሥራ ወይም በአንደበት ወይም በአሳብ ወይም በስሜት የተፈጸሙ ኃጢአቶችን በመገንዘብ በድጋሚ በኃጢአት ላለመውደቅ ንስሓ መግባትና ራሳችንን በትሕትና ማዋረድ::
- በንስሓ ውስጥ እውነተኞች መሆን:: በዚህም ለንስሓ አባት መዋሸት ማለት ለመንፈስ ቅዱስ መዋሸት መሆኑን ማወቅ:: እንደ ምሳሌ አድርገን ብንወስድ ሐናንያ ለቅዱስ ጴጥሮስ በዋሸ ጊዜ እንዲህ ብሎታል:- «. . . ሐናንያ ሆይ:- መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ?:» ሐዋ 5:3::
- ማንኛውንም ምሥጢርና የተደበቁ አሳቦችን አለመሸሸግ:: ይልቁንም እነዚህን ምሥጢራት ሁሉ በካህኑ ፊት በገሃድ በመግለጥ ካህኑ ንስሓ ለሚገባው ሰው እጅግ አስፈላጊውን መድኃኒት በመስጠት መንፈሳዊ ሕይወቱን እንዲገነባ ያስችለዋል:: ነቢዩ ኤርምያስ ስለ ሰው ልጆች ነፍስ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- «በጌታም ፊት ልብሽን እንደ ውኃ አፍስሺ፤ . . .» ሰቆ.ኤር 2:19:: ውኃ እየፈሰሰ ሲወርድ ምልክት ወይም ሽታ ትቶ አያልፍም:: ዘይት ሲፈስስ ግን ምልክት ትቶ ያልፋል ወይን ጠጅ ሲፈስስም ከበስተኋላው ትቶ ያልፋል:: እኛም ከኃጢአቶቻችን ለመንጻት የምንፈልግ ከሆነ ከበስተኋላው ምንም ዓይነት ቅሪት ትቶ እንደማያልፈው እንደ ውኃ ንስሓዎቻችን በካህኑ ፊት ማፍሰስ አለብን::

ለራሳችን ምክንያቶችን (ስበቦችን) አንፈልግ፤ሌሎች ሰዎችንም አንውቀስ:: ንሥሓ ማለት ለተፈጸመ ኃጢአት ራስን መውቀስ እንጂ በሌሎች ሰዎች ላይ መፍረድ አይደለምና:: ንጉሥ ሰሎሞን እንዲህ በማለት ይመክረናል:- «. . . በመልአክም (በካህን) ፊት:- ስሕተት ነበረ አትበል፤. . .» መክ 5:6::

አንድ ሰው ለራሱ አግባብ ያለው መሆን አለበት እንጂ እጅግ የበዛ ኀዘን ወይም ጭካኔ ወይም ጥርጥር ወይም ጭንቀት ሊኖረው አይገባም:: ይልቁንም ኃጢአቱን በሳል በሆነ ሕሊና በግልጽ መናዘዝ አለበት::

ንስሓ የሚገባው ሰው ንስሓ አባቱ በሚሰጡት መመሪያዎች ላይ ሲጣበቅ ይገባዋል፤የእርሱን ምክር ለመንፈሳዊ ሕይወቱ አስፈላጊ መፍትሔ አድርጎ በትጋት ሊከተል ያስፈልገዋል።

ተነሣሒው በንስሓ አባቱ የሚሰጡትን መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች በፍቅርና በትዕግሥት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡- «ስለዚህ ወዳጆቼ ሆይ፡- ሁልጊዜ እንደ ታዘዘችሁ፤በእናንተ ዘንድ በመኖራ ብቻ ሳይሆን ይልቁን አሁን ስርቅ፤በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ . . .» ፊልጵ 2:12። ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስም እንዲህ ብሏል፡- «ለሥጋችን ፈውስ ስንል የህኪሙን የቀዶ ጥገና ቢላዋና የመድኃኒቱን ምሬት እንደምንችለው ሁሉ ነፍስም ለኃጢአትና ለደካም በሽታ ፈውስ እንድታገኝ ተግሣጽን፣ ቅጣትንና ሌሎች የተለያዩ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችን እንድታደርግ ማስቻል አለብን።»

ንስሓ የሚገባው ሰው ኃጢአቱንና የኃጢአቱን ዝርዝር ሁኔታዎች በሙሉ በድፍረት ያለ ኀፍረት መናዘዝ አለበት። የንስሓ አባቱ አንዳንድ ነጥቦችን አስመልክቶ ጥያቄዎች ካነሣለት ወይም ኃጢአቱንና የኃጢአቱን ዝርዝር ሁኔታዎች በሙሉ ካነሣለት ማሟሪር ወይም መልሱን መሸሸግ የለበትም፤ይልቁንም መልሱን በታማኝነት መመለስ አለበት አንጂ። እኛ ይህን ስናደርግ ካህኑ ጥያቄዎችን ለእኛ የሚያቀርብልን ለኛ የሚበጁ ምክሮችን ሊሰግሰን እንደ ሆነ ማወቅ አለብን።

ንስሓ የሚገባ አንድ ሰው በጸሎቱ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር መታገል አለበት። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ በማለት ተናግሮናል፡- «ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ኃጢአታችሁ እንደ አለሳ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፤እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዙ ትጠራለች።» ኢሳ 1:18።

ከንስሓ፣ ከስርየትና ከይቅርታ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ የንስሓን በር በመክፈት ከሞት አደገኛ ጎዳና ላይ ስላዳነን እርሱን ልናመሰግን ግድ አለብን። ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- «ክፋት እንደ አሳት ይቃጠላል፤ኩርንችቱንና እሾሁን ይበላል፤ጭፍቅ የሆነውንም ዱር ያቃጥላል፤ጢሱም ተትነልጉሶ እንደ ዓምድ ይወጣል።» ኢሳ 9:18። መምህራችን ቅዱስ ጴጥሮስም እንዲህ ብሏል፡- «. . . ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ከፈተና እንዴት እንዲያድን፤ በደለኞችንም ይልቁንም በርኩስ ምኞት የሥጋን ፍትወት እየተከተሉ የሚመላለሱትን ጌትነትንም የሚንቁትን እየቀጣቸው ለፍርድ ቀን እንዲጠብቅ ያውቃል።» 2ኛ ጴጥ 2:9-10። ንስሓ የገቡ ሰዎች በንስሓ አማካይነት ከዚህ ሁሉ ችግር ነጻ የወጡ መሆናቸውን ሲያውቁ ከኃጢአት ጋር በሚያደርጉት ትግል ውስጥ

ኃይልን ይቀበሉ። ዘንድ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ያጠናክራሉ ዘወትርም በእርሱ ይታመናሉ። እግዚአብሔርም የሥጋችንን ዝቃ ምኞትና ድካም በማሸነፍ በሰይጣንና በማታለያዎቹ ሁሉ ላይ ድል እንድንቀዳጅ ያደርገናል።

መምህራችን ቅዱስ ጳውሎስ ሲመክረን «ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ. . .» (ኤፌ 6:13) ብሎናል። ንስሓ የገባ አንድ ሰው በድጋሚ በራሱ ፈቃድ ወደ ኃጢአት እንዳይመለስ ንጹሕ በሆነው በንስሓ መንገድ ላይ መጓዝ አለበት።

በስውየው መንፈሳዊ ዕድገት ላይ ዘንምተንነትን ስለሚያስከትል አንድ ንስሓ የገባ ሰው አንዱን የንስሓ አባት በሌላው የንስሓ አባት መለወጥ አይገባውም። አጀግ በጣም ብርቱ ምክንያቶች ካልገጠመው በስተቀር ንስሓ የገቡ ሰዎች የንስሓ አባቶቻቸውን መለወጥ/መቀየር አይገባቸውም።

ንስሓ የገባ ሰው ለንስሓ አባቱ ብርቱ ፍቅር ሊኖረው፤ በሽተኞች በህኪማቸው ላይ እንደሚኖራቸው መታመን እርሱም በእርሱ ላይ ሊታመንና እርሱ የሚሰጣቸውን መመሪያ ተግባራዊ እንዲሚያደርጉም እርሱም ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባዋል።

ሁሉም ባልና ሚስት የትዳር ሕይወታቸው በመለኮታዊው ጥበቃ ውስጥ አንድ ይሆን ዘንድ ተመሳሳይ ወይም አንድ የንስሓ አባት እንዲኖራቸው እንመክራለን። ካህኑ ስለ ሕይወታቸው ስለሚያውቅ እነርሱን ስለ ቤተሰቡ ደኅንነት ሲል በተገቢው መንገድ ይመራቸዋል። በሁለቱ መካከል ከተፈጠረም የተሰየ አመለካከት ያላቸው ሦስተኛ ወገኖች ጣልቃ በመግባት በቤተሰቡ ላይ ችግር ከመፍጠራቸው በፊት ካህኑ ተክክለኛ መፍትሔ ይሰጣል። በመሆኑም ለሁለቱም የጋራ የሆነ አንድ የንስሓ አባት ሊኖር ግድ ነው።

ለንስሓ አባት የሚበጁ አስፈላጊ ሁኔታዎች፡-

- በሕጋዊ መንገድ የተሾመ ካህን መሆን አለበት።
- የሥነ ልቦና አውቀትና ልምድ ያለው እንዲሁም ስለ ነፍሳትና ስለ ጥልቀታቸው አውቀት ሊኖረው ያስፈልጋል።
- ለልጆቹ እንዲጸልይና ስለ ችግሮቻቸው እግዚአብሔር መፍትሔ እንዲሰጣቸው ይሰምን ዘንድ በመንፈሳዊነቱ ወደ እግዚአብሔር የቀረበ መሆን አለበት።

- ሁሉት ዓይነት ጠባይ የሌለው፤ብርቱ ሰብእና ያለው፤ አወነቱን ለመናገር የማይፈራ፤ማንም ይሁኑ ማን ኃጢአተኞችን የሚገሥጽ መሆን አለበት።
- ምንም ላይናወጥ ችግሮችን የማዳመጥ ችሎታ ይኖረው ዘንድ ጸድቅ ሰው መሆን አለበት። ንስሓ በሚገባው/በምትገባው ልጁ ላይ ትዕግሥቱን መግሰጥና እንደ ገዛ ልጆቹ ሊንከባከባቸው ግድ አለበት። ኃጢአቶቻቸውን መናዘዝ ይችሉ ዘንድ መደላደልን ሊሰጣቸው የሚችል ሰው መሆን አለበት።
- የደካሞችን ድካም መሸከም እንዲችል፤ ንስሓቸውን መቀበል እንዲችል፤ ላይጸየፋቸውና ላይፈርድባቸው ኃጢአቶቻቸውን ማዳመጥ እንዲችል፤ ሰዎቹ ንስሓ ሲገቡ ከልቡ የሚያዳምጣቸውና ሲናገሩ የሚፈልጓቸውን ነገሮች በመሉ እንዲናገሩ ዕድሉን የሚሰጣቸው መሆን አለበት። ከዚህ በኋላም ሰውየው የተናዘዘቸው ኃጢአቶቹ ወደፊት ቢገጥሙት ድል እንዲነሣቸው የሚያስችሉትን አስፈላጊ ምክሮችና መመሪያዎች መስጠት አለበት።
- ልጆቹ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ወደ መንዳት ይዳርሱ ዘንድ የተሳሳቱ መመሪያዎችን እንዳይሰጣቸው ልጆቹን ለመምራት በመንፈሳዊነት የበሰለና ልምድ ያለው መሆን አለበት።
- ካህኑ የመጽሐፍ ቅዱስ አውቀት እንዲሁም በሥነ ልቦና እና በትምህርቱ በቂ መረጃ ያለው ሊሆን ግድ ነው፤በዚህ የተሰየዩ የዕድገት ደረጃዎችንና ልዩ የሥነ ልቦና አርምጃዎችን መገንዘብ ይችላልና። ከዚህ በኋላም ሰውየው ኃጢአቱን እንዲናዘዝ ለማበረታታት ይችል ዘንድ ያለ ምንም የሕመም ስሜት ለእያንዳንዱ በሽታ ተፈላጊውን መድኃኒት ይሰጣል።
- የንስሓ አባት ንስሓን ለመቀበል በዕድሜው የገፋ፣ ሰው አክባሪና ረጋ ያለ መሆን አለበት፤ይህ ከሆነ እያንዳንዱ ተነሣሒ ሰው ያከብረዋል የሚናገረውንም ይሰማል።
- የሴቶችን ንስሓ እንዲቀበልና በራሱ ላይ ምንም ዓይነት ውድቀት ሳያደርስ በምክሩ እንዲመራቸው በእሳቡ፤ በልቡና በሥጋው ንጹሕ የመሆን ግዴታ አለበት።

- ምክንያቶቹ ምንም ይሁኑ ምን የሰዎችን ምሥጢራት ለማንም ሳለመግለጥ ታማኝ ሆኖ የመገኘት ግዴታ አለበት። የቤተ ክርስቲያን ሕግ ይህን ይከለክላል የሰዎችን ምሥጢራትና ንስሓዎቻቸውን በመግለጥ እነርሱን የሚያሳፍረውንም ካህን ይቀጣልና፤(የቅዱስ ባስልዮስ ሕግጋት- አንቀጽ 34)።
- ወደ እርሱ በመቅረብ ኃጢአቶቻቸውን በሚናዘዙት ሰዎች ላይ በጥበብ ተግባራዊ ያደርጋቸው ዘንድ የቤተ ክርስቲያን ሕግጋትን በሚገባ የማወቅ ግዴታ አለበት።
- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለልጆቹ በነበረው ፍቅር ውስጥ «ልጆቼ ሆይ፡- ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዘናል።» (ገላ 4:19) እንዳለ ካህኑም እርሱን መምሰል አለበት፤ እርሱ ልጆቹ በጽድቅ ሥራዎቻቸውና በጠባዮቻቸው እውነተኛ ክርስቲያኖች እስከሚሆኑ ድረስ ይደክምላቸው ነበርና።
- ካህኑ ንስሓ ሰሚገባ ሰው ንስሓ የመጽናናት ምንጭና ለመንፈሳዊ ሕይወት እድገት ጠቃሚ መሆኑን ማመን አለበት። አንድ ሰው ለእርሱ ኃጢአቱን በመናዘዙ መጽናናት የማይሰማው ከሆነና ሌላ የንስሓ አባት ለመቀየር የእርሱን ፈቃድ የሚሻ መሆኑን ከገለጠለት ፈጽሞ መከልከል የለበትም። ይህን የማያደርግ ከሆነ ግን ሰውየውን እንዲያምፅና ዳግመኛ ንስሓ እንዳይገባ ሊያደርገው ይችላል። ሰውየው የንስሓ አባት ለመሰወጥ የፈለገበትን ምክንያት ግን ካህኑ ቢያውቀው መልካም ነው፤ የማጽናናትና የመርዳት ምንጭ የሆነ ሌላ የንስሓ አባት እንዲመርጥ ሊረዳው ይችላልና። ካህኑ ተነሳሒው ሌላ የንስሓ አባት መለወጥ መፈለጉን የሚያምነው ከሆነ ግን ተነሳሒው ለካህኑ ሳያሳውቅ በቀጥታ ወደ ጳጳሱ በመሄድ ከእርሱ ፈቃድ ያገኘ ዘንድ ይጠይቃል። እዚህ ላይ ካህኑ ልብ ሊለው የሚገባው ነገር ቢኖር እርሱ ግላዊ በሆኑ ጉዳዮች (በጋብቻ ወይም በሥራ ውሳኔዎች) ላይ አማካሪ መሆኑን ነው። በመሆኑም የራሱን አመለካከት በሌሎች ሰዎች ላይ መጫን የለበትም።
- ማንኛውንም ሰው በተሰይም የንስሓ አባቶች የሌሏቸውን ንስሓቸውን ለእርሱ እንዲናዘዙ መገፋፋት የለበትም። አንድ ካህን ከእርሱ ጋር የሚያገለግሉ ካህናት በዚህ ዙሪያ የሚሰማቸውን ስሜት ማወቅ አለበት፤እንዘልና ወንድሙ ለሆነው ሌላ ካህን በቅርቡ

ንስሓ ለመግባት ያልፈቀደው ሰው ማን እንደ ሆነ ማሳወቅ አለበት።

በምስጢረ ንስሓ ውስጥ ካህኑ አባት፣ ፈራጅና መምህር ነው።

1/ አባት ነው።

ንስሓዎቻቸው ድጎነቶቻቸው ለእርሱ መዳን ምክንያት ስለሚሆኑለት ካህኑ ልጆቹ ሁሉ ወደ ንስሓ እንዲደርሱ ይናፍቃል፤ በመጨረሻውም ቀን ለእግዚአብሔር «እነሆ፡- እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች. . .» (ኢሳ 8፡18) በማለት ይናገራል። ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ሆኖም እንዲህ በማለት ያውጃል፡- «. . . እናንተ በጌታ ጸንታችሁ ብትቆሙ አሁን በሕይወት እንኖራለንና።» 1ኛ ተሰ 3፡8። በየዕለቱ የልጁን መመለስ ይጠባበቅ የነበረውን የጠፋው ልጅ አባት ይመስለዋል፡- «እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፤ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው።» ሉቃ 15፡20። ከዚህ በተጨማሪ ንስሓውን ተቀብሎ ኃጢአቶቹን ሁሉ ይቅር ብሎታል፤በመመለሱ ተደስቷል፤ሰታሳት ወንድሙም እንዲህ በማለት መልስ ሰጥቶለታል፡- «. . . ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበረ ሕያው ስለ ሆነ ጠፍቶ ነበረ ስለ ተገኘ ደስ እንዲለን ፍስሐም እንድናደርግ ይገባናል አለው።» ሉቃ 15፡32።

2/ ፈራጅ ነው።

ካህኑ «. . . በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።» (ማቴ 18፡18) ተብሎ በተሰጠው ሥልጣን አማካይነት በልጆቹ ጉዳይ ላይ ይፈርዳል። ካህኑ ለዚህ መለኮታዊ ኃላፊነት ተጠያቂ ስለሆነ ስለ ግላዊ ጉዳዩ ሲል በዚህ ሥልጣን አላግባብና በጭፍን መጠቀም አይችልም። ሰውየው ምንም ይሁን ምን በኃጢአት ላይ የሚወስደው አቋም ጥብቅ መሆን አለበት። ይህንንም ሊያደርግ በሽተኛውን እንደሚወደው ግን እንደሚጠላው ሐኪም መሆን አለበት፤ይህ ሐኪም ሊያገኘው በሚችለው በማንኛውም የሚሻል መድኃኒት በሽታውን ለማጥፋት ይሞክራልና።

3/ መምህር ነው።

እርሱ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ያስተምራል ወደ እርሱ የሚመጡትንም በሙሉ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ያደርጋቸዋል። እርሱ ባክበተው አውቀት፣ ልምድና ፈተና፣ በመታገዝ ልጆቹ ወደ እግዚአብሔርና ወደ ክርስትና የብቃት ደረጃ የሚደርሱበትን መንገድ ያስተምራቸዋል። ሰዎችን ለማስተማርና የክርስቶስ ሐዋርያት ለማድረግ የሚፈልግ ካህን እርሱ ራሱ ለንስሓ አባቱ ሐዋርያና ታማኝ ሰው ሊሆን ይገባዋል፤ይህ የእርሱ የንስሓ አባትም በዕድሜ የገፋ፣

ብልኀና ከእርሱ የሚበልጥ ልምድ ያለው መሆን አለበት። ብመሆኑም ካህኑ «. . . ክርስቶስ በቃልና በሥራ፣ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፣ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም፤. . .» (ሮሜ 15፡18) በማለት የተናገረው መምህራችንን ቅዱስ ጳውሎስን ይመስለዋል። እርሱ ልምድ፣ መማር እና ማስተማር ገንዘቦቹ ናቸውና።

ካህኑ ልጆቹ ምሥጢረ ንስሓን ተግባራዊ እንዲደረጉ በቀጥታ ስርየት እንደሚያገኙ ማስተማር አለበት። በቅዳሴ ላይ የሚሰጠው የቡድን ስርየት ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል በቂ ነው፤እያንዳንዱ ሰው ኃጢአቶቹን ሲያስታውስ በእግዚአብሔር ፊት ንስሓ ይገባል የካህኑን ስርየት ለመቀበልም በእርሱ ፊት ይንበረከካልና። በመሆኑም ካህኑ በዜሙ ክርስቲያን ውስጥ ስርየቱን ንስሓ ላልገባው ለእያንዳንዱ ሰው ማንበብ አይጠበቅበትም። ቅዱስ ቁርባን ከወረደ በኋላ የስርየቱን ንባብ ማንበብ ክብድ ስሕተት ነው፤ማስተሰረያው ራሱ (ቅዱሱ ምሥጢር) በመሠዊያው ላይ ቀርቧልና። ታላቁ ሲቶ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ በመሠዊያው ላይ ቀርቦ ካህኑ ይህን በመዘንጋት ስርየት መስጠቱ ትክክል አይደለም።

ካህኑ ለልጆቹ በቂ መንፈሳዊ ልምምዶች ለመስጠት ጥንቃቄ ማድረግ ይገባዋል፤አነርሱ አስቀድመው በእነርሱ ዘንድ የነበሩትን ኃጢአቶችና ክፉ ልማዶች በማስወገድ በፋንታቸው የጽድቅ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ያደርጋቸዋልና።

ካህኑ እነዚህን ልምምዶች ከእነርሱ ጋር ሆኖ የሚከታተለው ለእነርሱ በመጸሰይና ስለ እነርሱ በእያንዳንዱ ንስሓ ውስጥ ልመና በማቅረብ መሆን አለበት። ካህኑ የማስታወሻ ደብተር ቢኖረው መልካም ነው፤ካህኑ ይህን ደብተሩን በመመልከት ለእነርሱ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ውስጥ በመከከታተል ይረዳቸዋልና።

ምሥጢረ ንስሓን ተግባራዊ የማድረግ ሥርዓት።

ሀ/ ንስሓ ከመግባት በፊት

የንስሓ ጊዜ ከአንድ ወር ወይም ከአንድ ወር ተኩል መብለጥ የለበትም። ከዚህ የሚዘገይ ንስሓ ሰውየውን ቸልተኛ ያደርገዋል፤ የፈጸማቸውን ኃጢአቶችም እንዲረሳ ያደርገዋል። የሚዘገይ ንስሓ ሰሰውየው ታላቅ ኪሣራ ከመሆኑም በላይ የሰውየውን መንፈሳዊ ዕድገት መዘግየት በገሃድ ይገልጣል።

አንዳንድ የንስሓ አባቶች ንስሓ የሚገቡ ልጆቻቸውን ስም መዝግበው የሚይዙበት ማስታወሻ ደብተር ስላላቸው በመጀመሪያ

ንስሓ የገቡበትን ቀንና የሚቀጥለውን ንስሓ የሚገቡበትን ቀን መዝግበው ይይዛሉ። እንዲህ ያለው ነገር ተነሳሒው ሰው ዘወትር ንስሓ ለመግባት የተዘጋጀ እንዲሆን ያደርገዋል።

ንስሓ የሚገቡ ሰዎች ንስሓ ለመግባት ከመሄዳቸው በፊት ራሳቸውን ለመመርመር ይችሉ ዘንድ በመጀመሪያ ከራሳቸው ጋር መቀመጥ አለባቸው። በመሆኑም ንስሓ ለመግባት በመጀመሪያ ነቢዩ ኤርምያስ እንደ ተናገረ እግዚአብሔር አምላክ ኃጢአቶቻቸውን በመግለጥ እንዲረዳቸው እንዲህ አሉ ይጸልያሉ፡- «የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው፤ማንስ ያውቀዋል? እኔ እግዚአብሔር ሰለው ሁሉ እንደ መንገዱ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን አመረምራለሁ።» ኤር 17፡9-10።

ሰንኰሉ በመዘጋጀት ውስጥ የተፈጸመ ኃጢአቶችን በመሉ በቀራጭ ወረቀት ላይ መመዝገብ የሚመከር ነገር ነው። ይሁን እንጂ አመዘጋገቡን መዝጋቢው ሰው ብቻ ሊረዳው በሚችለው መንገድ መሆን አለበት። ይህ የሚደረገውም ወረቀቱ ብትጠፋም በሌላ ሰው እጅ ንብታ እንዳትነበብ ነው። ስለሆነም ኃጢአትን መዝግቦ ከመያዝ በስተ ጀርባ ያለው ጥበብ በንስሓ ጊዜ የተፈጸመ ኃጢአቶችን ላለመርሳት ስለሚረዳ ነው።

አንድ ንስሓ የሚገባ ሰው ለንስሓ በሚያደርገው ዝግጅት ውስጥ ሰሦስት ጠቃሚ ነገሮች ትኩረት መስጠት አለበት፤እነዚህንም መዝግቦ ይይዛል፡-

የተፈጸሙ ስሕተቶችና ኃጢአቶች

- መልካሙን ከመጥፎው ለመለየት ይቻል ዘንድ በተፈጸመ አላባቸና ስሜቶች ላይ ከንስሓ አባት ምክር መቀበል።
- መንፈሳዊ ሕይወትን በተመለከተ በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ከንስሓ አባት ጋር ውይይት ማድረግና ምክር መቀበል።
- ራስን መመርመር ሌሎች ሰዎችን ባለመውቀስና በታማኝነት መፈጸም አስበት፤ንስሓ ስንገባ መውቀስ ያለብን ራሳችንን ወይም ሁኔታዎችን እንጂ ሌሎች ሰዎችን መሆን የለበትምና።
- ሰዎች ንስሓ ለመግባት ዝግጁ ከሆኑ በኋላ ወደ ግል ክፍላቸው ገብተው የሠሯቸውን ኃጢአቶች በመሉ በእግዚአብሔር ፊት በመግለጥ እርሱን በጸሎት ይቅርታ ይጠይቁታል፤ከዚህ በኋላም እነዚህን ኃጢአቶች የሚተዉባቸውን ኃይል እንዲያድላቸው ይማጸኑታል።

ይቅር የሚባሉ ኃጢአቶች ሦስት ጊዜ ንስሓ ሊገባባቸው ግድ ነው፡-

ሀ/ ኃጢአቱን በፈጸምንበት ሰው ፊት። ጠቢቡ ንጉሥ ሰሎሞን ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «ልጄ ሆይ፡- ይህን አድርግ፤ራስህንም አድን፤በጎረቤቶችህ እጅ ወድቀሃልና፤ፈጥነህ ሂድ፤ ጎረቤትህንም ነዝንዝው። ለዓይንህ እንቅልፍ፣ለሽፋሽፍቶችህም እንቅልፍን አትስጥ፤እንደ ሚዳቋ ከእጓኖ እጅ እንደ ወፍም ከአጥማጅ እጅ ተድን ዘንድ።» ምሳ 6፡3-5።

ለ/ በእግዚአብሔር ፊት፡- እርሱ እኛ ኃጢአት ለፈጸምንባቸው ሰዎች ሁሉ ኃላፊነት ያለው አባት ነውና። ዳዊት በቤርሳቤህና በባሏ በኦርዮ ላይ ኃጢአት በፈጸመ ጊዜ እንዲህ ያለውን ኃጢአት በቀጥታ በእርሱ ላይ የተነጣጠረ አድርጎ ስለ ቆጠረው ዳዊትን እንዲህ በማለት ወቀሳት ነበር፡- «ስለዚህም አቃልለኸኛልና፤. . .» 2ኛ ሳሙ 12፡10። ዳዊትም ኃጢአቱን በመናዘዝ «እግዚአብሔርን በድያለሁ. . .» (2ኛ ሳሙ 12፡13) ብሏል። የንስሓ መዝሙር በሆነው በመዝሙር 50 ውስጥም ነቢዩ ዳዊት ኃጢአተኛ ሰው መሆኑን እንዲህ በማለት ገልጦአል፡- «አንተን ብቻ በደልሁ፤በፊትህም ክፋትን አደረግሁ፤. . .» መዝ 50፡4።

ሐ/ በቤተ ክርስቲያን ፊት። ቤተ ክርስቲያን የምትወክለው በካህኑ ነው። ቤተ ክርስቲያን እናታችን ስለ ሆነች ለእኛ ለልጆቿ ሰላም፣ ለፍቅራችንና እርስ በእርሳችን ለመታረቃችን ትደክምልናለች። ካህኑ የሰላም ርግብ ስለሆነ ትክክለኛ የሆነውን ሰው መብት ተነክሰኛ ካልሆነው ሰው መብት ጋር ያስማማል። ንስሓ የሚገቡ ሰዎች ለኃጢአታቸው የሚሆነውን ስርየትና ይቅርታ የሚቀበሉት ሰእግዚአብሔር ምሥጢራት ቡራኬ ከሚሰጠውና እውነትን ወይም የሰውን ኃጢአት ከሚመለከተው ከካህኑ ነው። ካህኑ ተነሳሒው ሰው ተቀባይነት ያለው ንስሓ እንዲገባ ሁኔታዎችን የሚያዋሃሉት ቀኖና ጾቹንና አንዳንድ መንፈሳዊ አንትስታሲዎችን በመስጠት ስለሚረዳው ነው።

ይህ ሁኔታ ከተከናወነ ንስሓ የገባው ሰው ሥልጣንን ከመንፈስ ቅዱስ በተቀበለውና «በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእኔ በኩል የሚሆን ስርየታችውን አድሳችው» በማለት በሚጸልየው ካህን አማካይነት ስርየቱንና ይቅርታውን ይቀበላል። ይህ ስርየት አንድ ጊዜ በካህኑ በኩል ከተከናወነ ንስሓ የገባው ሰው የኔታችን የአማኑኤልን ቅዱስ ቁርባን ይቀበላል፤ኃጢአቶቹም በፈሰሰው በክርስቶስ ደም ይታጠባሉ። ይህ የሚሆንለትም ልብሳቸውን በበጉ ደም እጥበው እንዳነጹት (ራእ 7፡14) (1ኛ ዮሐ 1፡7) ተብሎ እንደተጻፈላቸው ቅዱሳን ነው።

ሰ/ ንስሓ በሚገባ ጊዜ

በኃይል መሞላታችንና መንጻታችን ይታወቀን ዘንድ ንስሓችን የሚከናወነው በቤተ ክርስቲያን አንጻር በሚገኝ ሞር ያለ ስፍራ ላይ መሆን አለበት። ንስሓ ምሥጢር እንደ መሆኑ መጠን ምንጊዜም ቢሆን መከናወን ያለበት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሆን አለበት። ይሁን እንጂ ካህኑ በየዕለቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን የማይመጡና ለክርስትና ሕይወት አዲስ የሆኑ ነገር ግን ንስሓ መግባት የሚፈልጉ ሰዎች ቢያጋጥሙት በሰዎቹ ቤት ተገኝቶ ንስሓቸውን ሊቀበላቸው ይችላል፤በተመሳሳይ ጊዜም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ ይጋብዛቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ሰዎች ቅዱስ ቁርባን ከመቀበላቸው በፊት ታመው በቤታቸው ቢተኙ ምሥጢረ ንስሓ በቤታቸው ውስጥ ይፈጸምላቸዋል።

ካህኑ ንስሓን ሲቀበል አካላዊና መንፈሳዊ ዝግጅት በሚያስፈልገው ቅዱስ ምሥጢር ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ላይ ስለሆነ ካባ ወይም ቆብ መልበስ አለበት።

ንስሓ ለመግባት በመጠባበቅ ላይ ላሉ ሰዎች መቆያ ይሆን ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ራሳቸውን ባተሉ የሚያደርጉበት በመጻሕፍት የተሞላ ክፍል መኖር አለበት።

ካህኑ ዘወትር ንቁ መሆን አለበት። ንስሓ በሚቀበልበት ቀን ንስሓ ምሥጢር ስለሆነ መብላትም ሆነ መጠጣት የለበትም። በመሆኑም ይህ ምሥጢር እንደ ሌሎቹ ምሥጢራት በጸም ውስጥ መከናወን አለበት። ንስሓ የሚገቡ ሰዎች የካህኑን እጅ ለመሳለም ሲመጡ በእርሱ ፊት በክብር ይቀመጣሉ፤እርሱ በመንፈስ ቅዱስ ፊት የእግዚአብሔር ምሥጢራት ሁሉ አገልጋይ ነውና።

ካህኑና ንስሓ የሚገባው ሰው በትምዕርተ መስቀል ካማተቡ በኋላ «አባታችን ሆይ» የሚለውን ጸሎት በኀብረት ይጸልያሉ።

ከዚህ በኋላ ካህኑ ንስሓ የሚገባውን ሰው ስለ መንፈሳዊ ሕይወቱ በመጠየቅ ኃጢአቶቹን እንዲናዘዝ ያበረታታዋል።

በዚህ ጊዜ ተነሣሒው ሰው ኃጢአቶቹን የዘረዘረበትን ወረቀት በማውጣት እያንዳንዱን ኃጢአት ያለ ምንም እፍረት ወይም ፍርሃት በዝርዝር ይናዘዛል። ከዚያም የንስሓ አባቱ የሚሰጠውን ተገቢ ምክርና መመሪያ ይጠባበቃል። ይህን ሁኔታ ጥፋት ከሠራ በኋላ የጸኖውን ፍርድ የሚጠባበቀውን ወንጀለኛ ወይም በሽታውን ለማከም የሚችሉ መድኃኒቶችን ከሐኪሙ ለመስማት የሚጠባበቀውን በሽተኛ ሰው ይመስላል። ንስሓ ተቀባዩ ካህን ንስሓ የሚገባውን ሰው ኃጢአቶች በመሉ ማወቅና እስከ ሞት ድረስ እነዚህን ኃጢአቶች በፀፀት ውስጥ ሆኖ መዋጋትን ዓላማው አድርጎ መነሣቱን መገንዘብ አለበት። ከካህኑ

ጋር የሚደረገው ውይይት በክብርና በመልካም ሥነ ምግባር መከናወን አለበት።

ንስሓ የሚገባው ሰው በመጀመሪያ እጅግ የከፉ ኃጢአቶቹን በመናዘዝ ይጀምርና ቀሰል ያሉትን ያስከትላል። እንዲህ ባለው መንገድ ተነሳሒው ትሕትናን ገንዘቡ ያደርጋል።

ሌሎች ንስሓ የሚገቡ ሰዎች እንደሚጠብቁት በማወቅ ተነሣሒው ከንስሓው ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸውን ታሪኮችን በመተረክ የካህኑን ጊዜ ማባከን የለበትም። በመሆኑም ተነሳሒያኑ በመሉ የዚህን ምሥጢር ክብርና በመንፈስ ቅዱስ ፊት መቆማቸውን ልብ ማለት አለባቸው።

ንስሓ የሚገቡ ሰዎች ተስፋ እንዳይቆርጡ ካህኑ አነርሱን ማውገዝ ወይም ማዋረድ የለበትም። በእንጻሩም ካህኑ ንስሓ ሲቀበል ልል መሆን የለበትም፤ተነሳሒው ኃጢአቱን ለመናዘዝ ቸልተኛ ይሆናልና። ካህኑ ተነሳሒያኑ ኃጢአቶችና ውድቀቶች ቢኖሩባቸውም እርሱ ለእነርሱ ብልኅ፣ የማይከብድና እነርሱን የሚወድ መሆን አለበት።

ከንስሓ በኋላ ንስሓ የሚገባው ሰው በካህኑ ፊት በመንበርከክ ጭንቅላቱን ዝቅ ካደረገ በኋላ «አምላክ ሆይ፡- እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ. . .» (ሉቃ 18:13) የሚሉትን ቃላት መላልሶ ይናገራቸዋል። ከዚህ በኋላ ካህኑ ከተቀመጠበት ተነሥቶ በቀኝ እጁ የያዘውን መስቀል በተነሳሒው ጭንቅላት ላይ ያሳርፍና የሥርየቱን ጸሎት ይጸልያታል።

ማስታወሻዎች

ካህኑ መስቀሱን ንስሓ በሚገባው ሰው ጭንቅላት ላይ ያስቀምጠዋል። በዚህም የስርየትና የይቅርታ ስጦታ የሚገኘው በመስቀል ላይ በፈሰሰው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም መሆኑን ያረጋግጣል። ጭንቅላት ከኃጢአት ሸክም የተነሣ ይሰግዳል፤በእርሱ ላይ የተቀመጠው መስቀልም ንስሓ የሚገባውን ሰው በካህኑ አማካይነት ለሰርየትና ለይቅርታ በሚጠራው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በአሳቡ፣ በሥጋውና በነፍሱ በተአምር ያነጻዋል። በዚህ ጊዜም በእግዚአብሔርና በተነሳሒው ሰው መካከል ዕርቅ ይፈጠራል፤ መምህራችን ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ነገረን ማለት ነው፡- «. . . በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ሰራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና።» (ቆላ 1:20)፤«ነገር ግን የሆነው ሁሉ፡- በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከእርሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፤ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ።» 2ኛ ቆሮ 5:18፤19።

ካህኑ እጁን ንስሓ በመግባት ላይ ባለው ሰው ራስ ላይ ሲጭንና ግራና ቀኝ ያሉትን ጠፍጣፋ የግንባር ክፍሎች (temples) በጣቶቹ መያዙ በርኅራኄ የተሞላው የእግዚአብሔር አባትነት ንስሓ የሚገቡ ሰዎችን የሚቀበል መሆኑን ያመለክተናል። ከዚህ በተጨማሪ የዚህ ምሳሌነቱ የእግዚአብሔርን እጅ ያመለክተናል፤ በዚህም እርሱ ሰዎችን ሁሉ በእጁ ውስጥ መያዙንና የሰዎችን እንቅስቃሴና አሳብ መቆጣጠሩን ያመለክተናልና። ይህን በማድረጉም እነርሱን ስለ ደህንነታቸውና ስለ ድኅነታቸው ያነጻቸዋል ወደ ትክክለኛውም አቅጣጫ ይመራቸዋል፡- «. . . ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፤. . .» 2ኛ ቆሮ 10:5። ሐዋርያው ቅዱስ እንደ ተናገረም፡- «እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን።» (1ኛ ቆሮ 2:16) ብለን መናገር እንችላለን። በዚህም የእግዚአብሔር አገልጋዮች በመሆናችንም እርሱን እናመልካለን፤ ፊቱን እናያለን፤ ስሙም በግምባሮቻችን ላይ ይሆናል፡- «. . . ባሪያዎቹም ያመልኩታል፤ ፊቱንም ያያሉ፥ ስሙም በግምባሮቻቸው ይሆናል።» ራእ 22:3-4። በዚህ ጊዜም የእግዚአብሔር ስም አፋቸውንም ሆነ ሕይወታቸውን ይሞላል።

ስርየት መቀበል ይቻል ዘንድ ንስሓ በሚገባው ሰው ሊደገሙ የሚገባቸው ጸሎቶች።

መዝ 50፡ «አቤቱ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤. . .»

የንስሓ ጸሎት፡- «አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፡- በፈቃዳችንም ሆነ ያለ ፈቃዳችን፤ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፤የሚታየውንና የማይታየውን ኃጢአታችንን አስተሠርይልን፤ አጥፋልን፤ ይቅርም በልልን። አቤቱ ጌታ ሆይ፡- በእኛ ላይ ስለሚጠራው ቅዱስ ስምህ ስትል ይቅር በለን፤ ይህም እንደ እንተ ቸርነት እንጂ እንደ እኛ ኃጢአት አይሁን።» ተነሣሒው በዚያው አስከትሎ፡- «አቤቱ ጌታዬ ሆይ፡- እኔ ኃጢአት ሠርቼያለሁና እንተ ኃጢአቴን ደምስስልኝ።» ይላል። ወይም ደግሞ እንደ ቀራጩ ጸሎት «እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ» በማለት ይጸልያል።

ከዚህ በኋላም ሥርየቱን ተከትሎ «አቡነ ዘበሰማያት» ይደገማል።

ይህ ካበቃ በኋላም ንስሓውን የተቀበለው (የናዘዘው) ካህን በተነሣሒው ራስ ላይ የስርየት ጸሎቶችን ይጸልያል። ይህ ሁኔታ ሰሦስት ጊዜ ያህል ይደገማል። ከዚህ በተጨማሪ ኃጢአተኛው ከኃጢአቱ ተመልሶ ንስሓ ስለገባም ለእግዚአብሔር ምስጋና ያቀርባል።

ካህኑ ንስሓ በገባው ሰው ራስ ላይ እጆቹን በመጫን የሚያደርሳቸው ጸሎቶች።

እነዚህ ጸሎቶች ሦስት የስርየት ጸሎቶች ናቸው። እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር ካህኑ ራሱን ከተነሣሒው ሰው ጋር በመደመር ጸሎቶቹን በብዙ ቁጥር እያደረገ መጸለዩን ነው። በእነዚህ የስርየት ጸሎቶች ውስጥም ካህኑ ስርየትና ይቅርታን ከሌሎች በረከቶች ጋር የሚጠይቀው ሰራሱና ሰተነሣሒው ሰው ነው። በእነዚህ የስርየት ጸሎቶች ውስጥ ብዛት ያላቸው ትርጉም የሚሰጡ፣ ተመስጦ የሚገባቸውና ልብ የሚነኩ ልመናዎችና ይገኛሉ። ካህኑና ተነሣሒው ሰው በእያንዳንዷ ቃል ላይ በተመስጦ እንዲቆዩ ካህኑ ጸሎቶቹን ድምፅ ሳያወጣና እያወጣ ይደግማቸዋል። ንስሓ በሚገባው ሰው ራስ ላይ የሚደገሙት እነዚህ ሦስት የስርየት ጸሎቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚደረጉት በነግህ፣ በምሽትና በሌሎች የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ማለትም በምሥጢረ ቁርዳል፣ በምሥጢረ ተክሊልና በሌሎቹም ሥርዓቶች ላይ እንደሚነበቡ መጥቀስ ተገቢ ነው።

አንደኛው የሥርየት ጸሎት። ለተሸነፈ (ለተማረከ) ልጅ የሚደረግ ጸሎት ተብሎም ይታወቃል።

«አቤቱ እባቡንና ጊንጡን እንድንረግጠውና በጠላት ኃይል ላይ ሁሉ ሥልጣን እንዲኖረን አድርገህ የሰጠሽን ጌታ ሆይ፡- እነዚህን የሰይጣን ራሶች ከእግራችን በታች ቀጥቅጥልን፤እኛን የሚቃወመንን ማንኛውንም የድካም ዕቅዱንም በፊታችን በታትንልን። አቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አንተ የእኛ ሁሉ ንጉሥ ነህና።»

ከአንደኛው የሥርየት ጸሎት የተወሰዱ ማስታወሻዎች።

እግዚአብሔር አምላክ ንጹሐን ሰሆኑ ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ በማለት ሥልጣን ሰጥቶአቸዋል፡- «እነሆ፡- እባቡንና ጊንጡን ትረግጣ ዘንድ፡- በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለው፤ የሚጎዳችሁም የለም፡።» ሉቃ 10:19።

«ራሶቹን ከእግራችን በታች ቀጥቅጥልን፤» የምንለው ሰይጣን ብዙ ራሶች እንጂ አንድ ራስ ስለሌለው ነው። እነዚህ ራሶቹ የሚወክሉትም ብዛት ያላቸው የተሰያዩ ዕቅዶቹንና ማታለሎቹን፤ አሳቦቹንና ማሰላቶቹን ሲሆን እነዚህም ወደ እነርሱ የተሳቡትን ስለሚያጠፏቸው ነው።

«እኛን የሚቃወመንን ማንኛውንም የድካም ዕቅዱንም በፊታችን በታትንልን።» ሰይጣናዊ ዕቅዶች ሰይጣን በእኛ ውስጥ ሊተክላቸው የሚሞክራቸው ክፉ አሳቦች ናቸው። እነዚህ ክፉ አሳቦች ወደ ጥፋት እንዳያደርሱን ነው እግዚአብሔርን በፊታችን በታትንልን የምንለው።

ሁለተኛው የሥርየት ጸሎት፡፡ ለተሸነፈ (ለተማረከ) ልጅ የሚደረግ ጸሎት ተብሎም ይታወቃል፡፡

«ሰማይና ምድርን የፈጠርህ አንተ እግዚአብሔር ሆይ፡- ስለ እኛ ድኅነት ስትል ከሰማያት ወርደህ ሰው ሆነሃል፡፡ አንተ በሱራፌልና በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ ጌታ ስትሆን የተዋረዱትን ትመለከታለህ፡፡ አሁንም ዐይኖቻችንን የምናነሣው ኃጢአታችንን ይቅር ብለህ ነፍሳችንን ከጥፋት ወደምታድናት ወደ አንተ ወደ ጌታችን ነው፡፡ እኛ የምናመልከው ሊናገሩት የማይችሉትን ርኅራኄህን ነው፡፡ የምንጠይቅህም የአንተን ሰላም እንድትሰጠን ነው፤ አንተ ሁሉንም ነገር ለእኛ ሰጥተኸናልና፡፡»

«አዳኛችን እግዚአብሔር ሆይ፡- እኛ ከምንጠራው ከአንተ ቅዱስ ስም በቀር ማንንም ስለማናውቅ የራስህ አድርገን፡፡ እግዚአብሔር ሆይ፡- አንተን የምንፈራና አንተን የምንፈልግ አድርገህ መልሰን፡፡ እኛ በአንተ መልካም ነገሮች ላይ ተጠግተን ደስ ስለ ተሰኘን ደስ ይበልህ፡፡ ራሶቻቸውን ከአንተ እጅ በታች ዝቅ ዝቅ ያደረጉትን በሕይወት መንገዳቸው ላይ ከፍ-ከፍ አድርጋቸው፤በቅድስናህም አስጊጣቸው፡፡ እኛ ሁላችን በሰማያት ያለች የክርስቶስን መንግሥት በእርሱ ፈቃድ፣ በአባቱ በእግዚአብሔር አብ ፈቃድና በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ መልካም ፈቃድ ለመውረስ ያብቃን. . .»

ከሁለተኛው የሥርየት ጸሎት የተወሰዱ ማስታወሻዎች፡፡

በዚህ የስርየት ጸሎት ውስጥ ካህኑ እግዚአብሔርን እንዲህ እያለ ይጠይቃል፡-

- እሳት ጭድን እንደሚያቃጥል ኃጢአት ሰላምን ስለሚያጠፋ ኃጢአት በመሥራት ያጠፋነው ሰላማችንን ስጠን፡፡ እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- «ለክፉዎች ሰላም የላቸውም. . .» ኢሳ 48:22፡፡
- «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት. . .» (ምሳ 1) ስለሆነ አንተን መፍራት በውስጣችን አሳድር፡፡ የአንድ ሰው ልብ እግዚአብሔርን በመፍራት የተሞላ ከሆነ መንፈሱ ስለሚነሣሣ እንደ አባ እንጦንስ እንዲህ ይላል፡- «ብርሃን ወደ አንድ ቤት ውስጥ ሲገባ ጨለማን እንደሚያስወግድ ሁሉ እግዚአብሔርን መፍራት ወደ አንድ ሰው ልብ ሲገባም አለማወቅን (በኃጢአት የሚወድቅበትን) ያስወግዳል፡፡»
- ኃጢአት በሚያሠሩንና መጨረሻቸው በሞት በሚጠቃለለው ነገሮች ተሳታፊዎች ከምንሆን ይልቅ አንተን እንድንሻህና መንፈሳዊና መለኮታዊ የሆኑትን ነገሮች እንድናጣጥም

አድርገን፡፡ በዚህ ምክንያት ካህኑ ይህን መሻት እግዚአብሔር ንስሓ ወደሚገቡት ሰዎች ልብ እንዲመልስ ይጠይቃል፤ እነርሱም ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር በመሆን «ሳበኝ፤ከአንተም በኋላ እንሮጣለን፤ . . .» (መኃ 1:4) ይላሉ፡፡

- ካህኑ በፀፀት ከእግዚአብሔር እጅ (ንስሐ በሚገባው ሰው ራስ ላይ በተጫነው በካህኑ እጅ በሚመሰለው) በታች ያጎነበሰውን ተነሣሒ እግዚአብሔር ራሱ ከፍ-ከፍ እንዲያደርገው ይጠይቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከኃጢአት ከአዳናቸው በኋላ በቅድስና እንዲያስጌጣቸው፣ እርሱን እንዲያከብሩና ለዘላለማዊው ሕይወትና ለዘላለማዊቷ የእግዚአብሔር መንግሥት የበቁ እንዲሆኑ ይጠይቃል፡፡ ይህች ዘላለማዊት የእግዚአብሔር መንግሥት የተዘጋጀችውም ቅድስናቸውን ፍጹም ለማድረግ በጽናት ለታገሉት ሰዎች ነው፡፡

ሦስተኛው የሥርየት ጸሎት፡፡ ለተሸነፈ (ለተማረከ) ልጅ የሚደረግ ጸሎት ተብሎም ይታወቃል፡፡

ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው የእግዚአብሔር አብ አንድ ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን በሕይወት ሰጪ መከራውና በማዳኑ ማንኛውንም የኃጢአታችን ቀንበር አጥፍቷል፡፡ እርሱ በቅዱሳን ሐዋርያቱ ፊት ላይ እፍ በማለት «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡፡ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸውም ተይዞባቸዋል. . .» ብሏቸዋል፡፡ ጌታችን ሆይ፡- አሁንም ቢሆን በአንተ ቅዱሳን ሐዋርያት አማካይነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚያገለግሉ ካህናት ኃጢአትን በምድር ላይ እንዲያስሩና እንዲፈቱ ጸጋቸውን አድለዋቸዋል፡፡ የሰው ልጆችን የምትወድ እግዚአብሔር ሆይ፡- አሁንም ለአገልጋዮችህ አባቶቼ፣ ለወንድሞቼ፣ ለእኔና ከአንተ ቅዱስ ክብር በታች ራሶቻቸውን ዝቅ ዝቅ ላደረጉት ተነሣሒያን ምሕረትን እንድታደርግ የአንተን ቸርነት እንጠይቃለን እንለምናለንም፡፡ ምሕረትህን አድለን፤ማናቸውንም የኃጢአት ቀንበሮች ፍታልን፤በአንተ ላይ ማንኛውንም ኃጢአት በማወቅ ወይም ባለማወቅ ወይም በተጨነቀ ልብ ወይም በሥራ ወይም በአንደበት ወይም በዛለ ልብ ሠርተን ቢሆንም ይቅር በለን፡፡ አቤቱ ጌታ ሆይ፡- አንተ የሰውን ድካም ታውቃለህና እንደ መልካምና እንደ አፍቃሪ አምላክነትህ ኃጢአቶቻችንን ይቅር በለን . . . አንተ ባርከን፣ አንተ አንጻን፣ አንተ ኃጢአቶቻችንን አስተሥርይልን፡፡ አንተን በመፍራት ሙላን፣ አንተ የእኛ አምላክ ስለ ሆንህ ወደ አንተ ቅዱስና መልካም ፈቃድ ምራን፤ ክብር፣ ምስጋና፣ ጌትነትና አምላክነት ሁሉ ለአንተ ብቻ ይሁኑ፤አሜን፡፡

ከሦስተኛው የሥርየት ጸሎት የተወሰዱ ማስታወሻዎች፡፡

በትዕምርተ መስቀል እየተማተበ ይህ የስርየት ጸሎት ሲደገም መንፈስ ቅዱስ ንስሓ በሚገቡት ሰዎች ላይ በመውረድ እነርሱ በካህኑ ፊት ለመንፈስ ቅዱስ የተናዘዙትን ኃጢአት ይቅር ይላቸዋል፡፡

ይህ የስርየት ጸሎት ለተለያዩ የኃጢአት ዓይነቶች ይቅርታ ይጠይቃል፡- «. . . በአንተ ላይ ማንኛውንም ኃጢአት በማወቅ ወይም ባለማወቅ ወይም በተጨነቀ ልብ (በፍርሃት) ወይም በሥራ ወይም በአንደበት ወይም በዛለ ልብ (በበታችነት፣ ራስን በማዋረድና በኀዘን) ሠርተን ቢሆንም ይቅር በለን፡፡» የምንለው ለዚህ ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠልም እግዚአብሔር ፍቱን የሆኑትን መድኃኒቶች «አንተ ባርከን፣ አንተ አንጻን፣ አንተ ኃጢአቶቻችንን አስተሥርይልን፡፡» በማለት ይጠይቃል፡፡ ኃጢአተኛው ሰው እነዚህን መለኮታዊ መድኃኒቶች ሲታደል ከኃጢአት ህመሙ ስለሚድን ወደ ዘላለማዊ ሕይወት በሚወስደው መንገድ ላይ በቅድስና ሊጓዝ ይጀምራል፡፡

ከስርየቱ በኋላ ካህኑ ኃጢአተኛውን ሰው ከባረከው በኋላ ንስሓ የገባው ሰው ከእርሱ ጋር አብሮ በሚደግመው የዘወትር ጸሎት (አቡነ ዘበሰማያት) ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም ካህኑ ንስሓ በገባው ሰው ፊት ላይ ሦስት ጊዜ እፍ በማለት ቅድስት ሥላሴ ኃጢአቱን እንዲያስተሠርዩለትና ይቅር እንዲሉት ይጠይቃል፡፡

በዚህ ጊዜ ንስሓ የገባው ሰው በጉልበቶቹ ተንበርክኮ መሬቱን በግንባሩ ካስነካ በኋላ ብድግ ብሎ የካህኑን መስቀልና እጅ ይሳለምና «ይፍቱኝ አባቴ» ሲል ካህኑ «እግዚአብሔር ይፍታህ!» ይሉታል፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ ንስሓ በመግባቱ፣ በመላእክትና በቅዱሳን ሰዎች ውዳሴ ከፍ ከፍ እያለ ንስሓውን ይፈጽማል፡- «. . . ንስሓ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሓ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል፡፡» ሉቃ 15:7፡፡ ከንስሓ በኋላ ንስሓ የገባው ሰው ከልቡ ላይ ታላቅ ሸክም ሲነሣለት ይታወቀዋል፡፡ ይህ ሸክም የኃጢአት ሸክም ሲሆን ንስሓ የገቡት ከተነሣላቸው በኋላ ነጻ ይሆናሉ፣ ድል አድራጊነት ይሰማቸዋል፣ ንስሓ ገብተው ከዳኑና ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ከሚገቡት ከሌሎች ብዛት ካላቸው ተነሣሒያን ጋር አብረው ለመግባትም ተስፋቸውን ያድሳሉ፡፡

ማስታወሻ፡፡

ንስሓ የገባው ሰው «ይፍቱኝ አባቴ» በማለት ስርየቱን ሲጠይቅ ካህኑ «እግዚአብሔር ይፍታህ» የሚለው ኃጢአትን የሚያስተሠርየው

እግዚአብሔር ስለሆነ ነው፤እርሱ የስርየትና የይቅርታ መገኛ ምንጭ ነውና፡፡

ከንስሓ በኋላ፡፡

ከንስሓ (ከስርየት) በኋላ ተነሳሒዎች ወዲያውኑ ቅዱስ ቁርባን ይቀበላሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉትም በጸጋው ኃይል በጽድቅ ሥራዎች እንዲያድጉና በመንፈሳዊው ትግል ውስጥ ብርታት እንዲያድጉ ነው፡፡ ከንስሓ በኋላ ንስሓ የገባው (ኃጢአቱ የተሠረየችለት) ሰው የምስጋና ጸሎት ያደርሳል፡፡ ይህ ጸሎት የሚያመሰግነው እግዚአብሔር የሰዎችን ንስሓ ስለ ተቀበለ ሲሆን በዚህም እግዚአብሔር ንስሓ የገቡትን ሁሉ በንስሓ ሕይወታቸው እንዲበረቱ እንዲረዳቸውና ለእርሱ ታማኞች እንዲሆኑ የሚጠይቅ ጸሎት ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ንስሓ የገቡት ሰዎች በድጋሚ በኃጢአት እንዳይወድቁ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ንቁዎች መሆን አለባቸው፤እያንዳንዱ ኃጢአት የሚመጣው በቸልተኝነት ወይም በስንፍና ነውና፡፡ እነዚህ ሰዎች የንስሓ አባቶቻቸው የቤተ ክርስቲያንን መመሪያዎች፣ ንስሓን ወይም መንፈሳዊ ቀኖናዎችን አስመልክተው የሚሰጧቸውን ምክርና መመሪያ መቀበል አለባቸው፤እነዚህ ቁስሎቻችንን በማከም ለማጥፋትና ህመሞቻችንን ድካሞቻችንን ለማስወገድ ፍቱን መድኃኒቶች ናቸውና፡፡

እኛ በጸጋና በመንፈሳዊ አቋም እንድናድግ ከተፈለገ በመንፈሳዊው አባት ምክር ላይ የተጣበቅን መሆን አለብን፡፡ ቅዱስ ባስልዮስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «እኛ ሰውነታችንን ለማከም ስንል መራራ የሆኑ መድኃኒቶችን እንደምንወስድ ሁሉ ከኃጢአት በመንፈሳዊ ህክምና ለመዳንም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በተግሣጽና በቅጣት የምንቀበለውን መድኃኒት መቀበላችንም ግድ ነው፡፡» እግዚአብሔር አምላክ ሲያስተምረንም «ወደ ዘለፋዬ ተመለሱ፤ እነሆ መንፈሴን አፈስስላችኋለሁ፤ቃሌን አስተምራችኋለሁ፡፡» (ምሳ 1:23) ብሎናል፡፡

አንድ ካህን ለሌላ ካህን የሚገባው የንስሓ ሥርዓት፡፡

እያንዳንዱ ካህን በዕድሜና በክህነት የአገልግሎት ጊዜ የሚበልጠው የንስሓ አባት ሊኖረው ግድ ነው፤እርሱ ለዚህ የንስሓ አባቱ ኃጢአቱን በመናዘዝ የእርሱ ደቀ መዝሙር ይሆናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «. . . ነገር ግን ለሌሎች ከለበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ፡፡» 1ኛ ቆሮ 9:27፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ካህን የሚከተለውን የመምህራችንን የቅዱስ ጳውሎስን ምክር አጥብቆ

መከተል አለበት፡- «ሰራስህና ለተምህርትህ ተጠንቀቅ፤በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህ።»

ካህኑ ንስሓ ሲገባ አንድ በሽተኛ ክሐኪሙ ፊት ለፊት እንደሚቀመጥ ከንስሓ አባቱ ፊት ለፊት መቀመጥ አለበት። ከዚህ በኋላ ስርየት፣ ይቅርታና ድኅነት በመጠየቅ በአውኅት ያለ ሐሰት ንስሓ ይገባል።

ከንስሓ በኋላ ካህኑ የቅስና ጥምጥሙን ወይም ቆቡን ከራሱ ላይ ካወለቀ በኋላ ስርየቱን ለመቀበል በንስሓ አባቱ ፊት ተንበርክኮ ራሱን ዝቅ ያደርጋል።

ስርየቱ በሚሰጥበት ጊዜም የንስሓው አባት ካህን መስቀሉን ንስሓ በሚገባው ካህን ራስ ላይ አያኖርም፤በትከሻው ላይ እንጂ። ወይም ደግሞ መስቀሉን ንስሓ ወደሚገባው ካህን ራስ በማስጠጋት ራሱን ሳያስነካ ለተገባው ንስሓ ተገቢ የሆኑትን የስርየት ጸሎቶች ያደርሳል።

የስርየት አሠጣጡ ሥርዓት ማብቂያ ላይም ንስሓ የሚገባው ካህን ራሱን ዝቅ አድርጎ የንስሓ አባቱን መስቀልና እጅ በመሳለም ስለ ታደለው የስርየት ጸጋ እና በንስሓውና በስርየቱ ስላገኘው ይቅርታ እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

ማስታወሻዎች።

የሚናገዘው ካህን ንስሓ በሚገባው ካህን ራስ ላይ መስቀሉን የማይጭነው በክህነት ማዕረግ እኩል ስለሆነ ነው። ይህ ይሁን እንጂ በረከት በአረጋዊው ለወጣቱ እንደሚታደል ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ገልጦልናል፡- «. . . ሴላ ካህን በመልክ ጼዴቅ ምሳሌ ቢነሣ ይህ አጅግ አብልጦ የሚገሰጥ ነው።» ዕብ 7:17።

አንድ ካህን በአንድ ጳጳስ ፊት ንስሓ ቢገባ ጳጳሱ ንስሓ በሚገባው ካህን ራስ ላይ መስቀሉን ጭኖ የስርየት ጸሎቱን መጸለይ ይችላል፤አርሱ ከካህኑ በማዕረግ ይበልጣልና።

ለከሃድያን የሚደረግ ጸሎት።

ክርስቶስን የካዱት (ከሐድያን/አሕዛብ) ወይም ሥጋቸውን በዝሙት ያረከሱት ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን አንደ ተመሰሱ ቤተ ክርስቲያን አስቀድማ የንስሓን ምሥጢር አታድልም። ይልቁንም ለእነዚህ ሰዎች «የከሃድያንን ጸሎት» ወይም «የብቃትን ጸሎት» ታደርሳለች። በዚህ ጸሎት ውስጥም የእግዚአብሔር ምሕረት ለሚያስፈልጋቸው አጅግ ከባድ ኃጢአቶች ይቅርታ ይጠየቃል።

ይህ በጥቅምና በመንፈሳዊት የተሞላ ጸሎት የተወሰደው አባ ዮሴፍ አባታ ከጻፉትና «Make Me Repent Lord» በሚለው ርዕስ ከሚታወቀው መጽሐፍ ገጽ 160-166 ላይ ነው። ይህ ጸሎት እግዚአብሔር በረከትና ኃይል እንዲያድል የሚጠይቅ ጸሎት ነው።

ለከሃድያን የሚደረግ ጸሎትና ሥርዓቱ።

አዲስ ሸክላ ሥራት የውኃ ገበቴ በንጹህ ውኃና ካህኑ ሦስት ጊዜ በሚያፈስሰው በማንኛውም ዘይት ከተሞላ በኋላ በትዕምርተ መስቀል ያማትብበታል። ከዚያም፡-

ካህኑ የምስጋና ጸሎት ይደግማል።

በጸሎቱ ጊዜም ካህኑ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዕጣን በማጠን ድምፁን ከፍ አድርጎ የአባ ጳውሊን ጸሎት እንዲህ አደለ ይጸልያል፡- «ጥንትና ፍጻሜ የሌለህ ታሳቁና ዘላሰማያዊው እግዚአብሔር ሆይ፡- አንተ በምክርህና በሥራህ ኃያል አምላክ ነህ፤ አንተ በሁሉም ቦታ ላይ አለህ፤ በአያንጻንዱም ሰው ውስጥ ታድራለህ። ስለሆነም ጌታችን ሆይ፡- በዚህች ሰዓት በእኛ መካከል ተገኝ በእኛም ውስጥ አደር። ልባችንን እንጻ ነፍሳችንንም አጥራ። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሠራናቸውን ኃጢአቶቻችንን አንጻ፤ በአንተ ፊትም ተገቢ መሥዋዕቶችን (የበረከት መሥዋዕቶችን) እና በመጋረጃው ውስጥ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ አልፎ የሚገባ መንፈሳዊ ዕጣን ለማቅረብ የበቃን አድርገን።» (ከዚህ በአራቱም አቅጣጫ ዕጣኑን በማዕጠንቱ ያጨሳል።)

ጉባኤውም «አቡነ ዘበሰማያት» ይደግማል።

ከዚያም በኋላ «አቤቱ፡- እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤» የሚለው 50ኛው የዳዊት መዝሙር ይደገማል።

ይህ ከሆነ በኋላ ይንበረከኩና «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፡- እኛ ከቸር አባትህ ከአግዚአብሔር አብ እና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እናመልክሃለን፤ ወደዚህ ዓለም መጥተህ አድነኸናልና።»

ከዚህ በኋላ ዲያቆኑ የሚከተለውን የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ያነባል፡-

«ወደ መቄዶንያ በሄድሁ ጊዜ አንዳንዶች ልዩ ትምህርትን እናዳያስተምሩና ወደ ተረት፤ መጨረሻም ወደ ሌለው ወደ ትውልዶች ታሪክ እንዳያደምጡ ልታዛቸው በኤፌሶን ትቀመጥ ዘንድ ለመንሁህ፤ እንደ እነዚህ ያሉ ነገሮች ክርክርን ያመጣሉና፤በእምነት ግን ሳለ

ለእግዚአብሔር መጋቢነት አይጠቅሙም። የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ሕሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው፤ ከእነዚህም አንዳንዶች ስተው የሚሉትን ወይም ስለ እነርሱ አስረግጠው የሚናገሩትን ሳያስተውሉ የሕግ አስተማሪዎች ሊሆኑ እየወደዱ ወደ ከንቱ ነገር ፈቀቅ ብለዋል።

ነገር ግን ሰው እንደሚገባ ቢሠራበት ሕግ መልካም እንደ ሆነ እናውቃለን፤ይኸውም ለበደለኞች ለማይታዘዙ፣ ለዓመፀኞችና ለኃጢአተኞች፣ ቅድስና ለሌላቸውና ለርኩሳን፣ አባትንና እናትን ለሚገድሉ፣ ለነፍስ ገዳዮችና ለሌሰኞችና፣ ከወንድም ጋር ለሚተኙ፣ በሰዎችም ለሚነግዱ፣ ለውሸተኞችም በውሸትም ለሚምሉ፣ የእግዚአብሔርንም ክብር እንደሚገልጥ ለእኔ አደራ እንደ ተሰጠኝ ወንጌል የሆነውን ደኅና ትምህርት ለሚቃወም ሌሌላ ነገር ሁሉ ሕግ እንደ ተሠራ እንጂ ለጻድቅ እንዳልተሠራ ሊያውቅ ነው።

ለአገልግሎቱ ሾሞኝ ታማኝ አድርጎ ስለ ቆጠረኝ፣ኃይል የሰጠኝን ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታችንን አመሰግናለሁ፤ አስቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ፤ አንገላችም ምንም ብሆን፤ይህን አደረገልኝ፤ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን ስላደረግሁት ምሕረትን አገኘሁ፤የጌታችንም ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ ካሉ ከእምነትና ከፍቅር ጋር አብልጦ በዛ። ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉም እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ፤ስለዚህ ግን የዘላለምን ሕይወት ሰማግኘት በእርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው ሰዎች ምሳሌ እንድሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና በምሆን በእኔ ላይ ትዕግሥቱን ሁሉ ያሳይ ዘንድ ምሕረትን አገኘሁ። ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘላለም ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፤አሜን።» 1ኛ ጢሞ 1:3-17።

ጉባኤው ኪራላይሶን ይላል።

በማስከተልም ካህኑ የወንጌልን ጸሎት ያነባል። ከዚያ በፊት ግን መዝሙረ ዳዊትን ከማንበቡ በፊት «የመዝሙር መምህራችን የሆነው የነቢይና የንጉሡ የዳዊት በረከት በእኛ ላይ ይደር፤አሜን።» ይላል። ቀጥሎም «አቤቱ፡- ምሕረትህንና ቸርነትህን አስብ፤ከጥንት ጀምሮ ናቸውና። የልጅነቴን ኃጢአትና መተላለፍ አታስብብኝ፤ አቤቱ፡- ስለ ቸርነትህ ብዛት እንደ ምሕረትህ አስበኝ። . . . አቤቱ ኃጢአቴ እጅግ ነውና፤ስለ ስምህ ይቅር በለኝ።» መዝ 24:6፤7፤11። ወንጌላዊና ንጹሕ ሐዋርያ የሆነው የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል እናነባለን፤ የእርሱ በረከት ከእኛ ከሁላችንም ጋር ይሁን፤አሜን። «ይህንም ምሳሌ ነገራቸው፤ እንዲህ ሲል፡- መቶ በግ ያለው ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋ ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ የጠፋውን እስኪያገኘው ድረስ ሊፈልገው የማይሄድ ከእናንተ ማን ነው? ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከመዋል፤ወደ ቤትም በመጣ ጊዜ ወዳጆቹንና ጎረቤቶቹን በእንድነት

ጠርቶ፡- የጠፋውን በጎን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላቸዋል። እላችኋለሁ እንዲሁ ንስሓ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሓ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።» ሉቃ 15:3-7። ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለሙ ድረስ ለእኑ ይሁን።

ከዚህ በኋላ ጉባኤው ሰወንጌሉ ተገቢውን ምላሽ እንዲህ በማለት ይሰጣል፡- «ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፡- ኃጢአት የሌለበት አገልጋይና ይቅርታ የማያደርግ ጌታ ስለሌለ በድያለሁና ይቅር በለኝ። ጌታዬ ሆይ፡- ከሞት በፊት ንስሓን አድለኝ፤በፊቱ ያሉትን የሲያል ደጃፎችም ዝጋልኝ። የሰማይ ሠራዊት መሪ የሆንኸው ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ሆይ፡- ኃጢአቶቻችንን ይቅር በልልን። አባቶቻችን ሐዋርያትና ደቀ መዛሙርት ሆይ፡- ጌታችን ኃጢአቶቻችንን ይቅር ይሰን ዘንድ ስለ እኛ ለምኑልን። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፡- የእንተ፣ የአባትህና የመንፈስ ቅዱስ ስም ዛሬም፣ ዘውትርም እስከ ዘላለሙ ድረስ የተባረከና የተቀደሰ ይሁን፤አሜን።

ከዚህ በኋላ ካህኑ፣ አባቶችና ጉባኤው ሦስት ዋና ዋና የንስሓ ጸሎቶችን ያደርሳሉ።

ለጉባኤው የታደሉት ጸሎቶች ማብቂያ ላይ ንስሓ የሚገባው ሰው ከጉባኤው ጋር በጎበረት የሃይማኖት ጸሎት ይጸልያል።

ከዚህ በኋላ ካህኑ የሚከተለውን ጸሎት ንስሓ ለሚገባው ሰው እንዲህ አደሰ ይጸልያል፡- «ጌታና ኃያል የሆንኸው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር ሆይ፡- ሁሉም ሰው በሕይወት እንዲኖርና ወደ አውነት አውቀት እንዲደርስ የምትፈልገው እግዚአብሔርና አፍኝ የሆንኸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፡- በክህደት ውስጥ ሰናረው (በክህደት ውስጥ የቆየው ሰው ስም ይጠቀሳል) እና አንተን በመካድ ክህበሰለ በኋላ አሁን በፊትህ ራሱን ዝቅ አድርጎ ከሰይጣንና ከሌሎች ከማናቸውም መጥፎ ነገሮች ሁሉ እንድታድነው እንጠይቅሃለን። የሰው ልጆችን የምትወድ ቸር እግዚአብሔር ሆይ፡- የእንተን ቸርነት የምንጠይቀውና የምንለምነው መንፈስ ቅዱስንና የእንተን ኃይል በዚህች ሰዓት ለዚህ ባሪያህ (በክህደት ውስጥ የቆየው ሰው ስም ይጠቀሳል) እንድትልክለት እንለምንሃለን። በልቡ ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ክፋትና መጥፎ እርግማን እስወግድለት። ልቡን ከማንኛውም መጥፎ አሳብ እንጸለት።

ሥጋውን ከማያምኑ ሰዎች ጋር አርክሶ ከሆነም ይቅር በለውና በነቢያት፣ በሐዋርያትና በአባቶች ወደ ተሰበከው ወደ ጽድቅ ሕይወት አምጣው። ይህን የእንተ ባሪያ (በክህደት ውስጥ የቆየው ሰው ስም ይጠቀሳል) የመንግሥትህ ወራሾች ከሆኑት መንጋዎችና ሕዝቦችህ ጋር

አንደ አድርገህ ቁጠረው። ከተወለደበት ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን ድረስ የሠራቸው ኃጢአቶቹን በመሉ ይቅር በለው፤በመንፈስ ቅዱስ መውረድና በእርሱ ላይ ማደር አስቀድሞ የተቀበለውን የጥምቀት ጸጋም አያጣውም። ባርከው፣ ቀድሰው፣ አንጻው፣ አንተን በመፍራት መሓው፣ ወደ አንተ በጎ ፈቃድም ምራው። የእግዚአብሔር እናት በሆነችው በእናታችን በቅድስት ማርያምና በሉሎች ቅዱሳን ሰዎች አማላጅነት ይቅር በለው። ስለ አንድ ልጅህ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ስትልም ይቅር በለው። ክብር፣ ምስጋና፣ ገዢነትና አምልኮ ከአባቱ ከእግዚአብሔር፣ ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዛሬም ዘውትርም እስከ ዘላለመ- ድረስ ይሁን፤አሜን።»

ንባኩው «አቡነ ዘበሰማያትን» ይደግማል።

ከዚህ በመቀጠልም የሚከተሉትን ልመናዎች ያቀርባል፦ «አምን ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ። እኛ ደካሞች ነንና አንተ ከምንችለው በላይ አንዳንፈተን አድነን። ከጠላት ወደ እኛ የሚወነጨፉትን አሳታዊ ፍላጻዎች አነዚህ ልመናዎቻችን ያቀዝቅዟቸው። ከዲያብሎስና ከጠብ ጫሪነቱ አንተ አድነን። ክብርና ምስጋና ለአንተ ይሁን፤አሜን።»

አዚህ ላይ ዲያቆኑ «ራሶቻችሁን በእግዚአብሔር ፊት በፍርሃት ዝቅ-ዝቅ አድርጉ።» ይላል።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ካህኑ የሚከተለውን የስርየት ጸሎት ያደርሳል፦ «ንፍሳችንን፣ ሥጋችንና መንፈሳችንን የምታድን ልዑል እግዚአብሔር ሆይ። አንተ ተቀዳሚና ተከታይ በሉለው በአንድ ልጅህ ለአባታችን ለቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ተናግረሃል፦ 'እኔም አልሃለሁ። አንተ ጴጥሮስ ነህ፣በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፣የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች አሰጥሃለሁ፤በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፤በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።' ስለሆነም አቤቱ

እግዚአብሔር ሆይ። አቤቱ የሰው ልጆችን የምትወድ እግዚአብሔር ሆይ። ባሪያህ (በክህደት ውስጥ የቆየው ሰው ስም ይጠቀሳል) ከማንኛውም ኃጢአት፣ ከማንኛውም እርግማን፣ ከማንኛ ውም ክህደት፣ ከማንኛውም የሐሰት መሓላ ከማንኛውም ከመናፍቃንና ከአረመኔዎች ግጭት በመንፈስ ቅዱስ ሁሉ የተፈታ አድርገው። የዓለሙን ኃጢአት የምታጠፋው እግዚአብሔር ሆይ። የባሪያህን ንስሓ ለኃጢአት ይቅርታና ለመረዳት ብርሃን አድርገህ ለመቀበል ፍጠን፤አንተ ርኅሩኅና ይቅር ባይ አምላክ ነህና። አንተ ታጋሽ አምላክ ነህ። ምሕረትህ ታላቅና አውነተኛ ነው። ሰውን የምትወድ እግዚአብሔር ሆይ። ይቅር በለው።»

ዲያቆኑም «መንፈስህን ልክህ አድነው፤አሜን።» ይላል።

ከዚህ በኋላ ካህኑ በውኃው ላይ ሦስት ጊዜ በመስቀል ያማትባል፤አንዲህ አያለ። «ቅዱሳት ለቅዱሳን ሰዎች፤የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስና የመንፈስ ቅዱስ ማንጻት የተባረክ ይሁን፤አሜን።»

ንባኩውም አንዲህ አያለ ተመስጥውን ይመልሳል። «ቅዱስ አብ አንድ ነው፤ቅዱስ ወልድ አንድ ነው፤ቅዱስ መንፈስ ቅዱስም አንድ ነው፤አሜን።»

በመጨረሻም ንባኩው «እግዚአብሔርን አመስግኑ. . .» (መዝ 150) የሚለውን መዝሙር በማዜም ላይ ሳለ ካህኑ ጥግ ላይ በመጋረጃ በተከለለ ቦታ ላይ ልብሱን እንዲያወልቅ ካደረገው በኋላ እንዲህ አያለ ውኃውን ሦስት ጊዜ ይረጨዋል። «ባሪያህን (በመ- ይጠቀሳል) አጠብቀዋለሁ፤በእግዚአብሔር አብ ስም፤በእግዚአብሔር ወልድ ስምና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም፤አንድ አምላክ፤አሜን።»

ካህኑ ውኃውን በተነሣሒው ሰው ራስ ላይ ካፈሰሰና ከረጨው በኋላ ዘይቱን ሻንዛሩ፣ ልቡና መዳፉ ላይ ይቀባዋል፤ እንዲህ አያለ። «የሁሉም ፈጣሪ እግዚአብሔር አብ የተባረክ ይሁን፤አሜን። ቀዳሚና ተከታይ የሌለው የእግዚአብሔር አብ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የተባረክ ይሁን፤አሜን። አጽናኙ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የተባረክ ይሁን፤አሜን።»

መቀባቱ ካበቃ በኋላ ተነሣሒው ልብሱን ሰብሶ ራሱን ዝቅ ሊያደርግ ካህኑ እንዲህ ይላል። «ጌታ፣ አምላክና ብቸኛው እግዚአብሔር ሆይ። አንተ ወደዚህ ዓለም የመጣኸው ኃጢአተኞችን ወደ ንስሓ ልትጠራ እንጂ ሞትን በኃጢአት ላይ ልታመጣ አይደለም። አንተ ወደዚህ ዓለም የመጣኸው ሰለሶች ንስሓና ሕይወትን ልታመጣ ነው። አንተ እኮ ወንድምህ በቀን ውስጥ ሰባት ጊዜ ቢበድልህና ሰባት ጊዜ ወደ አንተ 'በድዬሃለሁ' ብሎ ቢመጣ ይቅር በለው በማለት ያስተማርህ አምላክ ነህ። ጌታችንና ንጉሣችን እግዚአብሔር ሆይ። አሁንም አንተ በፊትህ ራሳችንን ዝቅ-ዝቅ ያደረግነው እኛ ኃጢአተኛ ባሮችህን ተመልከተን፤ በዚህ በባሪያህ (በክህደት ውስጥ የቆየው ሰው ስም ይጠቀሳል) ልብ ውስጥ ያሉትን ክፉ አሳቦች አስወጣለት፣ ኃጢአቶቹን ሁሉ ይቅር በለው፣ የውበትህን ክብር ታላቅነት እንዲመለከትም ከክፋው ጨለማ ውስጥ ነጻ አውጣው።

ጌታ ሆይ። ከኃጢአታችን፣ ከበደላችንና ከመተላለፋችን ነጻ አንወጣ ዘንድ አንተ አርዳን። ወደ አነዚህ ነገሮች ዳግመኛ አንዳንመለስም ፍቀድ፤ይልቁንም ከወደቅንበት አንሣን፤ በኃይልህ ከአኛ ጋር ተራመድና ከሰይጣን ትዝኅሳ አድነን። በአውነት ወደ አንተ መልሰን

ሕያዉታችንን ነጻ አውጣና ክርክሰት ሁሉ አንጻን፤ከማንኛውም ንጹሕ ወዳልሆነ አሳብ ከማንደልም ነጻ አውጣን። ኃጠአቶቻችንን ደምስስልንና አውን አድነን፤በክፉ መናፍስት ላይ በሚበረታ በአንተ ኃይል አንድንበረታም አድርገን። በአንተ በአግዚአብሔር አብ መልካም ፈቃድ፤ በልጅህ በአግዚአብሔር ወልድ መልካም ፈቃድ እና በሕይወትህ በአግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የዳንን አውነተኛ ታጋዮች አድርገህ ቁጠረን፤ዛሬም፣ ዘወትርም አስከ ዘላለም ድረስ፤አሜን።»

ይህን ጸሎት ተከትሎ ካህኑ ለአግዚአብሔር ወልድ ሦስተኛውን የስርየት ጸሎት ያደርሳል። «ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው የአግዚአብሔር አብ አንድ ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ . . .»

ከዚህ ሁሉ በኋላ ካህኑ ንስሓ ለገባው ሰው ኃጢአትን በድጋሚ እንዳይሠራ ያገዘዋል። በረከቱን በማነብነብ ካደለው በኋላ ሁሉቱም «አቡነ ዘበሰማያት» በኀብረት ይጸልያሉ።

መንፈሳዊ ልምምዶች።

ብዙ ካህናት በንስሓ ጊዜ ለንስሓ ልጆቻቸው አንዳንድ መንፈሳዊ ልምምዶች መስጠትን ይዘነጋሉ። ይህ ዝንጋዔ የሚመጣው ልጆቻቸውን በአነዚህ ልምምዶች ውስጥ ይከታተሉ ዘንድ ዝግጁ ሆነው ለመገኘት ጥረት ባለማድረጋቸውና በስንፍናቸው ነው። ለአነርሱ ጥረት የሚያደርጉላቸውም አነርሱን በማበረታታትና ለአነርሱ በመጸለይ ነው። አንዳንድ ካህናት ለዚህ ስንፍናቸው የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች የተቀበሏቸው ንስሓዎች ያላቸው የመንፈሳዊነት ደረጃ ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሣ መንፈሳዊ ልምምዶች አያስፈልጓቸውም ይላሉ ወይም ደግሞ አነርሱ (ካህናት) አነዚህን መንፈሳዊ ልምምዶች ለመከታተል ጊዜ የለንም የሚሉ ናቸው።

ይሁን አንጂ አነዚህ ምክንያቶች የአንድን ሰው መንፈሳዊ ዕድገት ይገታሉ፤ንስሓ መስጠትም ቃላት የመናገርና ስርዮት የማዝበብ ተደጋጋሚ ሥራ ሆኖ ይቀራል።

አንዳንድ በመንፈሳዊነት የሚቃጠሉ ወይም በመንፈሳዊ ዕድገታቸው ደስተኞች የሆኑ ተነሳሒዎች አነርሱን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ውስጥ ሊደግፏቸው ስለሚችሉት ስለ አነዚህ ልምምዶች እጦት ሲሉ ስሞታ ያቀርባሉ። ከጊዜ ወደ ጊዜም የንስሓ አባቶቻቸው አነዚህን ልምምዶች አንዲሰጧቸው ይጠይቃሉ። ይህ ሁኔታ ግን የተሰመደ ነገር አይደለም። አንዳንዶቹ ተነሳሒያን ደግሞ አንደ ፍላጎቶቻቸው መጠን የራሳቸውን ልምምዶች ሰራሳቸው ያገዛሉ። ይሁን አንጂ ይህ ትክክለኛ አርምጃ አይደለም፤ማንኛውም መንፈሳዊ ልምምድ ያለ ንስሓ አባት ፈቃድ ሊከናወን አይችልምና።

የዚህ ምክንያቱ ዲያብሎስ በመካከል ጣልቃ መግባቱ ሳይሆን ይልቁንም አርሱ የአነዚያን ሰዎች የዋህነት ወይም ልምድ የለሽነት በመጠቀም አብዝተው አንዲታገሉት ማድረጉ ነው። በዚህም በትዕቢት ኃጢአት ወይም በሉሎች የአርሱ ክፉ ዕቅዶች ውስጥ አንዲወድቁ ያደርጋቸዋል። ብልኀ ንጉሥ ሰሎሞን ሲያስጠነቅቀን አንዲህ ብሎናል። «. . . አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሣው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት።» መክ 4:10። አባ አንጦንስም «አንዲነግርህ አባትህን ጠይቅ፤ስለ አንተ መናገርንም ለታላላቆችህ ተውላቸው።» በማለት ተናግሯል።

ያለ ምንም ምክርና መመሪያ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ውስጥ በራሳቸው የሚንዙ ሰዎች ጠቢቡ ሰሎሞን አንደ ተናገረ በሰይጣን ወጥመድ ላይ ይወድቃሉ። «መልካም ምክር ከሌለ ዘንድ ሕዝብ ይወድቃል፤በመካሮች ብዛት ግን ደኅንነት ይሆናል።» ምሳ 11:14። አንድ ሰው በኃጢአት ከወደቀም አንዲህ ይላል። «ትላለህም። አንዴት ትምህርትን ጠላሁ፤ልቤም ዘለፋን ናቀ! የአስተማሪዎቼንም ቃል አልሰማሁም፤ጆሮዎቼንም ወደ አስተማሪዎቼ አላዘነበልሁም።» ምሳ 5:12-13።

ካህናት በንስሓ ውስጥ ለሚገኙ ልጆቻቸው አንዳንድ መንፈሳዊ ልምምዶች መስጠትና የአነዚህን ልምምዶች ዕድገት መከታተል ግዴታቸው ነው። ንስሓ የሚገቡትም መንፈሳዊ ዕድገታቸውን መውደድ አለባቸው። ስለሆነም አነዚህን ልምምዶች ከልባቸው ሆናቸው ለማግኘት ሽቱ፤በዚህ ጊዜ በጸጋና በሞገስ በአግዚአብሔርና በሰዎች ፊት ማደግ ትችላላችሁና።

ጥቂት የመንፈሳዊ ልምምድ ምሳሌዎች።

ከግል ድክማቸው በመነሣት ለምሳሌ፦ አንደ ውሽት፣ መሐላ፣ ሐሜት . . . ወዘተ ያሉ ኃጢአቶችን ለሚፈጽሙ ሰውየው አነዚህን ኃጢአቶች በፈጸመ ቁጥር ለአያንዳንዱ ኃጢአት አምስት-አምስት ስግደቶች የመስገድ ንስሓ ሊሰጠው ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ መንፈሳዊ ልምምዶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ሊወሰዱ ይቻላል፤በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አጅግ ብዛት ያላቸው ምሳሌዎች ይገኛሉ። ለምሳሌ፦ በአሥሮቱ ትእዛዛት (ዘጸ 20) ውስጥ ብዙ ምሳሌዎች አሉ. . .

- የጌታን ቀን (የሰንበትን ቀን) አስታውስ፤ቅዱስም አድርገህ ጠብቀው።
- አባትና እናትህን (በተሰይም በእርጅና ዘመናቸው) አክብራቸው።
- አትግደል።

❖ አታመንዝር (በአሳብም ሆነ በድርጊት)
❖ አትስረቅ (መማለጃም አትቀበል)
❖ የሐሰት ምስክር አትቀበል (ውሸት ወይም ማጭበርበር)
❖ የአንተ የሆነውንም አትመኝ።

ሌላው በእኛ መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ ተግባራዊ መሆን ያለበት ታላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ላይ የተናገራቸው ቃላት ናቸው. . .

❖ መንፈሳዊ ድህነት ወይም ትሕትና።

❖ በሰዎች ሁሉ የሚሆን የዋህነት።

❖ ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ ምሕረት ማድረግ።

❖ ሰላምን ለማውረድ እንጂ ችግርን ለመፍጠር አለመታገል።

❖ መከራን፣ ስደትንና የሐሰት ምስክሮችን በደስታ መቀበል፣ ስለ እግዚአብሔር ስትል የምትቀበለው ነውና።

❖ ለጸሎት እንቅፋት ስለሚሆን ጠላትነትን በሰዎች ዘንድ አታነሣሣ።

❖ በማንኛውም ነገር ውስጥ ሕጋዊ ሁን።

❖ ያለህበት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ዓይነት ነገር ቢጠይቅህ ስጠው፣ ጥቂትም ቢሆን እንኳ።

❖ ጠላቶችህን ውደድ፣ ለጠላቶችህ ጸልይ፣ ጠላቶችህ እንዲባረኩ ጠይቅ፣ በችግር ጊዜም ጠላቶችህን እርዳ።

❖ በምሥጢር ስጥ ጸልይም፣ ጾምህንም እንደሚገባህ ጹም።

❖ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሚታመኑት እንደ ምድር አበቦችና እንደ ሰማይ ወፎች በእግዚአብሔር ታመን። መታመን ማለት በእግዚአብሔር መቆም እንጂ በራ መቆም ማለት አይደለም።

❖ በእርግማን ውስጥ እንዳትወድቅ ይረዳሃልና እንደበትህን ለመጠበቅ ባለህ ኃይል ሁሉ ታገል። የአንደበት ኃጢአት አደገኛ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ቁጣና ፍርድ ሊያስከትልብህ ይችላል።

❖ በማንኛውም ጊዜ መጸለይን ተለማመድ። ለምን ይሉኛል፣ ፈልግ ታገኛለህ፣ አንኳኳ ይከፈትልሃል፣ በጸሎት ሕይወት ውስጥ መቆየት ጠቃሚ ነገር ነውና።

❖ ፈውስ እንዲሆንህ በአንተ ላይ ሊደረግ የሚትወደውን ነገር በሌሎች ሰዎች ላይ አታድርግ የሚለውን ወርቃማ ሕግ ተከተል።

መምህራችን ቅዱስ ጳውሎስ ሶቶሮንቶስ ሰዎች በላከው ሁለተኛ መልእክቱ ምዕራፍ 13 ውስጥ የጠቀሰልንን ሁሉንም የፍቅር ዓይነቶች ተግባራዊ እናድርግ. . .

❖ «ፍቅር ሁሉን ይታገሣል፤» ሰዎችን ሁሉ በትዕግሥት ቻል።

❖ «ፍቅር አያቀናናም፤» በሌሎች ላይ ላለመቅናት እንለማመድ።

❖ «ፍቅር ራሱን አያስመካም፤» አንድ ሰው ሌሎች ሰዎች ሊያገኙት በሚችሉት ነገር ላይ ሊመክባቸው አይገባም።

❖ «ፍቅር አያስታብይም፤» እግዚአብሔር አምላክ ትዕቢተኞችን ስለሚቃወምና ለትሑታን ጸጋን ስለሚሰጥ ትዕቢት አደገኛ ማነቆ ነው።

❖ «ፍቅር ክፉ ነገርን አያሳስብም፤» ሰውን የሚወድ ሰው በክፋት አይናገርም በትሕትና እንጂ፣ ልክ ጣፋጭ ውኃ እንደሚያመነጭ ንጹህ ምንጭ።

❖ «ፍቅር ብቻዬን ይድላኝ አያለኝም፤» ሰዎችን የሚወድ ሰው ራሱን ወዳድ አይደለም፣ ሌሎችን ይወዳል እንጂ። እርሱ ለእነርሱ መሥዋዕት ይሆናል፣ ያለውን ሊሰጣቸውም ዝግጁ ነው። ራስ ወዳድነት የብዙ ችግሮች ምክንያት ስለሆነ እርሱን ከእናንተ አርቁ።

❖ «ፍቅር አያበሳጭም፤» ብስጭት (ቁጣ) የእግዚአብሔርን ጽድቅ ስለማይሠራ አትበሳጩ።

❖ «ፍቅር ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤» ሌሎች ሰዎችን የሚጎዳ ውድቀትን አይመኝም። ሕሊናቸው ንጹህ ለሆነ ሰዎች ሁሉም

ነገር ንጹህ ነው። ንጹሐን ሰዎች ከራሳቸው ይልቅ ሌሎች ሰዎችን ያስቀድማሉ።

❖ «ፍቅር ከእውነት ጋር ደስ ይሰኛል፤» ፍቅር ያለው ሰው በሌሎች ሰዎች ስኬት ወይም ሀብት ወይም ደስታ ወይም ልጆች ወይም በሌሎች እግዚአብሔር በሚሰጣቸው በረከቶች ይደሰታል። «ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፤ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ።» ሮሜ 11፡15።

❖ «ፍቅር ሁሉን ይታገሣል፤» ታጋሽ ሰው ለመሆን ተለማመድ። እጅግ ከባድ የተባሉ ስሕተቶች ላይ ብትወድቅም እንኳ ቁጣ ፈጥና አትቀጣጠል፤ የሰዎችን ፍቅርና ክብር ታጣለህና። ለመታገሥ የሚቻለው ለማፍቀር ሲቻል ነው። ስለዚህ ሁሉንም ነገሮች፣ ሁሉንም ሁኔታዎችና ሁሉንም ሰዎች ያለ ምንም ማማረር ታገሡ።

❖ «ፍቅር ሁሉን ያምናል፤» ፍቅር ቀላል ነው እንጂ አታላይ አይደለም። ፍቅር ጠቢብና አርቆ አሳቢ ነው።

❖ «ፍቅር ሁሉንም ያምናል፤» ተስፋ የሚያደርገው ለሌሎች ሰዎች መልካምነትና ደስታ ነው።

❖ «ፍቅር በሁሉ ይጸናል፤» ከእርሱ ጋር የሕይወት አክሊል ስለሚመጣ ትዕግሥትን ተለማመድ። ሌሎች ሰዎችን መቻልም ተለማመድ፤ እነዚህ ሰዎች ችግር ፈጣሪዎች ቢሆኑም እንኳ። ይህን ስታደርግም ትዕግሥትህ መልካም ነገር እንደሚያስገኝልህ በማወቅ ይሁን።

❖ «ፍቅር ሰዘሳለም አይወድቅም፤» የተለያዩ ፈተናዎችና መከራዎች ቢገጥሙም እውነተኛ ፍቅር ፈጽሞ አይወድቅም፤ በማንኛውም ፈተና ፊት በጽናት ይቆማል እንጂ። «ፍቅር እንደ ሞት የበረታች ናትና፤. . . ብዙ ውኃ ፍቅርን ያጠፋት ዘንድ አይችልም፤ ፈሳሾችም አያሰጥሟትም፤ ሰው የቤቱን ሀብት ሁሉ ስለ ፍቅር ቢሰጥ ፈጽሞ ይንቁታል።» ምሳ 8፡6-7።

በትሕትና ውስጥ ያለ መንፈሳዊ ልምምድ።

❖ ለሰዎችን ለቁጣ አታነሣሣ።

❖ በሁሉም ነገሮች ውስጥ ዝምተኛና ሰላማዊ ሰው ሁን።

❖ ሰዎች እነማን ሆነም እነማን ዘመዶችህም ወይም ሌሎች ቢሆኑ በሌሎች ሰዎች ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ አትግባ። ሁሉንም ውደድ በሁሉም ሰዎች ጉዳይም አትግባ።

❖ ጥሩ አድማጭ መሆንን ተለማመድ፤ ሁሉንም ሰው በትዕግሥት አድምጥ። ይህን የምታደርገውም ሰዎቹ ከእንተ በዕድሜም ሆነ በሥልጣን የማይበልጡ ቢሆኑም እንኳ ነው።

❖ ለእግዚአብሔር በትሕትና ካልሆነ በስተቀር ስምታህን ለማንም አትናገር።

❖ ከሰዎች ሁሉ ጋር ደስተኛ ለመሆን ተለማመድ፤ ለሰዎቹ ጨካኞችና ክፉዎች ቢሆኑም እንኳ።

❖ አያንዳንዱ ክርስቲያን ታዛዥ፣ ብልህና ከሁሉም ሰው ጋር የሚስማማ መሆን አለበት።

በጸሎት ውስጥ ያለ መንፈሳዊ ልምምድ።

❖ ስትጸልይ በማክበር ውስጥ መሆንን ተለማመድ፤ የልብህና የሥጋ ማክበር ይኑርህ፤ የሰሜቶች ሰላምም እንዲሁ።

❖ ቀስ በቀስ መዝሙራትን፣ ወንጌላትንና የዘወትር ጸሎቶችን አጥና።

❖ በሁሉም ጊዜ ውስጥ ጸሎት መጸለይን ተለማመድ፤- ስትሠራ፣ ስትራመድና ከሌሎች ሰዎች ጋር ስትቀመጥ እንኳ።

❖ ዘወትር ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ «ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ።» እያልህ መጸለይን ተለማመድ።

❖ በማንኛውም ጊዜ ለሌሎች ሰዎች መጸለይን ተለማመድ፤ ለሁሉም ሰዎችም ፍቅር አሳይ።

❖ ለጠላቶችህና አንተን ለሚሰድቡህ ሰዎች እንድትጸልይ የሚያዝህን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ተለማመድና ተግባራዊ አድርግ።

በጸም ውስጥ ያለ መንፈሳዊ ልምምድ።

❖ በሚቻልህ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አጽዋማትን ለመጾም ትጋ።

- በጸም ወቅት ከምግብ ተከልክሎ የመቆየት ጊዜ መኖር አስፈላጊ ነገር ነው። ይህ የቆይታ ጊዜ ግን ከሰው ወደ ሰው ሊለያይ ይችላል።
- በምትመገባቸው የጸም የምግብ ዓይነቶች ላይ ውሳኔ ሁን።

በንባብ ውስጥ ያለ መንፈሳዊ ልምምድ።

- በየዕለቱ የሚደረግ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እጅግ አስፈላጊ ነው።
- በየዕለቱ ቢያንስ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ አንብብ።
- የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ በየዕለቱ የሚደረግ ጉዳይ እንጂ እንዲሁ በልማድ የሚደረግ መሆን የለበትም።
- ነጥቦችን ለማስፈር ትችል ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ በምታነብበት ጊዜ ሁሉ ብዕርና ማስታወሻ ደብተር ከአጠገብህ አይለይ።
- እጅግ በጣም ውጤታማ ናቸው የምትላቸውን ጥቅሶች አትልማቸው ወይም ከሥራቸው አስምርባቸው። ከዚያም ማስታወሻህን በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጻፋቸው አላቦዥህንም እንጂሁ።
- በዚያን ዕለት ልታጠናቸው የምትፈልጋቸውን ጥቅሶች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጻፋቸውና ቀኑን ሙሉ እነርሱን ስትደግም ዋል። የምትችል ከሆነ በምታነበው ጥቅስ ወይም ምዕራፍ ውስጥ ውጤታማ ወይም ጠቃሚ ነው ያልኸውን አጭር ተመስጦ ጻፈው።
- ከምዕራፉ ውስጥ ተግባራዊ የሆኑ ጥቅሶችን መዝግባቸውና ልዩ ምልክት አድርግባቸው። እነዚህ ጥቅሶች አንተን እንደሚጠቅሙ የሚታወቁህና በተግባር የምትፈጽማቸው ናቸው። ለምሳሌ፦ «ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ»፤ «እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ»፤ «ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን»፤ «ለማንም ስለ ክፋ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ»፤ «ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው አርዱ»፤ «መርቁ እንጂ አትርገሙ»፤ «ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፤ ከማያለቅሱም ጋር አልቅሱ።»

እነዚህን መንፈሳዊ ልምምዶች ተግባራዊ ለማድረግ ምክሩ፤ በእነርሱ ለመኖርም ተማሩ።

ለመንፈሳዊ ልምምዶች ስኬታማነት የሚጠቅሙ ሁኔታዎች።

የመንፈሳዊ ልምምዶችን ስኬታማነት ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ ጥቂት ሁኔታዎች። እነዚህ ነጥቦች የሚጠቅሙት ተግባራዊ ለሚያደርጓቸው ነው።

- **የልምምዱ ግልጽነት፦** ልምምድ ሊደረግባቸው ግድ ነው ተብሎ ንስሐ ለሚገባው ሰው የሚሰጡት መመሪያዎች ግልጽ መሆን አለባቸው እንጂ ጭፍን ወይም የተንዛዙ መሆን የለባቸውም።
- **የልምምዱ ዝርዝሮች፦** ዝርዝር ነጥቦች በአጽንዖት መገለጻቸው ግድ ነው፤ ለምሳሌ፦ ከምግብ መከልከል፣ በሌሎች ሰዎች ላይ አለመፍረድ፣ አለመስረቅ. . . ወዘተ።
- **የልምምዱ ወቅት፦** ለምሳሌ በአንድ ቀን በሚደረግ ልዩ የቤተሰብ ስብሰባ ላይ አርምሞን መለማመድ አንችልም። ልክ እንደዚሁ በሠርግ በዓል ላይ እና መጸም አንችልም. . ወዘተ።
- **በልምምድ ውስጥ የሚደረግ አዝጋሚ ዕድገት፦** ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ድንገት እንዳይወድቁ በዝግታ ማደጋቸው ጠቃሚ ነገር ነው።
- **የልምምዱ ጊዜ፦** እነዚህ መንፈሳዊ ልምምዶች መልካም ፍሬዎችን እስከሚያፈሩና መልካም ጠባይ እስከሚያስከትሉ ድረስ መድረጥ የለባቸውም። ቅዱስ ኤፍሬም ሶሪያዊ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «ረኀቡም ጊዜ የማይወስድ ማንኛውም ልምምድ ፍሬዎችን ሲያፈራ አይችልም።» ከመንፈሳውያን አባቶች አንዱ በዓመት ውስጥ አንድን መንፈሳዊ ልምምድ ማድረግ ከቻሉ መልካም ነው። ቅዱስ አርሳኒዎስ አርምሞን በሕይወቱ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ሦስት ዓመት ፈጅቶበታል።
- **የልምምዱ ስኬት፦** በመጀመሪያ ለውየው ስለ ስኬቱ አስፈላጊነትና ጥቅም ማመን አለበት። የልምምዱ ስኬት ንስሐ የገባውን ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበውን የማያቋርጥ ጸሎት ይሻል። ይህ የሚያስፈልገውም እግዚአብሔር ሰውየውን በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያድግና እንዲበረታ ከማድረጉም በላይ በሚፈጽማቸው ልምምዶች ውስጥ መልካም ፍሬዎችን እንዲያፈራ ወደዚያው ይመራዋል። ከዚህ በተጨማሪ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ዘላቂና ጽኑ ሰው ይሆን ዘንድ መንፈሳዊ ጸሎቶችና የንስሐ አባቱ እርዳታ ያስፈልጉታል። በተለይም ይህ በንስሐ ሕይወት ውስጥ ጀማሪ ሰሆኑ ሰዎች በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። እነዚህ ሰዎች በንስሐ አባታቸው አማካይነት

የሚሰጧቸውን መመሪያዎች በማስታወሻ ደብተሮቻቸው ላይ በትክክል ማስፈራቸውና እነዚህን መመሪያዎች በትጋትና በጥንቃቄ ተግባራዊ ማድረጋቸው ለእነርሱ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። የልምምዱ ስኬት የመንፈሳዊ ማስታወሻ ደብተር አጠቃቀም ይፈልጋል፤ እነዚህ ማስታወሻ ደብተሮች ንስሐ የሚገቡትን እነዚህን ሰዎች በመንፈሳዊ አቋምና በጸጋ እንዲያድጉ ይረዷቸዋልና።

አሜን።

«እናንተ ደክሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፦ ወደ እኔ ኑ፦ እኔም አሳርፋችኋለሁ።» ማቴ 11:28።

በጎውን ሁሉ ለእኛ ያደረገና የሚያደርግ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን።

ተመስጦ

«አቤቱ በቍጣህ አትቅሠፈኝ፤. . .» መዝ 6

አዘጋጅ፦ የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን 117ኛ ፓትርያርክ ቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ግልሳዊ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ. . .

በስመ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ፣አሜን።

ይህ መጽሐፍ በመዝሙራት ውስጥ ከሚገኙት ተመስጦዎች መካከል አንዱ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹም ታትመዋል።

ይህ መዝሙር በነጋህ ጸሎት ውስጥ ከሚጸሰዩት መዝሙሮች መካከል አንዱ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በምሽት ጸሎትና በሌሊት ጸሎት ውስጥ ይጸለያል።

ይህ መዝሙር እጅግ ጠቃሚ ከሆኑት ከንስሓ መዝሙራት መካከል አንዱ ነው።

ይህ ጸሎት በዓይነቱ እንባንና ንስሓን በእግዚአብሔር ከመደሰተልና የእርሱን መልስ ከማወቅ ጋር የተቀናጀ ጸሎት ነው። በመሆኑም የሚጠናቀቀው በደስታና ሐሴት በማድረግ ነው።

ይህን መዝሙር እኛ ሁላችን ልናጠናውና ልንጸልየው እንችላለን።

በነጋህ ጸሎት ውስጥ ከሚገኙት ጥቂት መዝሙራት መካከል በሌላው የተመስጦ መጽሐፍ እስክምንገናኝ ድረስ ሰላም ሁኑ።

አቡነ ሺኖዳ ግልሳዊ

መግቢያ

መዝሙር ስድስት ከነጋህ መዝሙራት መካከል አንዱ ነው።

እንደ መዝሙር አምላ የንስሓ መዝሙራት ከሆኑት መካከልም አንዱ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በመከራ ውስጥ ካለ ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚጮኽ መዝሙር ነው፤ልክ እንደ መዝ 12:1 «አቤቱ፡- እስከ መቼ ፈጽመህ ትረሳኛለህ? እስከ መቼስ ፊትህን ከእኔ ትሰውራለህ?» እና እንደ መዝ 3:1 «አቤቱ፡- የሚያስጨንቁኝ ምንኛ በዙ!»

ይህ መዝሙር በጠላቶቹ አማካይነት መከራ ለሚደርስበት ሰው ተገቢ መዝሙር ነው፤ክኃጢአትና ከሰይጣን የሚደርስበትን ልፋት ለመቋቋም በመንፈሳዊ ድካም ውስጥ ለሚገኝ ሰውም እንዲሁ።

መዝሙሩ የእግዚአብሔርን ምሕረት ለመጠየቅ በብዙ ሰዎች ልብ ውስጥ የሚያልፈውን ስሜት የሚገልጽ መዝሙር ነው።

ቤተ ክርስቲያን ይህን መዝሙር በነጋህ ጸሎት፣ ለመነኮሳት በሚደረግ ጸሎትና በአኩሶ ሌሊት ጸሎት ውስጥ በመደጋገም ለመዝሙሩ ክፍተኛ ትኩረት ሰጥታዋለች።

መዝሙሩ ከሚያስጨንቁት ጠላቶቹ የሚደርስበትን ድካም በመግለጽ ቢጀምርም የሚጠናቀቀው በደስታ ነው። አንድ ሰው ይህን ጸሎት በሚጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ ለደስታና ለውዳሴ የሚጠራ ጸሎቱን እንደ ተቀበለው ይታወቀዋል።

መዝሙሩ ተመሳሳይ መንፈስና ተመሳሳይ መልስ ስላለው በዚህ ከመዝሙር ሦስት እና ከመዝሙር አሥራ ሁለት ጋር ይመሳሰላል።

እኔ የዚህን መዝሙር ተመስጦዎች ኢ.አ.አ. በ1968 ዓ.ም. ግብፂያ ላይ በየሳምንቱ ዓርብ ማታ በምናደርገው ስብሰባ ላይ አቅርቤው ነበር። ውድ አንባብያን፡- እነዚህ ተመስጦዎች እግዚአብሔር አምላክ ፈቅዶ ከሃያ ሰባት ዓመታት ታትመው እስሚወጡና በእጃችሁ እስክሚገቡ ድረስ በድምፅ መቅጃ ክር ላይ ተቀድተው ነበር የቆዩት።

በዚያን ዘመን ይህ መዝሙር ለተመስጦዎቻችን ምክንያት ከሆኑን መዝሙራት መካከል አንዱ ነበር። አሁን ያላተምንላችሁ ከፊሉን ነው፤እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ቀሪው ወደ እናንተ በመምጣት ላይ መሆኑን ተስፋ አደርጋለሁ።

አቡነ ሺኖዳ ግልሳዊ
መጋቢት 1995 ዓ.ም.

ማውጫ

- አቤቱ በቍጣህ አትቅሠፈኝ 70
- በመዓትህም አትገሥጸኝ 73
- ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ 73
- የኢዮብ ምላሴነት 87
- የዳዊት ድካምና ፀፀት 88
- ነፍሴም እጅግ ታወከች 95
- አቤቱ፡- እስከ መቼ ድረስ ነው? 96
- አቤቱ፡- ተመለስ ነፍሴንም አድናት 100
- ስለ ቸርነትህም አድነኝ 101
- በሞት የሚያስብህ የለምና+ 103
- በጭንቀቴ ደከሜያለሁ፤ 106
- የዳዊት ልትሶ 107
- ዳዊት አብዝቶ አልቅሷል 110
- መልሱ 112
- ጠላቶቼ ሁሉ ይፈሩ. 114
- ሃሌሉያ 115

አቤቱ በቍጣህ አትቅሠፈኝ፣. . .

መዝሙር 6

አቤቱ በቍጣህ አትቅሠፈኝ፤
በመዓትህም አትገሥጸኝ።
ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ፤
አጥንቶቼም ታውከዋልና ፈውሰኝ።
ነፍሴም እጅግ ታወከች፤
አንተም አቤቱ፡- እስከ መቼ ድረስ ነው?
አቤቱ+ ተመለስ ነፍሴንም አድናት+
ስለ ቸርነትህም አድነኝ።
በሞት የሚያስብህ የለምና+
በሲኦልም የሚያመሰግንህ ማን ነው?
በጭንቀቴ ደክሜያለሁ፤
ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ+
በዕንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ።
ዓይኔ ከቍጡ ዕንባ የተነሣ ታወከች፤
ከጠላቶቼ ሁሉ የተነሣ አረጀሁ።
ዓመፃን የምታደርጉ ሁሉ ከእኔ ራቁ+
እግዚአብሔር የልቅሶዬን ቃል ሰምቶአልና።
እግዚአብሔር ልመናዬን ሰማኝ፤
እግዚአብሔር ጸሎቴን ተቀበለ።
ጠላቶቼ ሁሉ ይፈሩ እጅግም ይንቅጥጥ፤
ወደ ኋላቸው ይመለሱ፤በፍጥነትም ይፈሩ። ሃሌሉያ።

አቤቱ በቍጣህ አትቅሠፈኝ፤
በቍጣህ አትቅሠፈኝ፤

ይህ መዝሙር በሚገባ ከሚታወቁት የንስሓ መዝሙራት መካከል አንዱ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ለዚህ መዝሙር የተሰየ ትኩረት ስለምትሰጠው በነጋህ ጸሎቶቿ፣ በኩኩሰ ሌሊት ጸሎቶቿና መነኮሳት በሚጸልዩት የምንኩስና ጸሎት ውስጥ አካታዋለች። በዚህ መዝሙር መጀመሪያ ላይ ዳዊት እንዲህ ነው ያለው፡-

«አቤቱ በቍጣህ አትቅሠፈኝ፤
በመዓትህም አትገሥጸኝ።»

ዳዊት እዚህ ላይ ኃጢአቱን ተናዝሏል፣ቁጣና መቅሠፍት የሚገባውም ሰው መሆኑንም ተናዝዟል። ይሁን እንጂ ይህ በፍጥነት እንዳይከናወንበት ጠይቋል።

እርሱ ለእግዚአብሔር «አቤቱ በቀኙጣህ አትቅሠፈኝ፤» ነው ያለው። እርሱ ይህን ያለው ደካማ ሰው ስለሆነና የእግዚአብሔርን ቀኙጣ ለመሸከም ስለማይችል ነው . . . ጌታዬ ሆይ፦ በቀኙጣህ የምትገሥጸኝ ከሆነ ልታጠፋኝም ሆነ ሳትጠብቀኝ ትችላለህና የሚሰው። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አገላለጽ በነቢዩ ኤርምያስ ተነግሯል፦ «አቤቱ ቅጣኝ፤ነገር ግን እንዳታዋርደኝ በመጠን ይሁን እንጂ በቀኙጣ አይሁን።» ኤር 10:24።

እርሱ ከቀኙጣ ለማምለጥ ምንም ዓይነት ምክንያት አላቀረበም። ይልቁንም «አቤቱ በቀኙጣ አትቅሠፈኝ፤» ነው ያለው። ምክንያቱም «በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው።» ዕብ 10:31።

እግዚአብሔር በሕዝቡ ኃጢአት እጅግ በተቆጣ ጊዜ ዓለምን በውኃ አስጥሟት ነበር። ከዚህ በኋላ በርኅራኄ ተመልሶ ለሕዝቡ ሲያዝንላቸው በምድር ላይ ያለውን ሥጋ ለባሽ ሁሉ እንደማያጠፋ ምልክት ሰጥቶአቸዋል፤ዘፍ 9:15። እግዚአብሔር በፈርዖን ላይ በተቆጣ ጊዜ እርሱንና ሠራዊቱን በቀይ ባሕር ውስጥ አስጥሞአቸዋል፤ዘጸ 14:28። እግዚአብሔር አምላክ በቆራ፣ በዳታንና በአቤሮን ላይ ቁጣው በነደደች ጊዜ ምድር ተከፍታ እንድትውጣቸው አድርጓል፤ዘኁ 16:32።

† † †

እኛም በየዕለቱ ኃጢአት እንሠራለን፤ምናልባትም የእኛ ኃጢአት የእነዚህን ሰዎች ኃጢአት ሊመስል ይችላል።

በዚህ ጊዜም «አቤቱ በቀኙጣህ አትቅሠፈኝ፤» እያልን ወደ እርሱ እንጮሃለን።

ጌታ ሆይ፦ አንተ በቀኙጣህ ብትሩፈደን ማንም ሊድን አይችልም። በዐቢይ ጾም ውስጥ ወደ እግዚአብሔር ስንጸልይ እንዲህ እያልን እንጸልያለን፦ «አቤቱ ጌታ ሆይ፦ በእውነቱ አንተ ብትፋረደን ምንም ዓይነት በቂ ምክንያት ልናገኝ አንችልም።» ስለሆነም ነቢዩ ዳዊት እግዚአብሔርን «አቤቱ በቀኙጣህ አትቅሠፈኝ፤» አለው።

ቁጣ የራሱ በረከት ስላለው ከእርሱ መጠቀም እንችላለን።

አቤቱ ጌታ ሆይ፦ ይህ ይሁን እንጂ አንተ በቀኙጣህ አትቅሠፍ፣ በመዓትህም አትገሥጸኝ።

† † †

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስን የገሠጸበት አስደናቂ ተግሣጽም አለ። እርሱ ጌታውን በመካድ ሲያልና ሲገዝት ነበር «ሰውየውን አላውቀውም. . .» (ማቴ 26:72) በማለትም ተናግሮ ነበር። ይሁን እንጂ ጌታ እርሱን የገሠጸው ለስለስ አድርጎና በእርጋታ ነበር እንጂ በቀኙጣና በሚነድ ቅሬታ አልነበረም። በመሆኑም ከዚያ በኋላ እንዲህ ብሎታል፦ «. . . የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፦ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? . . . ግልገሎቼን አሰማራ፤ . . . ጠቦቶቼን ጠብቅ፤ . . በጎቼን አሰማራ።» ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ጥያቄ ለጴጥሮስ ያቀረበለት ሦስት ጊዜ ነበር፤ዮሐ 21፡15-17። አምላካችን ጴጥሮስን ስለ ክህደቱና ስለ ኃጢአቱ በእደጣይ አልወቀሰውም . . . አልጎዳውም አላሳፈረውምም።

እግዚአብሔር የሰዎችን ስሜት አያቆስልም፤ልቦቻቸውንም አይጎዳም።

በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር እርሱ የታመመውን ሰው ባለው እንክብካቤ ሁሉ እንደሚያድን ሀኪም ነው እንጂ በቅሬታ ወይም በማመናጨቅ እንደሚያክም ሀኪም አይደለም።

† † †

እግዚአብሔር ሰዎችን ስለ ብዙ ኃጢአቶቻቸው አይቀሥፍም።

ለምሳሌ፦ የአባቶች ሁሉ አባት የሆነው አብርሃም ሚስቱ ሣራን እንቱ ናት ስላለ የጌራራ ንጉሥ የሆነው አቢሜሌክ ለራሱ ወስዷት ነበር፤ዘፍ 20:2። እርሱ ከእግዚአብሔር የተቀበለው መቅሠፍት ምንድር ነው? እግዚአብሔር የተቆጣው አቢሜሌክን እንጂ አብርሃምን አልነበረም። በእርግጥ ግን አብርሃም ከአቢሜሌክ እንዲህ የሚል ቅጣን ተቀብሏል፦ «. . . ይህ ያደረግህብን ምንድር ነው? ምንስ ክፉ ሠራሁብህ? በእኔና በመንግሥቴ ላይ ትልቅ ኃጢአት አውርደሃልና፤ የማይገባ ሥራ በእኔ ሠራህብኝ።» ዘፍ 20:9። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እርሱን ምንም አላሰውም፤የተቀበለው በቂው ነበርና።

ቁጣን የሚያበዛው ወይም የሚጨምረው የሰው ልጅ ብቻ ነው።

አንድ ጠቢብ ሰው «ቁጣን የሚጨምር ሰው ራሱን ያጠፋል።» በማለት ተናግሯል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ባልንጀሮቹን ያጣል፤ በተግባራዊው ሕይወት ውስጥ የሚሆነው ይህ ነውና።

ጌታዬ ሆይ፦ አንተ ጴጥሮስን እንደ ገሠጽኸው እኔን ገሥጸኝ እንጂ በቁጣህ አትገሥጸኝ። ጉዳዩ ቁጣ የሚያስፈልገው ቢሆንም እንኳ ቁጣህ እስከ ዘላለም ድረስ የሚዘልቅ አይሁን። እኛ ወደ እግዚአብሔር ስንጸልይ «ቁጣህን ከእኛ ዘንድ አርቅልን።» ብለን እንጸልያለን። ዳዊት ጸሎቱን በመከተል . . .

«በመዓትህም አትገሥጸኝ።» ብሏል።

አቤቱ ጌታዬ ሆይ አንተ ገሥጸኝ . . . አባት ልጁን ይገሥጽ የለምን?! ተግሣጽን የማይቀበሉ ዲቃሎች እንጂ ልጆች አይደሉም! ዕብ 12:8።

ተግሣጽ ለእኔ ጥቅም ስለሚያስገኝና ለእኔ ስለሚጠቅመኝ ገሥጸኝ። የሠራሁት ሥራ በትክክል ተግሣጽና ከዚያም በላይ የሆነ ነገር ስለሚገባው ገሥጸኝ። ይሁን እንጂ በሚነድ መዓትህ አትገሥጸኝ። አንተ ልቀበለው በምችለው መጠን ገሥጸኝ። ጌታ ሆይ፦ የእንተን ተግሣጽ በምስጋና እቀበላለሁ።

«ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ፤»

«ማረኝ/ማረን» የሚለው ቃል በቤተ ክርስቲያንና በጸሎቶቿ ውስጥ ተደጋግሞ የሚገለጽ ቃል ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ «ማረኝ» የሚለው ቃል የማይገለጽበት ምንም ዓይነት ጸሎት የለም። «ኪራላይሶን» ብለን ስንጸልይም ብዙ ጊዜ እንደጋገመዋለን።

አቤቱ ጌታ ሆይ፦ እኔ ደካማ ነኝና ምሕረትህ በእኔ ላይ ትሁን . . . የእንተ ልብ ሰፊ ስለሆነ ዓይነቱ ምንም ይሁን ምን ማንኛውንም ኃጢአት መታገሥ ይችላል።

† † †

እግዚአብሔር ሆይ . . . አንተ ማረኝ! አንተ ካልማርኸኝ በስተቀር ማንም ሊምረኝ አይችልምና።

የእንተ ልብ በእኔ ላይ ከተዘጋ ሌላ ልብ ሳገኝ አልችልም። የእንተ ምሕረት ኃጢአቶቼ እንዳይገለጡ የምደበቅበት መሸሸጊያዬ ነው። የእንተ ምሕረት ነጻ የመውጣቱ መሠረት ነው . . . የእንተ ምሕረት የድኅነት መሠረት ነው።

† † †

እግዚአብሔር ሆይ፦ ምሕረትህ በእኔ ላይ ትሁን ማለት ኃጢአቶቼ በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ላይ ይሁኑ ማለት ነው።

ለእኔ ታላቅ መሥዋዕት የሆነ ይህ መድኃኒቴ እነዚህ ኃጢአቶቼን በክበረ ደሙ ያጥባቸዋልና።

ዳዊት ከድኅነት አስቀድሞ «አቤቱ ማረኝ» ካለ ይህ ድኅነት እንደሚመጣ ታላቅ ተስፋ ነበረው ማለት ነው። ድኅነት ከተፈጸመ በኋላ ላለን ለእኛ ደግሞ ይህ ተስፋ እጅግ ታላቅ ተስፋ አለው ማለት ነው። ስለሆነም ጌታዬ ሆይ፦ ስለ እነርሱ ስትል ደምህን ካፈሰስህላቸው ሰዎች መካከል እንደ አንዱ አድርገህ ቁጠረኝ።

አቤቱ ጌታ ሆይ፦ እኔ ደካማ ነኝና ማረኝ። አጥንቶቼ ታውከዋልና ጌታ ሆይ አንተ ፈውሰኝ። ነፍሴም እጅግ ታውካለች . . .

† † †

በኃይለኛው ዳዊትና በደካማው ዳዊት መካከል ታላቅ ልዩነት አለ።

ሰይፉን በወገቡ በሚታጠቀው፣ ጎልማሶቹም ሰይፎቻቸውን በወገባቸው እንዲታጠቁ በጠየቀውና ከሚሸልታቸው ብዙ በጎች መካከል ለእርሱ የሚገባውንና ለዕለቱ የሚያስፈልጉትን በጎች እንዲልክለት ጎልማሶቹን ወደ ናባል በላከበት ጊዜ ፈቃደኛ አልሆንም ሲል ሊገድሰው በተነሣው ዳዊት መካከል ልዩነት አለ፤1ኛ ሳሙ. 25:13እና22። በዚህ ጊዜ ዳዊት የተናገራቸው ቃላት ከባድ ስለ ነበሩ የተፈጠረውን ሁኔታ ትታደግ ዘንድ አቢግያ ካለችበት ቦታ ተነሥታ መጥታለች።

ይህ ሁሉ የሆነው በኃይል ውስጥ ነበር፤እግዚአብሔርም ለዳዊት በፈተናው ውስጥ ዋጋውን ከፍሎታል።

ከዚህ በኋላ ግን ዳዊት ኃጢአት ስለ ሠራ ተጸጽቷል፣ ንስሓ ገብቷል፣ መኝታውንም በዕንባዎቹ አርሷል። በመሆኑም ይህ ታላቅ ንጉሥ፣ ይህ ታላቅ መሪና ይህ ታላቅ ነቢይ በውስጡ የሚመኘና የሚወድቅ ደካማ ልብ በውስጡ እንዳለ ሊያውቅ ችሏል።

ስለሆነም በጸጸት ውስጥ ያለ ሰው ስለ ነበር ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ ብሎ ጸለየ።

እኔ ጎልያድን በታላቅ ኃይል ልገድል የቻልሁ ዳዊት አይደለሁም. . . ወይም ደግሞ የቀርሜሎሱን ናባል ያስፈራራሁ ዳዊት አይደለሁም። ጌታ ሆይ፡- አሁን በአንተ ፊት ደካማ ሰው ነኝና አቤቱ ምሕረትህ በእኔ ላይ ትሁን።

እግዚአብሔር ከደካሞች ጋር።

ምንጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር አምላክ ምሕረት የሚያደርገው ለደካማው ነው።

ታላቅ፣ ክባድ፣ ኃይለኛና ብርቱ ነኝ የሚለው ሰው ግን ከእግዚአብሔር የራቀ ሰው ነው። የእኛ አምላክ እግዚአብሔር የደካሞች አምላክ ነው. . . «ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ፤ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር የዓለምን የዓለምን ምኑ ነገር መረጠ፤ . . » 1ኛ ቆሮ 1:27። ብርቱ ሰው የሚመካው በኃይሉ ነው። ደካማው ሰው ግን እግዚአብሔር ከአጠገቡ የሚቆምለት ሰው ነው።

† † †

እግዚአብሔርን የሚመርጡት ብርቱዎችም ቢሆኑ በእርሱ ፊት የሚቆሙት እንደ ደካሞች ሆነው ነው። ስለሆነም አያንዳንዳቸው «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ፤» ይላሉ።

እንደ ምሳሌ አድርገን የደካማነት ስሜት የሚሰማቸውን ሰዎች መመልከት እንችላለን፦ ታላቁ ነቢይ ኤልያስ ኃይለኛ ሰው ነበረ። እርሱ በአንድ ወቅት አሳት ከሰማይ ወርዳ አምላውን እንድትበላ አድርጓል 1ኛ ነገ 1፡10። ኤልያስ አራት መቶ አምላ የበኣል ነቢያትን በማስያዝ አስገድሏቸዋል ፤1ኛ ነገ 18:40። እግዚአብሔር ለኤልያስ እንዲህ ያለው ነው የሚመስለው፦ ልጀ ሆይ፤ይህ ክባድ መንገድ አንተን ያሳሰበህ ይመስላል. . .

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ያደረገው ምንድር ነው? ንግሥቲቱ ኤልዛቤል ኤልያስን እንድታስፈራራው ስለ ፈቀደ ፈርቶ ወደ ምድረ በዳ ሸሽቷል። በዚህ ቦታ ላይም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከተገናኘ በኋላ «ኤልያስ ሆይ፦ በዚህ ምን ታደርጋለህ?» ብሎት ነበር። በዚህ ጊዜ ኤልያስ በፍርሃት ውስጥ እንዳለ «. . . ለሠራዊት አምላክ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ፤. . . ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና፤ እኔም ብቻዬን ቀርቻለሁ፤ ነፍሴንም ሊገድሏት ይሻሉ. . . » (1ኛ ነገ 19:14) ብሎ ነበር። ኤልያስ ሆይ. . . በመጨረሻ አንተም ልትፈራ ቻልህ. . .!!

† † †

እግዚአብሔር አምላክ የተዋረደና የተጸጸተ ልብን ስለሚፈልግ ጀግኖች የተባሉት ሰዎችም እንዲፈሩና ደካሞች እንዲሆኑ ይወዳል።

በእግዚአብሔር ፊት ደካማ ሆና የሚቆም ሰው በሰዎች ፊት ብርቱ ሆኖ መቆም የሚችል ሰው ነው. . . ራሳቸውን ብርቱዎች አድርገው ከሚቆጥሩት ሰዎች ግን እግዚአብሔር ራሱን ያርቃል።

በነቢዩ ኢሳይያስ የትንቢት መጽሐፍ ምዕራፍ 2 ውስጥ ስለዚህ ርዕሰ ጉዳይ የተጠቀሱ ዓረፍተ ነገሮች አሉ። ኢሳይያስ እንዲህ ነው ያለው፦

«የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቀን በትዕቢተኛውና በኮራተኛው ሁሉ ላይ ከፍ ባለውም ላይ ይሆናልና፤እርሱም ይዋረዳል፤ደግሞም በረዣዥሙ ከፍ ባለውም በሊባኖስ ዝግባ ሁሉ ላይ፣ በባሳንም ዛፍ ሁሉ ላይ፣ በረዣዥሙም ተራራ ሁሉ ላይ፣ ከፍ ባለውም ኮረብታ ሁሉ ላይ፣ በረዣዥሙም ግንብ ሁሉ ላይ፣ በተመሸገውም ቅጥር ሁሉ ላይ፣ . . . ሰውም ሁሉ ይዋረዳል፣ የሰውም ዙራት ይወድቃል፣ በዚያም ቀን እግዚአብሔር ብቻ ከፍ ከፍ ይላል።» ኢሳ 2፡12-17።

† † †

በብርታታቸው፣ በሥልጣናቸውና በኃይለኛነታቸው የሚመኩ ሰዎች እያንዳንዳቸው ሌሎችን የሚያጠቁና የሚጨቁ መስሎ ይታያቸዋል፤የሚቀጡና ከሥልጣን የሚያባርሩም ይመስላቸዋል። እነዚህ ሰዎች ትርጉምና ጥልቀት ባላቸው እና «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቀን በትዕቢተኛውና በኮራተኛው ሁሉ ላይ. . . ሰውም ሁሉ ይዋረዳል፣ የሰውም ዙራት ይወድቃል፣ በዚያም ቀን እግዚአብሔር ብቻ ከፍ ከፍ ይላል።» በሚሉት ቃላት ፊት ሲቆሙ አይፈሩምን?

እንዲህ ዓይነቱ ትዕቢተኛና ዙራተኛ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ራሱን አዋርዶ «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ፤» ማለት አለበት።

አንተ በሥራህ ውስጥ ታላቅ ማማ ልትሆን ትችላለህ. . . አንተ በሰዎች ፊት እንደ ሲባኖስ ዝግባ ልትሆን ትችላለህ. . . በእግዚአብሔር ፊት ስትቆም ግን በትሕትና ውስጥ ሆነህ «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ፤» በለው። እግዚአብሔር አምላክ የሲባኖስን ዝግባ ሲቆርጥ የባሳንንም ዛፍ ሲጥል ይችላል. . . በዚያን ቀን ከፍ - ከፍ ማለት የሚችለው እርሱ ብቻ ነውና።

† † †

ወንድሜ ሆይ፦ እውነት የሆነው ነገር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሰዎች ጋር አነጻጽረን ስንመለከተው እርሱ ለደካሞችና ራሳቸውን በእርሱ ፊት ለሚያዋርዱት ሁሉ እጅግ ርኅሩኅና እጅግ ቸር አምላክ መሆኑንና ኃይለኞችን ደግሞ ጥብቅ በሆነ ሁኔታ እንደሚመለከታቸው እንረዳለን።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደካማ የሆነውን ሰው በመቃወም የቆመበት ጊዜ ፈጽሞ አልነበረም። እርሱ ደካሞችን ይሰበስባቸዋል፣ ይጠብቃቸዋል፣ ይራራላቸዉማል።

† † †

ስታመነዝር የተያዘችውን ሴት ነጻ ካወጣት በኋላ እንዲህ ነበር ያላት፦ «. . . እኔም አልፈርድብሽም፤ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ኃጢአት አትሥሪ. . . » ዮሐ 8:11። እርሷ የተቀበለችው አፍረትና ውርደት ይብቃት ነበር። ኃይለኞች ነን የሚሉት ሰዎች ግን እርሷን በማጋለጥ ወደ ፍርድ ጎትተዋታል። በዚህ ጊዜ ጌታ ኃጢአቶቻቸውን በምድር ላይ ከፈፀ በኋላ እንዲህ ነበር ያላቸው፦ «. . . ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት . . . » ዮሐ 8:7። በዚህ ጊዜ ሊያፍሩ ስለ ጀመሩ አንዱ ሌላውን በመከተል ሄደዋል።

አነርሱ አፍረው የተመለሱት ለምን ነበር? ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ የተነገረውንና «. . . ሰውም ሁሉ ይዋረዳል፤የሰውም ዙራት ይወድቃል፤. . . » የሚለውን ቃል በዚህ ፈጽሞታል። ጌታ ለእነዚህ ሰዎች እንዲህ ያላቸው ነው የሚመስለው፦ «ሕስቲ ትዕቢታችሁን አቁመና ጭንቅላቶቻችሁን ዝቅ አድርጉ። እናንተም እኮ በፍርድ ፊት ኃጢአተኞች ናችሁ! . . . ይህቺንም ሴት ሆነ ሌሉች ሰዎችን በድንጋይ ለመውገር አትጣደፉ. . . ሁላችሁም «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ!» ልትሉ ይገባችኋል።

ደካሞች ሆናችሁ እግዚአብሔር እንዲምራችሁ ከፈለጋችሁ እናንተም ለደካሞች ምሕረት አድርጉ።

ለእግዚአብሔር እንዲህ በሉት፦ ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ! እርሱ ደግሞ እንዲህ ብሎ ይመልስላችኋል፦ ይህ ድካማችሁ ወይስ ነው ያለው? በዚህ ትዕቢትና ታላቅነት ውስጥ ነው ያለው?! በዚህ የበላይነት ውስጥ ነው ያለው?! . . . ደካሞች ስትሆኑ እኔ ምሕረት አደርግላችኋለሁ። ማንኛውም ሰው ተነሥቶ፦ «ጌታ ሆይ፦ እኔ ጀግና ነኝና ምሕረት አድርግልኝ ማለት ይችላልን? እኔ ጻድቅ ነኝና ምሕረት አድርግልኝ ማለት ይችላልን? አይችልም! እንዲህ ያለው አመለካከት የእግዚአብሔርን ምሕረት ለመጠየቅ አይረዳችሁም።

ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ተሸናፊ ነበር። እርሱ እንዲህ ያለ ነው የሚመስለው. . .

እኔ ጎልያድን የገደልሁ ጀግና ሰው አይደለሁም፤ከእርሳቤህ ጋር በኃጢአት የተገደልሁ ደካማ ሰው እንጂ።

በመጨረሻ እግዚአብሔር ለእርሱ ድኅነቱንና ደስታውን ባይመልስለት ኖሮ ኃጢአት በውስጡ ያለውን ገጽሕና ፃድቁነት ነበር።

† † †

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቀራጮችና ለኃጢአተኞች ከፍ ያለ ርኅራኄ ነበረው። እርሱ በገዛ ዐይኖቹ ፊት ራሱን ጻድቅ አድርጎ በመቁጠር በእርሷ ላይ ሊፈርድ ከነበረው ፈሪሳዊው ይልቅ እግሮቹን በዕንባው ጅ ስታጥብለት ለነበረችው ሴት ርኅሩኅ ነበር። ይህቺ ሴት አንድ ኃጢአት ስለ ሠራች እግዚአብሔር አልተቆጣትም። ይልቁንም ለእርሷ ፍቅርና ጸጸትን በመግለጽ ኃጢአትሽ ተሠርዮልሻል ብሏታል። ዙራተኛውን ፈሪሳዊ በተመለከተ ግን ይህቺ ኃጢአተኛ ሴት ከእርሱ እንደምትሻል ነግሮታል፤ሉቃ 7:36-48። ስለሆነም ሰበባዊነት ፍላጎት አያስፈልግም ማለት ነው። ይልቁንም በዳዊት መዝሙር ላይ እንደተጻፈው «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ!» ብትሉት የሚመረጥ ነገር ነው። ይህ ፈሪሳዊ በወቅቱ ደካማ ስላልነበረ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀጣው እንዲህ በማለት ገሥጾታል፦ «እኔ ወደ ቤትህ ገባሁ፤ውኃ ስንኳ ለእግሬ አላቀረብህልኝም፤. . . አንተ አልሳምሽኝም. . . አንተ ራሴን ዘይት አልቀባኸኝም፤. . . » ሉቃ 7:44-45። አንተ ማንኛውንም ዓይነት መከተንግዶ ወይም የፍቅር ሥራዎች አላቀረብህልኝም፤የአንተ ሥራ ሙሉ ለሙሉ ያተኮረው በልብህ በመፍረድ ላይ ብቻ ነበርና። ስለሆነም «ሰውም ሁሉ ይዋረዳል፣ የሰውም ዙራት ይወድቃል፣ በዚያም ቀን እግዚአብሔር ብቻ ከፍ ከፍ ይላል።»

† † †

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸሎቱ ውስጥ ስለ ጽድቅ ሥራው በመናገር ይኮራራ ከነበረው ፈሪሳዊ ይልቅ ኃጢአቱን በመናዘዝ ለነፍሱ ምሕረት ይጠይቅ ለነበረው ቀራጭ ርኅራኄ ነበረው። በመሆኑም ከፈሪሳዊው ይልቅ ቀራጩ ጻድቅ ሆኖ ተመልሷል፤ሉቃ 18:9-14።

† † †

አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአሕዛብ፣ ሰላምራውያንና ሲወደዱ ጀምሮ ዐይነ ሥውር ለነበረውና ከምኩራብ ላስወጡት ሰውርኅሩኅ ነበር። ክርስቶስ ይህን ሰው ካገኘው በኋላ ራሱን ገልጦለታል ወደ እምነትም ጋብዞታል፤ዮሐ 9:35-38።

ኃይለኞች የነበሩት ለመምራት ይችል ዘንድ ኃይለኛነታቸውን እስከሚተዉ ድረስ ጌታ ይተዋቸው ነበር። እርሱ ካህናትንና አለቆችን እንደዚሁም ቀራጮችንና ጻፎችን በቀኖጣው ይገሥጻቸው ነበር፤እነርሱ በጥብቅነታቸው እጅግ ክባዶች ነበሩና። ከዚህ በተጨማሪ ጌታ እነዚህን ሰዎች ስለ አስቸጋሪ ትእዛዞቻቸው እንዲህ በማለት ገሥጾአቸው ነበር፦

«እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፤መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ፤ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ። . . .»፤«. . . ፍርድንና ምሕረትን ታማኝነትንም፤በሕግ ያለውን ነገር ስለምትተዉ ወዮላችሁ፤. . .» ማቴ 23:13እና23። ክርስቶስ ከዚህ በተጨማሪ እነርሱ ነቢያትን ስለገደሉም በቀኖጣው ገሥጾአቸዋል፤ማቴ 23:31።

ከዚህ ሌላ እንዲህ በማለት በቀኖጣው ገሥጾአቸዋል፦ «ክባድና አስቸጋሪ ሸክሞች ተሸክፀው በሰው ትከሻ ይጭናሉ፤እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም።» ማቴ 23:4።

† † †

አቤቱ ጌታ ሆይ፦ እነዚህ ክባድ ትእዛዛት የእንተ ትእዛዛት ናቸውን?

ክርስቶስ ለዚህ የሰጠው መልስ አይደሉም የሚል ነው። ምክንያቱም የእርሱ ትእዛዛት ክባዶች አይደሉምና፤1ኛ ዮሐ 5:3። ከዚህ በተጨማሪ እንዲህ ብሏል፦ «. . . ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሲል ነውና።» ማቴ 11:30። በመሆኑም እርሱ ክባድ ሸክምን በሰዎች ላይ አይጭንም። አምላካችን በሌላ ጊዜ ደግሞ እንዲህ ብሎናል፦ «የምነግራችሁ ብዙ ነገር አለኝ፤ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም።» ዮሐ 16:12። ስለሆነም አሁን ያንን መሸከም አያስፈልግም ማለት ነው።

ልክ እንደዚሁ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትም በሥራቸው እርሱን ነበር የሚመስሉት። እነርሱ ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትን ሰዎች ለመቀበል በኢየሩሳሌም ገዛኢዎቹው ላይ ሲገናኙ እንዲህ ነበር ያሉት፦ «. . . ስለዚህ ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር

የሩሩትን እንዳናስቸግራቸው ነገር ግን ከጣዖት ርኩሰትና ከዝሙት ከታነቀም ከደምም ይርቁ ዘንድ እንድንጽፍላቸው አቁርጣለሁ።» ሐዋ 15:19፤20እና28።

ቸር የነበረውና ሰብዎች ክባድ ሸክም ማሸክም የማይወደው ሐዋርያው ትዳስ ጳውሎስም እንዲህ በማለት ተናግሯል፦ «እኔም ወንድሞች ሆይ፦ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፤በክርስቶስም ሕጻናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም። ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ውተት ጋትኋችሁ፤ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም።» 1ኛ ቆሮ 3:1-2።

† † †

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃይለኛው ዓሳው ይልቅ ደካማውን ያዕቆብ ነው የመረጠው። ከዚህ በተጨማሪ ወንድሞቹ በእርሱ ላይ በማሤር እንደ ባሪያ የሸጡት ደካማውን ዮሴፍ ነው የመረጠው።

እግዚአብሔር ያዕቆብን የመረጠው እንዲህ እያለ ወደ እርሱ በጮኽ ጊዜ ነበር፦ «ከወንድሜ ከዓሳው እጅ አድነኝ፤መጥቶ እንዳያጠፋኝ፤እናቶችንም ከልጆች ጋር እንዳያጠፋ እኔ አፈራዋለሁና።» ዘፍ 32:11። በዚህ ምክንያት ነው እግዚአብሔር «ያዕቆብን ወደድሁ ዓሳውን ግን ጠላሁ. . .» (ሮሜ 9:13) ያለው። ከዚህ ሌላ ያዕቆብና ዓሳው ከመወለዳቸው በፊት ነው እግዚአብሔር ለእናታቸው «. . . ታላቁም ለታናሹ ይገዛል።» (ዘፍ 25:23፤ሮሜ 9:12) ያላት።

† † †

እግዚአብሔር አምላክ ወንድሞቹ ወደ ጉድጓድ ከጣሉትና በመጨረሻም ለእስማኤላውያን አሳልፈው ከሸጡት ከወጣቱ ዮሴፍ ጋር ነበረ፤ዘፍ 37:20እና29።

የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን ለኃጢአት ሥራ በተጋፈጠችውና በሐሰት ወንጂ ባስጣለችው ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበር፤ዘፍ 39:19-20። ይሁን እንጂ ዮሴፍ በእግዚአብሔር ከፍ.ከፍ በማለት ለፈርዖን አባት፤ ለቤቱ ሁሉ የበላይና ለግብጽ ምድር ሁሉ ተጠሪ ሆኗል፤ዘፍ 43:26እና28።

† † †

እግዚአብሔር ከደካማው ከሙሴም ጋር ነበረ።

ስለዚህ ትሑትና ራሱን ዝቅ ስለሚያደርግ ስለ ሙሴ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው እንዲህ ተብሎ ነው፦ «ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ።» ዘኁ 12:3።

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ በማለት ተናግሮታል፦ «. . . እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ፤. . .» ዘጸ 7:1።

ይህም ማለት ለእርሱ አለቃ ትሆናለህ ማለት ነው። ሰውንድሙ ለአሮንም እንዲህ በማለት ተናግሮታል፦ «አንተም ትናገረዋለህ ቃሉንም በአፉ ታኖራ፤ የሚሆነውን እርሱ እኛ ይሆንልሃል፤ አንተም በእግዚአብሔር ፋንታ ትሆንለታለህ።» ዘጸ 4:15-16። ይህም ማለት አሮን የመነሣሣት ምንጭ ስለሚሆንለት ቃሉን ለመናገር መነሻ ይሆነዋል ማለት ነው።

አሮንና እኅቱ ማርያም ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን ሴት ሲያገባ በተቃውሞ ባንረመረመቡት ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረ። በመሆኑም እግዚአብሔር ለእርሱ በመሢገት እንዲህ ብሎ ተናግሯቸዋል፦ «. . . እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው። እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ፤. . .» ዘኁ 12:7። ከዚህ በኋላ የሙሴ እኅት ማርያም እርሱን ስለ ተናገሯች እግዚአብሔር አምላክ በለምጽ መትታታል።

† † †

ከሕዝቡ መካከል በሦስቱ የሚዛኑን ሰዎች ላይ ደካማውን ሙሴና ጨካኑን ፈርዖን የሚያስቀምጠው ማነው?!

ከእነዚህ ከሦስቱ የሚያሸንፈውስ ማነው ይላሱ?!

መጀመሪያ ላይ ፈርዖን ሥልጣኑንና ጨካኝነቱን እንዳስፈለገው መጠቀም ጀምሮ ነበር። ሙሴ በመካከል ስለ እነርሱ ጣልቃ እስከሚገባ

ድረስ ሕዝቡን ያስቃያቸው ነበር። በዚህም ጊዜ ፈርዖን በትዕቢት እንዲህ ነበር ያለው፦ «. . . ቃሉን አለማ ዘንድ እስራኤልንስ አስቅቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማነው? እግዚአብሔርን አላውቅም፤እስራኤልንም ደግሞ አልለቅም. . .» ዘጸ 5:2።

ታዲያ መጨረሻው ምን ሆነ? ደካማው፣ የተረጋጋውና ትሑቱ ሙሴ በትዕቢተኛው ፈርዖን ላይ ድል ተቀዳጅቷል።

† † †

ባላቸው ጭካኔ ሁሉ እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን አስረው ወደ አሳቱ በወረወሯቸው በምስቱ ብላቴናዎች ላይ የደረሰው ሁኔታም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ከእነዚህ ደካማ ልጆች ጋር ስለ ነበረ አንዲቷ ጠጉራቸው እንኳ አልተቃጠለችም። ሰላው ሁሉ ቢቀር የአሳቱ ሽታ እንኳ አልደረሰባቸውም። ይልቁንም የሚጉላላውና አሳት ያቃጠለው አነርሱን ወደ አሳቱ የወረወሯቸውን ጨካኝ ሰዎች ነበር። በመጨረሻ ከአሳቱ ውስጥ ካወጧቸው በኋላ ናቡከደነፆር እንዲህ ነበር ያለው፦ «. . . መልአኩን የላከ፤ ከአምላካቸውም በቀር ማንንም እንዳያመልኩ ለእርሱም እንዳይሰግዱ ሰውነታቸውን አሳልፈው ባሪያዎቹን ያዳነ የሲድራች፣ የሚሳቅና የአብድናጎ አምላክ ይባረክ።» ከዚህ በኋላም ንጉሡ በባቢሎን አውራጃ ውስጥ ማዕረግ ሰጥቶአቸዋል፤ዳንኤል 3:28እና30።

ጨካኝ ሰዎች በክፋት በማሤር እርሱን ወደ አናብስት ጉድጓድ እንዲጣል ባደረጉት ጊዜ እግዚአብሔር ከደካማው ከዳንኤል ጋር ነበረ። ይሁን እንጂ እርሱን በሐሰት የወነጀሉትን ሰዎች ንጉሡ ዳርዮስ ወደ ጉድጓዱ እንዲጣሉ አድርጓል፦ «ንጉሡም አዘዘ፤ዳንኤልንም የከሰሱ አንዚያን ሰዎች አመጡአቸው፤እነርሱንና ልጆቻቸውንም ሚስቶቻቸውንም በአንበሶች ጉድጓድ ጣሉአቸው፤ወደ ጉድጓዱ መጨረሻ ሳይደርሱ አንበሶች ያዙአቸው፤አጥንታቸውንም ሁሉ ሰባበሩ።» ዳን 6:24።

† † †

ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር አምላክ ደካማውና ሙኩ ዳዊት በግዙፉ ዖልያድ ፊት በቆመ ጊዜ ከእርሱ ጋር ነበረ።

ይህ ግዙፍ ሰው ዳዊትን በተመለከተው ጊዜ ናቀው አሳንቋበትም፤ብላቴና ነው ብሎ አሸሸልሷ። ዳዊት ግን ጠጠሩን በወንጭፉ ውስጥ ካስገባ በኋላ ነፍሱ ሁሉ «ድጪይ ነኝና አቤቱ

ማረኝ!» እያለች ወደ እግዚአብሔር ትጮህ ነበር:: እግዚአብሔርም ከዳዊት ደካም ጋር ስለ ነበረ በጎልያድ ላይ ድል አቀዳጅቶታል፤ራሱ ዳዊት እንደተናገረው ሰልፉ ለእግዚአብሔር ነውና:: ከዚህ በተጨማሪ ለጎልያድ እንዲህ ብሎታል:- «. . . አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ፤እኔ ግን በተገዳደርኸው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ ስም በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ:: እግዚአብሔር አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል!. . .» 1ኛ ሳሙ 17:45-47::

† † †

ታላቁ ቅዱስ እንጦንስ «ደካማ» የሚለውን ቃል ተጠቅሞበታል::

እርሱ በምድረ በዳ ሳለ አጋንንት ሲያሰቃዩት እንዲህ ነበር ያላቸው:- «እናንተ ብርቱዎች ናችሁ፤ከእኔ ከደካማው የምትፈልጉት ምንድር ነው? . . . እኔ ከእናንተ መካከል ታናሽ ከተባለው ጋር እንኳ ልዋጋ አልችልም::» አጋንንት ይህን በትሕትና የተሞላ ጸሎት ሲሰሙ እንደ ጉም በነው ጠፍተዋል:: ይሁን እንጂ በዚህ ቅዱስ ሰው ጥልቀት ውስጥ «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ!» የሚለው ጸሎት ቀርቶ ነበር::

አቤቱ ጌታ ሆይ:- እኔ በአንተ ፊት ደካማ ነኝ::

እኔ «. . . የሚውጠውን ፈልጎ እንደ አንበሳ ይዞራልና. . .» (1ኛ ጴጥ 5:8) ተብሎ በተነገረለት በሰይጣን ፊት ደካማ ነኝ:: ይሁን እንጂ የእኔ ብርታት ያለው በአንተ ውስጥ ነው:- «ኃይሌም ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው፤እርሱ መድኃኒት ሆነልኝ::» መዝ 117:14::

እኔ በራሴ ፊት ደካማ ነኝ:: ስለሆነም ያለ ማቋረጥ እርዳታህን እሻለሁ::

እኔ በሰዎችም ፊት ደካማ ነኝ:- «እንግዶች ቁመውብኛልና፤ ኃያላንም ነፍሴን ሽተዋታልና:: እግዚአብሔርን በፊታቸው አላደረጉትም::» መዝ 53:3::

ስለ[illegible] ወንድሞቼ:- እያንዳንዳችሁ በኃይል ሥልጣን ወይም በጭካኔ የተ[illegible]ላ ሁኔታ ውስጥ ከመግባት ራሳችሁን ጠብቁ::

ሌላው ቢቀር በኩራት መንፈስ ውስጥ ሆናችሁ:- እሠራለሁ፣ እቀጣለሁ፣ ትምህርት እሰጣለሁ አትበሉ::

ወንድሜ ሆይ:- ሥልጣን የተሰጠህ ከሆነ ተጠንቀቅ:: ራስህን ጠብቅ፤ከራስህም ተጠበቅ:: የወጣትን ኃይል፣ ሥልጣንና ጭካኔ ገንዘብህ አታድርግ:: ይልቁንም በጸሎትህ እንዲህ በል:-

«ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ፤የማንንም ዕድል ፈንታ በእኔ እጅ ውስጥ አታስቀምጥ፤የእኔንም ዕድል ፈንታ በሌሎች ሰዎች እጅ ውስጥ አታስቀምጥ:: እኔን ይረግጠኝ ዘንድ ለማንኛውም ሰው አንተ ኃይል አትስጠው:: ጌታዬ ሆይ:- እኔም ሌላውን ሰው እረግጠው ዘንድ ኃይል አትስጠኝ::»

መጉዳትን ሳይሆን መጎዳትን፤መስቀልን ሳይሆን መሰቀልን፤ ማሸነፍንም ሳይሆን መሸነፍን ዘወትር አድለኝ፤በዚህ ጊዜ አንተ ከእኔ ጋር ትሆናለህና:: በአንተ ፊት በራሴ ላይ ድል የምቀዳጅ አድርገኝ እንጂ በሰዎች ላይ ድል የምቀዳጅ አታድርገኝ::

እያንዳንዱ ሰው ኃይልን፣ ኩራትንና ታላቅነትን ይፍራ:: ምክንያቱም:- «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቀን በትዕቢተኛውና በኵራተኛው ሁሉ ላይ ከፍ ባለውም ላይ ይሆናል!. . . ሰውም ሁሉ ይዋረዳል፣ የሰውም ኵራት ይወድቃል፣ በዚያም ቀን እግዚአብሔር ብቻ ከፍ ከፍ ይላል::» ተብሎ ተጽፎአልና::

† † †

የአሦርያ ንጉሥ የነበረውን ሰናክሬም ምሳሌ አድርገን እንመለከታለን::

እርሱ በኃይሉ እጅግ ይመካ ስለ ነበረ በሙሉ ኩራት ውስጥ ሆኖ የይሁዳ ንጉሥ የነበረው ሕዝቅያስን ለማስፈራራት ሰዎችን ወደ እርሱ ልኮበት ነበር:: ሕዝቅያስ በዚህ ሁሉ ታላቅ ሠራዊት ፊት እና በሰናክሬም ማስፈራሪያ ፊት ሊያደርግ የሚችለው ምን ነበር? ሕዝቅያስ ድካሙ ስለ ታወቀው ልብሱን ቀደደ፤ማቅ ሰብሶም ወደ እግዚአብሔር ቤት ገባ:: ወደ እርሱም እንዲህ ብሎ ጸለየ:- «አቤቱ:- ጆሮህን አዘንበልና ስማ፤አቤቱ:- ዓይንህን ክፈትና አይ፤ በሕያው አምላክ ላይ ይገዳደር ዘንድ የላከውን የሰናክሬምን ቃል ስማ:: . . . የምድር መንግሥታት ሁሉ አንተ ብቻ እግዚአብሔር አምላክ እንደ ሆንህ ያውቁ ዘንድ እንድታድነን እለምንሃለሁ::» 2ኛ ነገ 19:16-19:: ንጉሥ ሕዝቅያስ የእግዚአብሔር ነቢይ ወደ ሆነው ወደ ኢሳይያስ መልእክተኞች ልኮ ነበር:: የሕዝቅያስ ስሜትም ድውይ ነኝና አቤቱ ማረኝ የሚል ነበር. . .

በዚህ ምክንያት ነው ነቢዩ ኢሳይያስ ለሰናክሬም እንዲህ በማለት የተናገረው:- «የተገዳደርኸው የሰደብኸውስ ማን ነው? ቃልህንስ ከፍ ከፍ ያደረግኸው ዓይንህንም ወደ ላይ ያነሣኸው በማን ላይ ነው? በእስራኤል ቅዱስ ላይ ነው::» 2ኛ ነገ 19:22:: «በዚያችም ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ወጣ፤ከአሦራውያንም ሰፈር አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ሺሕ ገደለ፤ማለዳም በተነሡ ጊዜ እነሆ ሁሉ በድኖች

ነበሩ::» 2ኛ ነገ 19:35:: ሰናክሬምም ወደ ነነዌ ከተመለሰ በኋላ የገዛ ልጆቹ በሰይፍ ገድለውታል::

እነዚህ ሁሉ ደካማ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ሲቆሙ የሚከተለውን የመዝሙር ቃላት ያዜሙ ነበር:- «አጥንቶቼ ሁሉ እንዲህ ይሉሃል:- አቤቱ እንደ አንተ ማነው? ችግረኛን ከሚቀማው እጅ፤ችግረኛንና ድሀውንም ከሚነጥቀው እጅ ታድነዋለህ::» መዝ 34:10::

ይህ የሚሆነውም ደካሞች፣ ድሆችና ችግረኞች ከጥልቅ ውስጣቸው «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ» ብለው ስለሚጮሁ ነው:: ብርቱዎች ነን የሚሉት ግን ደካሞች ናቸው::

ኃጢአት እንኳ አብዝታ የምትቆጣጠረው ብርቱዎቹን ነው::

በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአት እንዲህ ብሏል:- «ወግታ የጣለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸውና፤እርስዋም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው::» ምሳ 7:26::

ከብርቱዎቹ መካከል ምሳሌ የሚሆነን ራሱን ከኃጢአት የማይጠብቀው ሰው ነው:: እርሱ እንዲህ ነው የሚለው:- ይህ ኃጢአት ቀላል ስለሆነ ለእኔ አይደለም፤ጀማሪዎች ይዋጉት! ራሱን የሚጠብቀው ደካማ ግን «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ!» ይላል:: የሚድነውም ይህ ነው::

† † †

ከዕለታት አንድ ቀን በማስታወሻ ደብተሬ እንዲህ የሚል አገላለጽ አስፍሬ ነበር:- ሰይጣን በአንድ ወቅት ለእግዚአብሔር እንዲህ አለው:- ብርቱዎቹን እኔ ስለምጠብቃቸው ለእኔ ተዋቸው:: እኔ የምፈራቸው ደካሞቹን ነው፤እነርሱ ድካማቸውን ያውቃሉና:: እነርሱ የሚዋጉኝ በአንተ ኃይል ስለሆነ ያሸንፉኛል::

ደካማው ሰው ዘወትር ወደ አንተ «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ!» እያለ የሚጮኸው ነው:: እኔ ይኼኛውን ሰው መቆጣጠር አልችልም. . . እርሱ ሁልጊዜ ወደ አንተ ስለሚጮህ አንተ ወደ እርሱ መጥተህ ከጎኑ በመቆም ለእርሱ ትዋጋለታለህ፤እኔም ድል ልነሣው አልችልም::

ነቢዩ ዳዊት እግዚአብሔር አምላክ ከብርቱዎች ይጠብቀው ዘንድ ዘወትር ወደ እርሱ ይጮህ ነበር::

በመሆኑም እንዲህ ይል ነበር:- «አቤቱ በስምህ አድነኝ፤ በኃይልህም ፍረድልኝ:: አቤቱ:- ጸሎቴን ስማኝ፤የአፌንም ቃል

አድምጥ!. . . ኃያላንም ነፍሴን ሽተዋታልና::» መዝ 53:1-3:: እኔ ግን «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ!» ከማለት በስተቀር ሌላ የምለው ነገር የለኝም:: ምክንያቱም እግዚአብሔር አምላክ ብርቱዎች ከሚባሉት ሁሉ የበረታ ነውና::

እግዚአብሔር በኩራት ውስጥ ሆነው በብርታታቸው የሚመኩትን ወይም ብርቱ የሆኑ የሚመስላቸውን ወይም በብርታታቸው ላይ የሚደገፉትን በሙሉ ይቃወማል::

† † †

እግዚአብሔር አምላክ በነቢዩ አሞጽ የትንቢት መጽሐፍ ውስጥ የተናገረውን ልብ በሉ:- «እኔ ግን ቁመቱ እንደ ዝግባ ቁመት፤ ብርታቱም እንደ ኮምበል ዛፍ የነበረውን አሞራዊውን ከፊታቸው አጠፋሁ፤ፍሬውንም ከላዩ፤ሥሩንም ከታቹ አጠፋሁ::» አሞ 2:9:: እግዚአብሔር ድሆችን ያጠፋቸው ዘንድ ይፈልጋቸዋል ማለት አሳማኝ ነገር አይደለም፤በትዕቢት ማዕረጋቸው እስከ ሰማይ ድረስ ከፍ-ከፍ ያሉትን ግን ያጠፋቸዋል::

ቤተ መቅደሱ ሊሠራ ሲጀመር ለዘሩባቤል የእግዚአብሔር እርዳታ አስፈልጎት ነበር:: ይህ እግዚአብሔራዊ እርዳታ በትንቢተ ዘካርያስ መጽሐፍ ውስጥ የመጣለት እንዲህ በማለት ነበር:- «. . . በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም፤ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር:: ታላቅ ተራራ ሆይ:- አንተ ምንድር ነህ? በዘሩባቤል ፊት ደልዳላ ሜዳ ትሆናለህ::» ዘካ 4:6::

ለደካማው ሰው ብርታት የሚመጣለት ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው:: በመሆኑም ጻድቁ ኢዮብ እንዲህ በማለት ተናገረ:- «ኃይል የሌለውን ምንኛ ረዳኸው? ብርታት የሌለውን ክንድ ምንኛ አዳንኸው?» ኢዮ 26:2::

የተባረክኸው ልጂ ሆይ:- በጸሎቶችህ ውስጥ «ድውይ ነኝና አቤቱ ማረኝ!» የሚሉት ቃላት ላይ ስትደርስ ወደ ነፍስህ ጥልቀት ውስጥ ግባ እና በነፍስ ቤተ መቅደስ ውስጥ የተደራጁትን ጣዖታት ሰባብራቸው::

ልትሰባብረው የሚገባህ የመጀመሪያው ጣዖት ራስ ወዳድነት ነው:: በዐይኖችህ ፊት ያለው፣ ድንቅ መስሎ የሚታይ፣ አንተን ከፍ-ከፍ የሚያደርግህ፣ የሚመራህ፣ አንተም መመሪያውን ተፈጻሚ የምታደርግለት፣ የሚመታህና ኃይልህን የሚነጥቅህ የአንተ ታላቅ እና ብርቱ ራስ ወዳድነት አንተንም ሊመታህ ይችላልና አንተ ቀድመህ ምታው::

በአንተ ዘንድ ያለው ራስ ወዳድነት አመድና አፈር ሆኖ ሲለወጥ በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ከአንተ አጠገብ ይቆማል።

እግዚአብሔር አምላክ ከአንተ አጠገብ ሲቆምም «ድውይ ነኝና አቤቱ ማረኝ!» የሚሉትን ድንቅ ቃሳት በጆሮዎቹ ውስጥ ሹክ በልለት።

የኢዮብ ምሳሌነት።

ታላቁ ነቢይ ኢዮብ በጽድቁ እና በታላትነቱ በተመካ ጊዜ ለመከራና ለበትር ተላልፎ ተሰጥቶ ነበር። እንዲህ በማለት ተናግሮ ነበርና፦ «እግዚአብሔር ይጠብቀኝ እንደ ነበረው ጊዜ፣እንደ ፊተኛው ወራት ምነው በሆንህ! . . . መንገዴ በቅቤ ይታጠብ በነበረ ጊዜ፣ ድንጋዩ የዘይት ፈሳሽ ያፈስስልኝ በነበረ ጊዜ። ወደ ከተማይቱ በር በወጣሁ ጊዜ፣በአደባባዩም ወንበሬን ባኖርሁ ጊዜ፣ጎበዞች እኔን አይተው ተሸሽጎ፣ሽማግሌዎችም ተነሥተው ቆሙ። አለቆች ከመናገር ዝም አሉ፣እጃቸውንም በአፋቸው ላይ ጫኑ። . . . የሰማችኝ ጆሮ አሞገሰችኝ፣ያዩኝም ዓይን መስክረችልኝ፣የሚጮኸውን ችግረኛ፣ ድህ አደጉንና ረዷ የሌለውን አድኜ ነበርሁና። . . . ጽድቅን ለብሰሁ፣ እርስዋም ለበሰችኝ፣ፍርዴም እንደ መጎናጸፊያና እንደ ሦፋር ነበረ።» ኢዮ 29:1-14።

ከዚህ በተጨማሪም በብርታቱና በጽድቁ ኩራት ውስጥ ሳለ እንዲህ በማለት ተናግሮ ነበር፦ «የኃጢአተኛውን መንጋጋ ሰብሮሁ፣ የነጠቀውንም ከጥርሱ ውስጥ አስጣልሁ።» ኢዮ 26:17። እርሱ እኔ፣ እኔ፣ . . . የምትሰውን አዛባል ደጋግሚት ነበር።

† † †

ኢዮብ ይህችን አባባል ሲደጋግማት ራሱን አጽድቆ ነበርና «ሊዮብም ራሱን ጻድቅ አድርጎ ነበርና . . .» (ኢዮ 32፣1እና35፣2) እግዚአብሔር ገሥጾታል።

በመጨረሻ ግን ራሱን ሲንት ለእግዚአብሔር እንዲህ በማለት ተናግሮ ነበር፦ «ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፣በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ አጸጸታለሁ።» ኢዮ 42፣10። እርሱ ወደ አመድና ወደ አፈር በተጠጋ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ ፊተኛውን ከእርሱ ላይ አንሥቶለታል። «. . . እግዚአብሔር ምርኮውን መለሰለት፣ እግዚአብሔርም ቀድሞ በነበረው ፋንታ ሁለት እጥፍ አድርጎ መለሰለት።» ኢዮ 42፣10።

ኢዮብ ወደ አመድና ወደ አፈር በተጠጋ ጊዜ ነቢዩ ጻዲት ወደ ተናገራቸውና «ድውይ ነኝና አቤቱ ማረኝ!» ወደሚሉት ቃላትም ተጠግቶ ነበር።

እርሱ በቀደሙት ዘመናት ውስጥ ክብርና ታላትነት ነበረው። በዚህ ጊዜ እንዲህ ብሎ ነበረ፦ «. . . ጎበዞች እኔን አይተው ተሸሸጉ፣ ሽማግሌዎችም ተነሥተው ቆሙ። አለቆች ከመናገር ዝም አሉ፣እጃቸውንም በአፋቸው ላይ ጫኑ።» ኢዮ 29፣8-9። አሁን ግን አመድና አፈር ሲሆን ወደ ራሱ አውነት ደርሷል።

† † †

እኔ ለሁሉም ሰው የምስጠው ምክር፦ አናንተ ያላችሁበትን ብርታታችሁንና ኩራታችሁን እንዲሁም ፍላጎታችሁን እርሱት የሚል ነው።

ሥልጣን ከተሰጣችሁ አትጠቀመብት፣ማሰቴም ራሳችሁን ከፍ ከፍ እንዲያደርጋችሁ አድርጋችሁ አትጠቀመብት።

በሌሎች ሰዎች ላይ አትብርቱ. . . ማንኛውንም ሰው ከእግሮቻችሁ በታች አታድርጉ. . . በማንም ላይም አትመጻደቁ። ዘውትር ድል ለመንሣት ወይም ለማሸነፍ የምትሞክሩ አትሁኑ ወይም በማንኛውም አጋጣሚም ሰብአናችሁንና ብርታታችሁን ለማሳየት አትሞክሩ. . . የማንንም ቅስም አትሰባብሩ. . . ይልቁንም በሰዎች ሁሉ ፊት ትሑታን ሁኑ. . . ከነቢዩ ጻዲት ጋር ሆናችሁም «ድውይ ነኝና አቤቱ ማረኝ!» በሉ።

የጻዲት ድካምና መከራ።

አውነቱ ነገር ነቢዩ ጻዲት በመዝሙራቱ ውስጥ በተደጋጋሚ ስለ ድካሙና ስለ ድካሙ መናገሩ ነው፣በተለይም በጠላቶቹ ብርታትና ኃይል ፊት።

እርሱ ይህን ያደረገው በዚህ በመዝሙር 6 ውስጥ ብቻ አይደለም፣ በሌሎችም ብዙት ባላቸው መዝሙራት ውስጥ እንጂ። በነገህ ጸሎት በመጪረሻው መዝሙር ውስጥ እንዲህ በማለት ጸሎቱን አድርሷል፦

«ጠላት ነፍሴን አሳድዶአታል፣ሕይወቴንም በምድር ውስጥ አንስቀሎአታል፣ቀድሞ እንደ ሞተ ሰው በጨለማ አኑሮኛል። . . . አቤቱ ወደ አንተ ተማፅኛለሁና፣ከጠላቶቼ አድነኝ። በጽድቅህ ነፍሴን ከመከራዋ አውጣት።» መዝ 143።

ጻዲት በእግዚአብሔር ፊት ሲቆም ጠላቶቹን ድል እንደሚነሣ ኃይል ሰው ሆኖ አልነበረም፣የጠላቶቹን እደጋ እንደሚጋፈጥ ደካማ ሰው ሆኖ እንጂ። እነዚህ ጠላቶቹ አርሱን የሚያሳድዱት፣ መከራ የሚያጸንብትና ከሞቱ ረኽናም ዘመናት እንዳስቆጠሩት ሰዎች በጨለማ ውስጥ እንዲኖር የሚያደርጉት ነበሩ።

† † †

ታዲያ እናንተ ከእነዚህ መዝሙራት የምትጠቀሙት ምንድር ነው? በሕይወታችሁ ውስጥ የምታደርጉትስ እንዴት ነው? በምን ዓይነት መንገድ? «ከጠላቶቻችን» ስትሉስ ምን ማለታችሁ ነው?

ከሰዎች ጋር በመነጋገር ውስጥ በሚኖረው ተግባራዊነት ከሆነ የእናንተ ጠላቶች፦ ተቃዋሚዎች ወይም ጠላቶች ናቸው። በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ ከሆነ ግን የእናንተ ጠላቶች ሊጋንኑት፣ አሰቦችና ምኞቶች ናቸው።

መልካም የሆነውን ሁሉ የሚቃወም ተቃውሞ ነፍሴን አሳድዶአታል። እርሱ በእኔ ላይ የከፈተው ውጊያ ሰሪኛም ጊዜ ቆይቷል. . . በኃጢአት ውስጥ እንድወድቅና በ[illegible]ት አትምም እንድዋጋው አድርጎኛል። ከአውነተኛው ብርሃን በማ[illegible]ት በጨለማ ውስጥ እንድናና አድርጎኛል። ጨለማ ደግሞ የኃጢአት ሕይወት ነው። ይህን ሰዎች ክብርሃን ይልቅ የወደዱት ነገር ነው፦ «. . . ሥራቸው ክፉ ነበርና. . .» ዮሐ 3፣19። በዚህ ጨለማ ውስጥ የሚኖሩት እነዚህ ሰዎች ደግሞ መጪረሻ ላይ፦ «. . . በውጭ ወደ አለው ጨለማ ይጣላሉ፣» (ማቴ 8፣12)፤«. . . በዚያም ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።» ማቴ 25፣30።

ይህ ደግሞ ወደ ዘላለማዊው ሞት የሚመራው መንፈሳዊ ሞት ነው፣ሉቃ 15፣24፤ራሕ 3፣2። ይህ በጨለማ ውስጥ የሚቀመጡት ሰዎች ዕጣ ነው፣አስክ ሕልቀተ ዓለም ድረስ እንደ ሞቱት መሆን።

በዚህ ዓይነት መንገድ ነው ጻዲት መከራውን ስላጸነበት ጠላቶቹ ኃይል የተናገረው። እርሱ በመዝሙር 20 ውስጥ ስለ ጠላቶቹ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «እነዚያ በሰረገላ እነዚያም በፈረስ ይታመናሉ፣እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ክፍ ክፍ እንላለን።» መዝ 19፣7። እኔ ሰረገሎች እንዳሉአቸው እንደነዚህ ኃያላን አይደለሁም፣ፈረሶችም ከሰረገሎቹ ጋር ነበረና። እኔ የምበረታው በእግዚአብሔር ስም ነው፣በኃይልም ፊት የቆምሁት በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም ነበረና፣1ኛ ሳሙ 17፣45።

† † †

በሰድስተኛው ጸሎት ውስጥ ከምንደግማቸው መዝሙራት መካከል የመጀመሪያውን መዝሙር ከነቢዩ ጻዲት ጋር በመሆን እንዲህ እንለዋለን፦ «አቤቱ፦ ጸሎቴን ስማኝ፣የአፌንም ቃል አድምጥ፣እንግዶች ቁመውብኛልና፣ኃያላንም ነፍሴን ሽተዋታልና። እግዚአብሔርን በፊታቸው አላደረጉትምና።» መዝ 53፣4-5።

እነዚህ ሰመንግሥቱ እንግዶች. ናቸው። ኃያላኑ የታጠቁትም የመልካም ነገር ተቃዋሚ የሆኑትን መሣሪያዎች ሁሉ ነው። እነርሱ ነፍሴን የሻታት ሊያጠፏት ነው፣እንተን በፊታቸው አላደረጉህምና። እኔ ግን እንዲህ አላሰሰሁ፦ «ውልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ፣በቀኜ ነውና አልታወከም።» መዝ 15፣8።

† † †

በጠላቶቼ ኃይል ፊት የሚበልጠውን የእግዚአብሔር ኃይል አስቀምጣለሁ።

ነቢዩ ጻዲት በስድስተኛው ጸሎት ሁለተኛ መዝሙር ውስጥ የጠላቶቹን ኃይል በመከታተል ሲጀምር እንዲህ ብሏል፦ «እግዚአብሔር ቸርነቱንና አውነቱን ላክ። ነፍሴን ከአንበሶች መካከል አዳናት። ደንግጠው ተኛሁ፣የሰው ልጆች ጥርሶቻው ጦርና ፍላጻ፣አንደበታቸውም የተሳለ ሾተል ነው።» መዝ 56፣3-4። እግዚአብሔር አምላክ የጻዲትን ነፍስ ከአናብስት መካከል ያዳናት በፍርሃትና በድንጋጤ ተኝቶ ሳለ ነበር።

እርሱ በዚሁ ተመሳሳይ መዝሙር ውስጥ እንዲህ በማለት ተናግሯል፦ «. . . ለአግሮቼ ወጥመድን አዘጋጁ፣ነፍሴንም አጉበጡአት፣ጉድጓድን በፊቴ ቈፈሩ፣በአርሱም ወደቁ።» 56፣6።

አቤቱ ጌታ ሆይ፦ እኔ የጠላቶቼን ኃይል እና በእኔ ላይ የተጠመደውን ወጥመድ ባስታወስሁ ጊዜ ሁሉ የአንተን እኔን ለማዳን መምጣት አብሬ አስታውሳለሁ።

እነርሱ እኔን በመቃወም አንደበታቸውን እንደ ሾተል ቢስሉም ጥርሶቻቸውን አረሳቸዋለሁ። እነርሱ እኔን ለመያዝ በፊቴ ያዘጋጇቸውን ወጥመዶችም አረሳቸዋለሁ። አወድቅበት ዘንድ በፊቴ የቆፈሩትን ጉድጓድም አረሳዋለሁ. . . እኔ የማስታውሰው ስእኔ ባጠመዳት ወጥመድ ውስጥ እንዲወድቁ የሚያደርጋቸውን የአንተን ምሕረት ብቻ ነው. . .

† † †

ጻዲት የእነርሱን የጭካኔ መጠንና እንዴት እንደ አሳት እንደ ከበቡት በመዝሙር 117 (በፀሐይ መጥለቂያ ጸሎት) ውስጥ እንዲህ በማለት ገልጾታል፦

«መከበቡንስ ከበቡኝ፣በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው፣ንብ ማርን እንዲከብብ ከበቡኝ፣እሳትም በእሾህ ውስጥ እንዲነድድ ነደዱ፣ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው።» መዝ 117፣11-12።

ዳዊት ሆይ፡- በዚህ ሁሉ አደጋ ፊት የእንተ ሁኔታ እንዴት ነበር?

እንዲህ ነው ያለን፡- «ገፋኸኝ፣ለመውደቅም ተንገደገድሁ፣ እግዚአብሔር ግን አገዘኝ። . . . የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን የእግዚአብሔር ቀኝ ክፍ አደረገችኝ፣የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች። . . . . አልምትም በሕይወት እኖራለሁ እንጂ፡፡ የእግዚአብሔርንም ሥራ እናገራለሁ።» መዝ 117:13-16።

እኔ ስለ ራሴ ድካምና ስለ እነርሱ ብርታት አልናገርም፣እኔን ስለ መታደጉና እኔን ስለ ማዳኑ ሥራ እንጂ።

ይህ በመሆኑም ነቢዩ ዳዊት ስለ ጠላቶቹ ኃይልና ባእርሱ ላይ ስላመጡት ስለ ክፉ ጭካኔያቸው የተናገረባቸውን ቃላት የሚደመድመው በሚከተሉት ድንቅ የመዝሙር ቃላት ነው፡-

«ኃይሌም ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው፣እርሱም መድኃኒት ሆነልኝ።» 117:14።

እኛም ይህን ጥልቅ አንላለጽ በድንቅነቱ በማስታወስ በሰሙነ ሕማማት ውስጥ እንዘምረዋለን። የምናስታውሰውም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጋፈጣቸውን ሕማምና መከራ በማሰብ ነው። ይህ ለእኛ ኃይላችንና ድኀነታችን ሆኗል። እርሱ ለእኛ ብርታትና ድኀነት በመሆኑም እርሱን እናመሰግነዋለን።

† † †

ከዚህ በተጨማሪ ዳዊት በፀሐይ መጥለቂያ ጸሎት ውስጥ ከሚደገመው መዝሙራት መካከል ይኼኛውን እናስታውሳለን፡- «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን፣ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ፣ ቊጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ፣በዚያን ጊዜ ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር፤ . . .» መዝ 123:2-3። ዳዊት ሆይ፡- እንተ በእነርሱ ፊት ደካማ የሆንኸው እስከዚህ ድረስ ነበርን? እነርሱስ በእንተ ላይ ብርቱዎች የሆኑት ይህን ያህል ነበርን?!

በዚህ ጊዜ እንዲህ በማለት ይመልስልናል፡- «ሰጥርሳቸው ንክሻ ያላደረገን እግዚአብሔር ይባረክ።» መዝ 123:6። እነርሱ እንደሚናከሱ አውሬዎች ነበሩ ማለት ነው?! አዎን ነበሩ፣ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በመካከል በመግባት አድኖናል፡- «ነፍሳችን እንደ ወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች፣ወጥመድ ተሰበረ እኛም አመለጥን። ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው።» መዝ 123:7-8።

ዳዊት እንዲህ የሚል ነው የሚመስለው፡- ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ። አኔ በአጥማጆች ወጥመድ እንደምትያዝ እንደ ትንሽ ወፍ ነኝ። የእንተ ምሕረት ካልከበበኝ፣በጠላቶቼ እጀት ውስጥ እወድቃለሁ። አንድ አጥማጅ ሲይዘኝ ከቻለ ብዙት ያላቸው አጥማጆች ምነኛ ይይዙኝ!!

† † †

እርሱ ከመኝታ በፊት በሚደረሰው ጸሎት ውስጥ በሚገኘው መዝሙሮም እንዲህ ብሏል፡- «በቃሉ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፣ በቃሌ ወደ እግዚአብሔር ለመንሁ። ልመናዬን በፊቱ አፈስሳለሁ፣ መከራዬንም በፊቱ አናገራለሁ። ነፍሴ በውስጤ ባሰቀች ጊዜ መንገዴን አውቅህ፣በምሄድባት በዚያች መንገድ ወጥመድን ሰውሩብኝ። ወደ ቀኝ ተመለከትሁ አየሁም፣የሚያውቀኝም አጣሁ፣ መሸሸጊያም የለኝም፣ስለ ነፍሴም የሚመራመር የለም። አቤቱ ወደ አንተ ጮኽሁ፡- . . .» መዝ 141:1-5።

† † †

ይህ ጸሎት በሥቃይ ውስጥ ያለች ነፍስ ጩኼት ነው። በፊት ለፊቱ የጠላት ወጥመድ ስላለ ማምለጫ የለም፣ስለዚህ ጉዳይ የሚጠይቅም ማንም የለም። ብቸኛ አርዳታው እግዚአብሔር ነው።

በመሆኑም የቅዱሳን መንገድ ቀላል አልነበረም። ብዛት ባላቸው የጠላት ጥቃቶች፣ ተቃውሞዎች፣ ችግሮችና ሥቃዮች ስለ ተጨናነቀ መንገዱ አስቸጋሪ ደኻም ጠባብ ነው። ይኸው ዳዊት በዚያው ተመሳሳይ መዝሙር ውስጥ ወደ እግዚአብሔር «አቤቱ ወደ አንተ ተማልጄያለሁና፣ከጠላቶቼ አድነኝ።» (መዝ 142:9) በማለት ጮኼል። እዚህ ላይ የእርሱን ድካምና የጠላቶቹን ብርታት አስታውቋል። በመሆኑም ጌታ ሆይ ወደ አንተ እጮኻለሁ ብሏል። እርሱ እና እኔ እየጮኽን. . . ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ በማለት እንጮኻለን።

† † †

እግዚአብሔር እርሱን ንጉሥ አድርጎ ቢቀባውም መንግሥቱ ሥልጣን፣ ታላቅነትና ክብር በመሆን አላዳነውም፣ይልቁንም እንዲህ በማለት ተናገረ፡- «የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው፣ እግዚአብሔርም ከሁሉ ያድናቸዋል።» መዝ 33:19።

ዳዊት በሁሉም አቅጣጫ ለከበቡት ለእነዚህ ሁሉ መከራዎች የሚገባውን ነገር አድርጓል። እርሱ በሕይወቱ ውስጥ ለገጠሙት ብዙት ሳላቸው ጠላቶቹም የሚገባውን ነገር አድርጓል። በመሆኑም እነርሱን

አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ አለ፡- «በክንቱ የሚጠሉኝ ከራሴ ጠጕር በዙ፤ . .» መዝ 68:4።

† † †

እንዲህ ያለው ጉዳይ በሚጠሉህ ሰዎች ጥላቻና ለእንተ ባላቸው መጥፎ ስሜት ሲቆም ይችላልን? አይችልም፣ ይልቁንም ጥላቻቸው ወደ ጥቃት ተሸጋገረ እንጂ። በመሆኑም እንዲህ አለ፡-

«ኃጢአተኞች በጀርባዬ ላይ መቱኝ፣ኃጢአታቸውንም አስረዘሙት።» መዝ 128:3።

በእግዚአብሔር ፊት እንደ ደካማ ሰው የቆመው ዳዊት ይህ ነው። ጠላቶቹ እጅግ የተስራሩ ነበሩ. . . እርሱ በብርታት እንደ እነርሱ አልነበረም. . . ቁጥራቸውም ከእርሱ የራስ ፀጕር የበዙ ነበሩ። እርሱን አሳድደውታል ኃጢአታቸውንም አስረዝመውብታል። እነርሱ ጀርባውን መምታት ከጀመሩ ረዥም ጊዜ አስቆጥረው ነበር . . . በእርግጥም እርሱ በእግዚአብሔር ፊት ደካማ ሆኖ በመቆም «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ፤ . .» ብሎ የእርሱን እርዳታ ጠይቋል።

† † †

እርሱ በተታውሞ ከሚያሳድዱት ከእነዚህ ኃጢአተኞች በታች በነበረ ጊዜ ሙሉ እምነት ነበረው። በነበረው ልምድም እግዚአብሔር አምላክ የእነርሱን ኃይል በመርታት ከእነርሱ እንደሚያድነው ያውቅ ነበር። በመሆኑም፡-

«እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፣የኃጢአተኞችን አንገታቸውን ቆረጠ።» (መዝ 128:4) አለ።

እርሱ እንዲህም ብሎ ነበር፡- «የኃጥአን በትር በጻድቃን ዕጣ ላይ አይኖርም።» መዝ 124:3። እነርሱ ለኃጥአን በትር የተጋለጡ ቢሆኑም በትሩ በእነርሱ ላይ አያርፍም። ይህን ግለትም እግዚአብሔር በቆይታ በመካከል ስለሚገባና በትሩን ስለሚያስወግደው ጉዳዩ በዚህ ዓይነት መልክ አይቀጥልም ማለት ነው።

† † †

ለመሆኑ እግዚአብሔር ይህን በትር የሚያስወግደው መቼ ነው? እግዚአብሔር አምላክ ኃጢአተኞች ኃጢአታቸውን በማስረዘም መራሩን ሕማም እስከሚያመጡብትና ወደ እርሱ፤«መቼ ታጽናናኛለህ እያልሁ፣ ዓይኖቼ ስለ ቃልህ ፈዘዙ። . . . በሚያሳድዱኝስ ላይ መቼ ትፈርድልኛለህ?» (መዝ 118:82እና84) በማለት እስከሚጮኽ ድረስ ነው። እርሱ እንዲህ በማለትም ጮኽ ነበር፡-

«ከምድር ሊያጠፉኝ ጥቂት ቀርቶአቸው ነበር፤ . .» መዝ 118:87።

ይህ በሴላ ትርጓሜ «ሰጥቂት ጊዜ ያህል እነርሱ በምድር ላይ አጥፍተውኝ ነበር።» ተብሎ ተተርጕሟል።

ይህ ሰው በመዝሙሩ «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ፤ . .» በማለት የጮኸው ዳዊት ነው።

† † †

ነቢዩ ዳዊት በመዝሙራቱ ውስጥ ድካሙን አስመልክቶ የተናገራቸውን ቃላት ስትሰሙ በእናንተ ሕሊና ውስጥ ምን ዓይነት ተመስጦ ተፈጠረ?

በመንፈሳዊ ውጊያዎቻቸሁ ውስጥ ርኩሳን መናፍስት እናንተን በመቃወም ኃጢአቶቻቸውን ሲያስረዝሙባችሁ ስለዚህ ኃይላቸው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ!

የሰይጣን ሠራዊት ያለ ምንም ምክንያት አናንተን አያሳድዷችሁም፣ኃጢአቶቻቸውን አያስረዝመባችሁም፣ሊያጠፏችሁም ጥቂት አይቀራቸውም። መውደቃችሁን የሚመኙና ነፍሳችሁን ማጥፋት የሚሹ መጥፎና የሚጫኑ አሳቦች ሲመጡባችሁ ጮኹ! በዚህ ጊዜም «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ፤ . .» በሉ።

ልትቋቋሙት በማትችሉት ኃጢአት ስትወድም ሆነ ልታመልጡት የማትችሉት ችግር ውስጥ ስትገቡ ከነቢዩ ዳዊት ጋር ሆናችሁ «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ፤ . .» በሉ።

† † †

ዳዊት በታላቅ ኃጢአት ምክንያት ከወደቀ በኋላ (2ኛ ሳሙ 11) ድካሙ ይበልጥ ተሰምቶት ነበር። በመጀመሪያ ስለ እርሱ «. . . ጽኑዕ ኃይል ነው፤ . .» (1ኛ ሳሙ 16:18) ተብሎ ተነግሮ ነበር። ሴቶች እየዘመሩ፣ እየዘፈኑ፤ አልልም እያሉ በክብርና በአታም ሲቀበሉት ሲወጡ «ሳኦል ሺህ፣ዳዊትም አልፍ ገደለ. . .» (1ኛ ሳሙ 18:6-7) በማለት እየተቀባበሉ ዘፍንውለት ነበር። ከዚህ በኋላ የተሸነፈው ግን በሺዎች ወይም በአሥር ሺዎች አይደለም፣በእንጂት ሴት ብቻ እንጂ። እርሱ በኃጢአት ውስጥ ወድቋል።

በእርግጥ ኃጢአት ቢጥለውም ልክ እንደዚሁ ከመውደቁ ተጠቅሟል ብለን መናገር እንችላለን።

በመሆኑም በታላቁ መዝሙሩ (መዝ 118) ውስጥ እንዲህ ሲል እናገኘዋለን፡- «ሥርዓትህን እማር ዘንድ፣ያስጨነቅኸኝ መልካም ሆነልኝ።» መዝ 118:71። እርሱ ያገኘው መልካም መንፈሳዊ ነገር ምንድር ነው?

ከምንም በላይ ደካማ መሆኑ ታወቀው። ይህ ደግሞ ድንቅ የነፍስ ትሕትና ነው። በመሆኑም በስድስተኛው መዝሙሩ ውስጥ «ድዉይ ነኝና አቤቱ ማረኝ፤. . .» አለ። እኔ ደካማ ስለ ሆንሁ የእግዚአብሔር እርዳታ ያስፈልገኛል።

«ነፍሴም እጅግ ታወከች፤. . .» ብሏል።

ከዚህ በኋላ ምንድር ነው ያለው? አዎን፣እንዲህ ነው ያለው ...

«አጥንቶቼም ታውከዋልና ፈውሰኝ። ነፍሴም እጅግ ታወከች፤...»

ኃጢአትና ውጤቶቹ በሥጋና በነፍስ ላይ ተጽዕኖ ስለሚያሳድሩ እርሱ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ሕይወቱ ታማሚ ሆኖ ነበር። እርሱ ሰውነቱን አስመልክቶ ሲናገር «አጥንቶቼም ታውከዋል . . .» ብሏል። ገላችን ቢንቀጠቀጥ ይህ ቀላል ጉዳይ ነው። ብርቱና ጠንካራ የሆኑት አጥንቶች ታወኩ ማለት ግን መላው አዕማዊ አቋማችን ተናጋ ማለት ነው። ይህ የሚያሳየንም መላው ሰውነት በጥፋት አፋፍ ላይ መሆኑን ነው።

ዳዊት ያለው ሰውነቴን ብቻ አይደለም፣«ነፍሴም እጅግ ታወከች፤» እንጂ።

† † †

የሚያውክ ነፍስ ለኃጢአት ደስታ ማካካሻና የመልስ ምት ነው፣ሰውየው ነፍሱን ያገኛታልና።

ኃጢአት ሰሥጋ ምኞት የሚሆን ቀላል እርካታ አይደለም፣ወደ ኋላ በነፍስ ላይ ከባድ የመልስ ምት የሚያስከትል እንጂ። ነቢዩ ናታን ለዳዊት «. . . ያ ሰው አንተ ነህ። . . . አሁንስ በፊቱ ክፉ ትሠራ ዘንድ የእግዚአብሔርን ነገር ለምን አቃለልህ? . . . ነገር ግን በዚህ ነገር ለእግዚአብሔር ጠላቶች ታላቅ የስድብ ምክንያት አድርገሃልና. . .» (2ኛ ሳሙ 12:7፣9እና14) ባለው ጊዜ አንቀላፍቶ የነበረው ሕሊናው ነቅቷል።

በመሆኑም የኃጢአቱን ጥልቀት ሲያውቅ ነፍሱ መጮኸና ማልቀስ ጀመረች. . . ሌላው ቢቀር እንኳ እንዲህ ብላ ጮኻለች፡- «በጭንቀቴ ደክሜያለሁ፤. . .» (መዝ 6:6)

እስከ መቼ?

ዳዊት በዚህ ብቻ አላበቃም፣በነፍሱ መታወክ ጥልቀት ውስጥ ሆኖ እንዲህ አለ እንጂ. . .

«አንተም አቤቱ፡- እስከ መቼ ድረስ ነው? አቤቱ÷ ተመለስ ነፍሴንም አድናት÷ ስለ ቸርነትህም አድነኝ።» መዝ 6:3-6።

«አድነኝ» የሚለው አገላለጽ እርሱ በገዛ ራሱ አመለካከት እንደ ሞተ መሆኑንን ነው። በእርግጥም በዚህ ለማለት የፈለገው ሞራላዊውንና ሞት እና መንፈሳዊውን ሞት ነው። ልክ የጠፋው ልጁ ከጠፋበት በተመለሰ ጊዜ አባቱ «. . . ይህ ልጄ ሞቶ ነበረና ደግሞም ሕያው ሆኖአል. . .» (ሉቃ 15:24) በማለት እንደ ተናገረው ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላክም በሰርዴስ ላለው መልአክ (የቤተ ክርስቲያን አለቃ) እንዲሁ ብሎታል፡- «. . . ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ፣ሞተህማል።» ራእ 3:1።

በመሆኑም ዳዊት ራሱን የገለጸው ደካማ፣ ሕመምተኛ፣ አጥንቶቹ የታወኩ፣ የተናወጠ፣ የተረበሸ፣ የተጨነቀ፣ የሚያለቅስና የሞተ. . . አድርጎ ነው።

† † †

እግዚአብሔርም የእርሱ ጽዋ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ስለ ተወው ነፍሱ ለኃጢአት ተገዝታ ነበር።

በመጨረሻም በፊቱ የተጋረደው ነገር ስለ ተወገደ ዐይኖቹ ተከፈቱ። ስለ ራሱ እውነት የሆነው ነገር ማለትም እርሱ በራሱ ፊት ምንም አለመሆኑ ታወቀው. . . ራሱን የተመለከተው ደካማ፣ ሕመምተኛና የእግዚአብሔርን ምሕረት የሚፈልግ አድርጎ ነበር። አሁን የነበረባቸው ሁኔታዎች ተቀይረዋል. . . ከዚህ ጀግና ሰው የፊት ገጽታ ላይ ሽፋኑ ተወግዷል. . . «ነገር ግን የሰው ልጆች ከንቱ ናቸው፣የሰው ልጆችም ሐሰተኞች ናቸው፣በሚዛንም ይበድላሉ፣እነርሱስ በፍጹም ከንቱ ናቸው።» መዝ 61:9። ያ ታላቅ ጀግና ሰው ወዴት ነው ያለው?! እርሱ በቤተ መንግሥቱ ሰገነት ላይ ቆሞ ዐይኖቹን ወደ ጎረቤቱ በመወርወር ተራ እይታ ስለ ተመለከተ መላው እርሱነቱ ወድቋል፣2ኛ

ሳሙ 11:2። በእውነትም እርሱ ምንም አይደለም ነበር. . . «ሕያው የሆነ ሰው ሁሉ በእውነት ከንቱ ብቻ ነው።» መዝ 39:5እና11። በተራ እይታ ብቻ. . .!!

† † †

የጦር ሰው የሆነው ያ ጀግና ወዴት ደረሰ?! የዋሽንትና የበገና ሰው የሆነው ወዴት ደረሰ?! እርሱ በገናውን ሲደረድር በሳኦል ላይ ሰፍረው የነበሩትን ርኩሳን መናፍስትን ሲያስወጣ የነበረው ሰው ወዴት ደረሰ?! እኛ ከእርሱ የመዝሙራት ጸሎቶች እስከ ዛሬ ድረስ ትምህርት የምናገኝበት ያ የጸሎት ሰው ወዴት ነው ያለው?! ወዴት?. . . ወዴት?. . . ወዴት?. . . በእርሱ ዘንድ የቀሩት የታወኩ አጥንቶች፣ የተጨነቀች ነፍስ እና «አንተም አቤቱ፡- እስከ መቼ ድረስ ነው? አቤቱ÷ ተመለስ ነፍሴንም አድናት፤. . .» በማለት የሚጮኽ ድምፅ ብቻ ናቸው።

በዚህ ውስጣዊ ድካምና በሚውጥ ዝዝን ውስጥ የምቆየው እስከ መቼ ድረስ ነው? ይህን የዛለ ልቦና እና ይህን እፍረት በእኔ ዘንድ የሚኖረው እስከ መቼ ድረስ ነው? የኃጢአት ትዝታዎች ረብሸውኛል . . . እንደዚህ የምትተወኝ እስከ መቼ ድረስ ነው? አቤቱ፡- ተመለስ ነፍሴንም አድናት። የማዳንህን ደስታ ስጠኝ. . . «በሂሶጵ እርጨኝ እነጻማለሁ፣እጠበኝ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ።» መዝ 50:8። ስለ ቸርነትህም አድነኝ።

† † †

«ነፍሴም እጅግ ታወከች፤» ይህን ማለት ውስጣዊ ሰላሙን አጥቷል ማለት ነው።

ኃጢአት በውስጡ ፈጽሞ ሰላም ሊኖረው አይችልም. . . እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ ብሏል፡- «ለክፉዎች ሰላም የላቸውም . . .» ኢሳ 48:22። ዳዊት ሆይ፡- ውዳሴዎችህና መዝሙራትህ የት ነው ያሉት?! ያ ድንቅ በገናህ ወዴት ነው ያለው? . . . «በአኻያ ዛፎችዋ ላይ መሰንቆቻችንን ሰቀልን። . . . የእግዚአብሔርን ዝማሬ በባዕድ ምድር እንዴት እንዘምራለን?» መዝ 136:2እና4። ኃጢአት ከእግዚአብሔር በመለየት በባዕድነት እንድቀመጥ አድርጎኛል. . .

† † †

«ነፍሴም እጅግ ታወከች፤» በእርግጥም የነፍስ ሕመም ከሥጋ ሕመም እጅግ የበረታ ነው።

በመሆኑም «አቤቱ፣ተመለስ ነፍሴንም አድናት፤» በማለት ወደ እግዚአብሔር ጮኺል። አንተ ወደ አንተ መልሰኝ እንጂ እኔ ወደ አንተ መመለስ አልችልም. . . የእኔ ድኅነት በአንተ እጅ ስለሆነ አድነኝ. . . ልታጽናናኝ የምትችለው አንተ ብቻ ነህ። «አንተን ብቻ በደልሁ፣በፊትህም ክፋትን አደረግሁ፤. . .» ያልሁትን በሚገባ አውቃለሁ። ስለሆነም ስለ ቸርነትህ አድነኝ።

ዳዊት ወደ ነፍስ ትሕትና በመድረስ ወደ እግዚአብሔር ደርሷል።

እርሱ በእግዚአብሔር ፊት ከቆመ በኋላ ለእርሱ በእውነት በመናገር ከኃጢአት በኋላ የነበረበትን ሁኔታ ገልጦአል፣ ምሕረትንም ከእርሱ ፈልጓል። እርሱ ለጌታው «አቤቱ፡- እስከ መቼ . . .» መዝ 78:5። ጌታዬ ሆይ፡- እኔ ወድቄያለሁ፣አንተ ግን ወዴት ነው ያለኸው?

«ጠላቶቼ ሁልጊዜ፡- አምላክህ ወዴት ነው? ባሉኝ ጊዜ፣ አጥንቶቼን እየቀለጣጠሙ ሰደቡኝ።» መዝ 41:10።

አምላኬ ሆይ፡- እኔ የተፈለገውን ያህል ከአንተ ብርቅም አንተ ግን ከእኔ አትራቅ። እኔ የተፈለገውን ያህል ደካማ ብሆንም ድካሜን የምትረዳው አንተ ብቻ ነህ። እኔ ብወድቅ እንኳ ከውድቀቴ የምታነሣኝ አንተ ነህ። ኃጢአት ቢያጠፋኝም እንኳ ተመለስና ስለ ቸርነትህ ስትል አድነኝ። ጌታዬ ሆይ፡- እንደ እኔ በደል ሳይሆን እንደ አንተ ምሕረት ይሁንልኝ።

እኛ ወደ ዳዊት ልብ በመግባት ስሜቶቹን ልናነብ እንችላለን...

እዚህ ላይ እርሱ «አቤቱ፡- እስከ መቼ ፈጽመህ ትረሳኛለህ?» (መዝ 12:1) አላለም። «አቤቱ፡- ለምን ርቀህ ቆምህ? በመከራም ጊዜ ለምን ትሰወራለህ?» (መዝ 10:1) ብሎም አልተናገረም። ይልቁንም በመዝሙሩ «. . . እስከ መቼ?. . .» ነበር ያለው። ከዚህ በኋላ ዝም ነው ያለው!! ስለ ተሸነፈ ንግግሩን ሊቀጥል አልቻለም. . . አቤቱ ጌታዬ፡- ለመናገር የፈለግሁትን አንተ ታውቀዋለህ. . .

አምላኬ ሆይ፡- እኔ ከአንተ የምጠብቀው የአንተን በመካከል መግባት ነው። አትተወኝ።

አንተ ለደካማ ነፍሴም ሆነ ለብርቱ ጠላቶቼ አትተወኝ። ለታወኩ አጥንቶቼና ለተጨነቀች ነፍሴ አትተወኝ። በመሆኑም ዳዊት «. . . እስከ መቼ?» ይለዋል። ይህን ያለው ጊዜው ረዥም ጉዳዩም ከባድ ስለሆነ ነው። በመሆኑም ዳዊት እግዚአብሔር አስፈልጎታል።

† † †

እውነቱ ነገር ግን እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ በአፋጠኝ መመለሱና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ዘግይቶ መመለሱ ነው!

እርሱ ፈጥኖ በመመለሱና ዘግይቶ በመመለሱ ውስጥ የራሱ የሆነ ጥበብ አለው።

ፈጥኖ መመለሱን በተመለከተ እርሱ በትንቢተ ኢሳይያስ የትንቢት መጽሐፍ ውስጥ ድንቅ የሆነ ምሳሌውን አስነብቦናል፦ «. . . ሳይጠሩ አመልስላቸዋለሁ፣ገናም ሲናገሩ አሰማለሁ።» ኢሳ 65:24። በእርግጥም ይህ አስደናቂ ነገር ነው። እግዚአብሔር አምላክ እርሱን ከመጠየቃችን በፊት ብዙ ጊዜ መስጠቱ ግን ለእኛአንግዳ ነገራችን አይደለም።

«. . . ገናም ሲናገሩ አሰማለሁ።» ማለቱም በመናገር ላይ ያሉትን ከመጨረሻው በፊት አሰማቸዋለሁ ማለቱ ነው። እኔ እንደበት ከመናገሩ አስቀድሞ በልብ ውስጥ ያለውን አሰማለሁ ማለቱ ነው።

† † †

ጌታዬ ሆይ፦ አንተ ፈጥነህ የምትሰማው ኃጢአት ያልሠሩትን ወይም በሥራቸው ያላሳዘኑህን ጻድቃን ሲሆን ይችላል። እኔ ግን ከእነርሱ መካከል አንዱ አይደለሁም። እኔ ፊቴን ወደ አንተ ተና ለማድረግ የማፍር ሰው ነኝ። ስለሆነም አጥንቶቹ ያውኩኛል ነፍሴም ክፉኛ ታስጨንቀኛለች። አንተ እኔን የታገሥኸኝ በዚህ ምክንያት ነው። አቤቱ፦ ግን እስከ መቼ ድረስ?

ጻዲት ሆይ፦ ምናልባት እኔ ከወይኖችህ ውስጥ ጨምቄ የማወጣቸው የእንባ ዘለላዎች ተከማችተው ሲሆን ይችላል። ምናልባትም አንተ ገና ያላስወጣኻቸው የሲቃ ድምፆች ሲኖሩ ይችላሉ . . . ንስሓህ ሙሉ ይሆን ዘንድ የሚያስፈልገህ ጥቂት ፀፀቶች ሲኖሩ ይችላሉ። አንተን የታገሥሁህ በእነዚህ ምክንያቶች ሲሆን ይችላል. . . የታገሥሁህ «ሉጲቴን ሁሉ አልጋዬን እጥባለሁ፣ በዕንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ።» (መዝ 6:6) እስከምትል ድረስ ይሆናል።

አቤቱ፦ እስከ መቼ ድረስ? እስከ መቼ ድረስ ነው ጠላቶቼ እያስጨነቁኝና እያጠቁኝ የምቀጥለው? መዝ 41:9። የሚያስጨንቁኝና የሚያሳዝኑኝ ነፍሴን፦ «እምነትሽ አያድንሽም አልዋት።» መዝ 3:2። ጻዲት ሆይ፦ ምክንያቱ ግን አንተ ነህ።

† † †

እግዚአብሔር አምላክ ምንጊዜም ቢሆን በመካከል ጣልቃ የሚገባው በተገቢው ጊዜ ነው። ምናልባት እኛ ግን ዘገየ ወይም ጉዳዩ ይህ አልነበረም ብለን እናስብ ይሆናል።

አቤቱ፦ ተመለስ ነፍሴንም አድናት!
ተመለስ ነፍሴንም አድናት!

ጻዲት የእግዚአብሔርን መመለስ ስለሚጠይቅ ብቻውን መሆኑ ታውቆታል ማለት ነው። እግዚአብሔር ከእርሱ አንደ ራቀ፣ ከእርሱ አንደ ተለየና እርሱ ለእግዚአብሔር ባዕድ አንደ ሆነ ታውቆታል። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር አንደማይሠራም ታውቆታል።

በመሆኑም ተመለስ ነፍሴንም አድናት! አለ። የታወኩ አጥንቶቼ አንዳሉ ይሁን፣የሚያውከኝ ሰውነቴ አይደለምና። ከሚገባው በላይ የምታስጨንቀኝ ነፍሴ ናት። እናም ጥቂት ስለምና ጥቂት መደላደል ስጣት፣ነፍሴንም ባለችበት የተጨናነቀ ሁኔታ ውስጥ አትተዋት።

ጻድቁ ኢዮብ በተፈተነ ጊዜ ሰለይጣን ፈቃድ የሰጠኸው ሥጋውን ብቻ እንዲመታ ነበር። የኢዮብን ነፍስ በተመለከተ ግን ሰይጣን ሜጯን እንዳይነካ አግደኸዋል. . . ኢዮ 2:6። የእኔ ነፍስ ግን ክፉኛ ተጨንቃለች. . . ስለሆነም ተመለስ ነፍሴንም አድናት!

† † †

ጻዲት ለእግዚአብሔር እንደ ባዕድ ሆኗል፣ብቸኝነትም ተሰምቶታል። በመሆኑም እርሱን እንዲህ የሚለው ነው የሚመስለው፦

አቤቱ ጌታ ሆይ፦ የመጀመሪያ ፍቅርህ ወዴት ደረሰ? የቆየው ማጽናናትህስ ወዴት ነው ያለው? ፊትህ የት ነው ያለው? ፊትህን ከእኔ በመመለስህ እኔ የምጨነቀው ለምንድር ነው?

ምናልባት ይህ ኢዮብም መከራ ውስጥ በገባ ጊዜ የተሰማው ስሜት ሊሆን ይችላል። በመሆኑም እንዲህ አለ፦ «እግዚአብሔር ይጠብቀኝ እንደ ነበረው ጊዜ፣እንደ ፊተኛው ወራት በሆንሁ! በራሴ ላይ መብራቱ በበራ ጊዜ፣እኔም ጨለማውን አልፌ በብርሃኑ በሄድሁ ጊዜ! . . . እግዚአብሔር ድንኳኔን በጋረደ ጊዜ!. . . መንገዴ በቅቤ ይታጠብ በነበረ ጊዜ፣ድንጋዩ የዘይት ፈሳሽ ያፈስስልኝ በነበረ ጊዜ።» ኢዮ 29:2-6።

በመሆኑም ጻዲት አቤቱ ተመለስ አለ. . .

ከእኔ ጋር ወዳለህ ግንኙነት ተመለስ!ቀደም ሲል እኔን ከወንድሞቼ መካከል እንደ መረጥህባቸው ቀኖች። በዚህ ጊዜ አንተ

ነዚዩ ሳመ-ኤልን ወደ እኔ በመላክ የንግሥናውን ዘይት እንዲቀባኝና መንፈስ ቅዱስ በእኔ ላይ እንዲወርድ አድርገሃል። አሁን ተመለስና ነፍሴን አድናት።

† † †

እርሱ መልሶና መላልሶ የሚናገረው «አቤቱ፦ . . . » እያለ ነው። እርሱ ሌላ ማንንም መጠጊያው ቢያደርግ ናሮ እርዳታ ወይም መደላደል ወይም ተስፋ አያገኝም ነበር።

ይህን ጻዲት ሁልጊዜ የሚያደርገው ሥርዓቱ ነው። እርሱ በሌላ መዝሙሩ ላይ እንዲህ በማለት ተናግሯል፦ «እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፣እኔም በጠላቶቼ ላይ አያለሁ። በሰው ከመታመን ይልቅ በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል። በገዦች ተስፋ ከማድረግ ይልቅ በእግዚአብሔር ተስፋ ማድረግ ይሻላል።» መዝ 117:7-9።

† † †

እርሱ ለእግዚአብሔር «. . . አድነኝ. . . » ይለዋል። ግን ለምን? . . . እንዲህ ይሰናል፦

«በሞት የሚያስብህ የለምና፣በሲዖልም የሚያመሰግንህ ማን ነው?» መዝ 6:5።

አቤቱ÷ ተመለስ ነፍሴንም አድናት፣ስለ ቸርነትህም አድነኝ።

አቤቱ÷ ተመለስ ነፍሴንም አድናት፣ስለ ቸርነትህም አድነኝ።

አምን፣የምታድነኝ ስለ ቸርነትህ ብለህ ነው እንጂ ስለ አስፈላጊነቴ ወይም ስለ ጸሎቴ ወይም ስለ ዕንባዬ አይደለም። አንተ ርኅሩኅና ቸር ስለ ሆነህ ስለ ቸርነትህ ብለህ አድነኝ።

ጻዲት አጥብቆ የያዘው ብርቱውን ምክንያት ሲሆን ይህም የእግዚአብሔር ምሕረት ነው. . .

ጻዲት በንስሓው ጥቅም ላይ የተመካ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ ባለው ነበር፦ አንጻችም የሚገባህ ነገር አይኖርም። ኃጢአትህ እግዚአብሔርን በመቃወም ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ወሰን የለውም። በመሆኑም የተፈለገውን ያህል ንስሓ ብትገባ ንስሓህ ውሱን ነው የሚሆነው . . .

ከዚህ ይልቅ የእግዚአብሔርን ምሕረት አጥብቆ ከያዘ የእግዚአብሔር ምሕረት ታላቅ ነው፣ጻዲትም ይህንን በሚገባ ያውቀዋል። እርሱ ኃጢአት ከሠራና ሕዝቡን ካስቆጠረ በኋላ ከሥስቱ

ቅጣቶች መካከል አንዱን እንዲመርጥ ምርጫው ሲቀርብለት እንዲህ ነበር ያለው፦ « . . . ምሕረቱ ብዙ ነውና በእግዚአብሔር እጅ እንውደቅ፣በሰው እጅ ግን አልውደቅ. . » 2ኛ ሳሙ 24:14።

† † †

እርሱ ለእግዚአብሔር እንዲህ ብሎታል፦ አንተም አቤቱ፦ እስከ መቼ ድረስ ነው?

እርሱ «አቤቱ» የሚለውን ቃል በዚህ መዝሙር ውስጥ አራት ጊዜ ደጋግሞታል። እንዲህ እያለ . . .

«አቤቱ በቁጣህ አትቅሠፈኝ!»
«ድዉደ ነኝና አቤቱ ማረኝ!»
«አንተም አቤቱ፦ እስከ መቼ ድረስ ነው?»
«አቤቱ፦ ተመለስ ነፍሴንም አድናት!»

ጻዲት በዚህ መዝሙሩ መዝጊያ ላይ እንዲህ ብሏል፦ «እግዚአብሔር የልቅሶዬን ቃል ሰምቶአልና። እግዚአብሔር ልመናዬን ሰማኝ፣እግዚአብሔር ጸሎቴን ተቀበለ።» መዝ 6:8-9።

እርሱ አሥር ቁጥሮች ባሉት በዚህ መዝሙር ውስጥ ሰባት ጊዜ ነው ስመ እግዚአብሔርን የጠራው (አቤቱ እና እግዚአብሔር የሚለውን)።

«የእግዚአብሔር ስም የጸና ግምብ ነው፣ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል።» ምሳ 18:10።

እግዚአብሔር አምላክ ምንጊዜም ቢሆን በመካከል ጣልቃ የሚገባው በተገቢው ጊዜ ነው። እኛ ግን ዘገየ ወይም ጉዳዩ ይህ አልነበረም ብለን እናስብ ይሆናል።

እኛ እግዚአብሔር ረስቶናል ወይም ራሱን ከእኛ ሰውሯል ብለን እናስብ ይሆናል። በመሆኑም «አቤቱ፦ እኔን ለማዳን ተመልከት፣አቤቱ፦ እኔን ለመርዳት ፍጠን፣. . . ረዳቴ ታዳጊዬም አንተ ነህ፣አቤቱ፦ አትዘግይ።» (መዝ 69:1እና5) እንላለን። እኛ መዘግየት አድርገን የምንቆጥረው ጊዜ እርሱ ስለ እኛ ሲል የሚሠራበትን ጊዜ የሚጠብቅበት ጊዜ ነው።

ሕዝቡ ከባርነት ቀንበር የተነሣ በሲቃ ሲጮኹ እግዚአብሔር ስለ ተመለከተ ለእነርሱ ርኅራኄውን ገልጠላቸዋል።

ይሁን እንጂ እርሱ ትዕግሥተኛ ስለሆነ አሁን ነጻ አላወጣችሁም በማለት ተናግሮ ነበር። ለምን? እግዚአብሔር አምላክ ይህን ለእርሢም በራሱ በገለጸለት ጊዜ እንዲህ ብሎት ነበር፦ «አንተ

ግን ወደ አባቶችህ በሰላም ትሄዳለህ፤በመልካም ሽምግልና ትቀበራለህ። በአራተኛው ትውልድ ግን ወደዚህ ይመሰሳሉ፤ የአሞራውያን ኃጢአት ገና አልተፈጸመምና።» ዘፍ 15:15-16። በጠላቶችህ ላይ የተነሣው የቁጣ ጽዋ ገና አልሞላም። ጊዜው በደረሰ ጊዜ ግን በዐይኖችህ ፊት አበትናቸዋለሁ፤ይህ ለእነርሱ ትክክለኛና ተገቢ ነገር ነውና። በመሆኑም፦ «. . . ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።» ሮሜ 8:28።

እኛ ግን እንዲህ እንለዋለን፦ አቤቱ፦ እስከ መቼ ድረስ ነው? ምክንያቱም እርሱ እንደሚመጣ ሙሉ እምነት አለን ማለት ነው. . .

እርሱ ከሌሊቱ በአራተኛው ክፍለ ጊዜም ሆነ (ማቴ 14:25) አልዓዛር በሞተ በአራተኛው ቀን ይመጣል (ዮሐ 11:27) ይመጣል. . . «. . . አምን፤በቶሎ እመጣለሁ ይላል።» ራእ 22:20። ስለሆነም፦ «እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፤በርታ፦ ልብህም ይጽና፤ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።» መዝ 26:14። እግዚአብሔርን ተስፋ የምታደርገው በዛሬች ነፍስ አይደለም፤በመልካም ድፍረት እንጂ። በእምነትህ የበረታህና የጸናህ ሆነህ ተስፋ አድርገው።

† † †

ዳዊት መዝሙሩን ቀጥሎ ሲናገር እንዲህ ነው ያለው፦

በሞት የሚያስከህ የለምና፤. . .

ዳዊት በኃጢአትና በድካም መካከል ሞትን ማስታወስ ጀምሯል። ሞትን ማስታወስ ጠቃሚ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም . . .

እርሱ ከመሞቱ በፊት እግዚአብሔር እምላክ በመንፈሳዊነት በድጋሚ እንደሚያስነሣው እርግጠኛ እንዲሆን ፈልጓል። ብዙ ሰዎች መሞት እንደሚፈልጉ ይናገራሉ። ዋናው ቁም ነገር ግን ሰውየው ከመሞቱ በፊት ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታው ምን እንደሚሆን ማረጋገጡ ላይ ነው። ይህ ሰው ከሞተ በኋላ ወዴት እንደሚሄድ ለማወቁ እርግጠኛ መሆን አለበት!

† † †

ሞትን የሚመኘው ማነው? ይህን ማለት የሚችለው ሰው ከሐዋርያው ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ሆኖ እንዲህ ብሏል፦ «. . . ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፤ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፤. . .» ፊልጵ 1:23።

ቅዱስ ጳውሎስ ከሞት በኋላ ከክርስቶስ ጋር እንደሚሆን አውቋል። ከእርሱ ጋር የሚኖረውም በገነት ውስጥ ነው፤ሉቃ 23:43። ስለሆነም ይህ የሚሻል ነገር መሆኑን ተመልክቷል ማለት ነው።

ዳዊትን በተመለከተ ግን እርሱ ሞትን ፈርቶት ነበር። ይህ ስለሆነ ነው «በሞት የሚያስብህ የለምና፤በሲኦልም የሚያመሰግንህ ማን ነው?» በማለት የተናገረው።

እኔ ከመሞቴ በፊት አንተን አሁን ላስታውስህና ለአንተ ምስጋና ለማቅረብ እወዳለሁ።

«በሲኦልም የሚያመሰግንህ ማን ነው?» የሚለው አገላለጽ በኃጢአት ለሞቱት የሚሰጠው ትርጉም ምንድር ነው?

ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «. . . በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤. . . በፊት ተመላለሳችሁባቸው።»

በመሆኑም ዳዊት፦ አድነኝ. . . በሞት የሚያስከህ የለምና አለ።

እኔ በአንተ ሕያው እንደምሆን ከሞት ይሻውም ከኃጢአት ሞት አድነኝ፤የዚህ ኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ሮሜ 6:3።

እኔ በአንተ ውስጥ ሕያው ከሆንህ ለዘለዓለም እኖራለሁ፤ከሞት ውስጥ አንተን ማስታወስ የለምና። በዚህ ምድር ላይ በኃጢአታቸው ሙታን የሆኑ ሰዎች አንተን አያስታውሱህም፤ እነርሱን ከአንተ የለዩአቸው ሌሎች ጉዳዮች አሉና። እነዚህ ሰዎች ወደ ሲዖል ሲወርዱም ለአንተ ምስጋና ሊያቀርቡ አይችሉም።

† † †

እዚህ ላይ የሞት ዓይነቶችን መጥቀስ እንችላለን።

የመጀመሪያው ሞት የሥጋ ሞት ሲሆን ይህም የነፍስ ከሥጋ መለየት ነው።

ሁለተኛው ሞት የሞራል ሞት ነው። ይህ ሞት መለኮታዊውን ገጽታ የሚያሳጣና የእግዚአብሔርን ልጆች ከዓለም ልጆች የሚለየውን መንፈሳዊ ተፈጥሮ የሚያሳጣ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር «የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው፤. . .» (1ኛ ዮሐ 3:10) ብሏል።

ሦስተኛው ሞት መንፈሳዊ ሞት ሲሆን ይህም መንፈስ ከእግዚአብሔር የሚለይበት ሞት ነው። ይህም ሐዋርያው ቅዱስ

ጳውሎስ «በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ. . .» (ኤፌ 2፡1እና5) በማለት የተናገረው ሞት ነው።

አራተኛው ሞት ዘላለማዊው ሞት ወይም ዘላለማዊው ጥፋት ሲሆን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ሞት ውስጥ ያለውን የክፋዎች ዕጣ ሲገልጸው እንዲህ ብሏል፦ «. . . እናንተ ርጉማን ሰለይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ።» ማቴ 25:41እና47። ይህ ደግሞ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ቀንና ሌሊት ይለቃዩበት ዘንድ ወደ ተዘጋጀው ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ የሚጣሉበት ሞት ነው፤ራእ 20:10። «. . . በውሸ ወዳለው ጨለማ አውጡት፤በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።» ማቴ 25:30።

† † †

❖ ዘላለማዊውን ሞት በመሞት ስለሚጠቃለሉት ሰዎች መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር «. . . በኃጢአታችሁም ትሞታላችሁ፤እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም. . .» (ዮሐ 8:21) ብሏል። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን አላስታወሱም ምስጋናም ለእርሱ አላቀረቡም። እነርሱ ከእግዚአብሔርና ከቅዱሳኑ ኅብረት ውጪ ባለው ጨለማ ውስጥ ናቸው ይህም እሳቱና ዲኑ ያለበት ባሕር ነው።

❖ በሞራል ወይም በመንፈሳዊው ሞት ውስጥ ያሉትም እግዚአብሔርን አያስታውሱም ለእርሱም ምስጋና አያቀርቡም፤ በኃጢአት ሕይወት ውስጥ ናቸውና። እነርሱ በምድር ላይ ሳሉ የንስሓ ዕድል በፊታቸው ነበር። እነርሱ ንስሓ ቢገቡ ኖሮ የጠፋው ልጅ አባት የተናገራቸው ቃላት ለእነርሱም ተስማሚ ይሆኑ ነበር፦ «. . . ይህ ልጄ ሞቶ ነበረና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፤ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም።» ሉቃ 15:24። ንስሓ ለእነርሱ የሚቆጠረው ከሙታን መካከል እንደ መነሣት ነው፤ለዚያውም ከኃጢአት ሞት።

❖ የሥጋን ሞት በተመለከተ እንደ ዓይነቱ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኛ መንገድ ነው። አንድ ሰው በኃጢአት ውስጥ ሳለ ቢሞት «በሞት የሚያስብህ የለምና፤. . .» የሚለው አገላለጽ ለእርሱ ይስማማዋል።

† † †

ይሁን እንጂ በጽድቅ ሥራው ውስጥ ሳለ ቢሞት «ለአገልጋዮችህ ሞት የለባቸውም፤ዕረፍት እንጂ።» የሚለው የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ለእርሱ ይስማማዋል።

እነርሱ በሞታቸው ውስጥ እግዚአብሔርን ያስታውሳሉ ምስጋናም ለእርሱ ያቀርባሉ።

እነርሱ በመጀመሪያ ከእርሱ ጋር በገነት ይሆናሉ ከዚያም በመንግሥተ ሰማያት።

በእርግጥም እነዚህ ከሞት በኋላ ሕያው የሚሆነውን ምስጋና በመንፈስ ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ። ሥጋ ግን ወደ አፈርነት ይለወጣል። በእነዚህ ሙታን ሰውነት ውስጥ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ምስጋና አይኖርም። ይህ ሲሆን የሚችለው መንፈሳዊና ሰማያዊ አካል ይዘው ከሚነሡበት ትንሣኤ በኋላ ነው፤1ኛ ቆሮ 15:44እና49። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔርን ያስታውሳሉ ለእርሱም ምስጋና ያቀርባሉ፤ ከመንፈሳቸው (ከነፍሳቸው) ጋር ከተዋሀዱ በኋላ።

† † †

በጽድቅ ውስጥ ያለው ይህ ሥጋዊ ሞት ቤሐዋርያው ተወድሷል፤ እርሱ ስለዚህ ሞት ሲናገር እንዲህ ብሏልና፦ «ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፤ሞትም ጥቅም ነውና።» ፊልጵ 1:21። እርሱ እንዲህም ብሏል፦ «እንግዲህ ሁልጊዜ ታምነን በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና፤በሥጋ ስናድር ከጌታ ተለይተን በስደት እንዳለን የምናውቅ ከሆንን፤ታምነናልና ይልቁንም ከሥጋ ተለይተን በስደት መኖር በጌታም ዘንድ ማደር ደስ ይለናል።» 2ኛ ቆሮ 5:6-8።

እርሱ በሞት ይደሰታል፤ከሥጋው ተለይቶ ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚሆን።

እናንተም በጸሎት ውስጥ ስትሆኑ ከመሞታችሁ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለመፍጠር ሞክሩ።

† † †

ዳዊት ስለ ሞት እንዲሁም ሙታን እርሱን እንደማያስታውሱትና ለእርሱ ምስጋና ማቅረብ እንደማይችሉ ከጠቀሰ በኋላ ለእግዚአብሔር «በጭንቀቴ ደክሜያለሁ፤» ነው ያለው . . .

«በጭንቀቴ ደክሜያለሁ፤ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ፤»

እርሱ የተጨነቀው (ያቃሰተው) በመቸገር ነው። በእርግጥም የሚያቃስት ሰው ብዙ ካቃሰተ በኋላ ይደክማል፤በዚህ ዓይነት ሁኔታም ሊቀጥል አይችልም. . .

በአንድ ወቅት ዳዊትና ሰዎቹ አማሌቃውያን የጺቅላግን ከተማ አቃጥለው በውስጧ ያሉትን ሰዎች በሙሉ ማርከው ከወሰዱ በኋላ ሊደርሱ ያለባት ሁኔታ እጅግ አሳዛኝ ነበር፦ «ዳዊትና ሰዎቹም ወደ ከተማ በመጡ ጊዜ እነሆ በእሳት ተቃጥላ፤ሚስቶቻቸውም ወንዶችና

ሌቶች ልጆቻቸውም ተማርከው አገኘ። ዳዊትና ከእርሱም ጋር የነበሩ ሕዝብ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለማልቀስ ኃይል እስከሚያጡ ድረስ አለቀሰ።» 1ኛ ሳሙ· 30:3-4። ይህ ከባድ አገላለጽ ነው· · ·

በእርግጥም አንድ ሰው ከልቅሶው የተነሣ ሊደክምና ለማልቀስ ኃይል እስከሚያጣ ድረስ ሊያለቅስ ልቅሶውን ሊያበረታ ይችላል!!

ዳዊት ያደረገውም ይህንኑ ነው፡- እርሱ ከጭንቀቱ የተነሣ ማቃሰት እስከሚያቅተው ድረስ በኃጢአቶቹ ላይ አቃስቷል። እርሱ ምኞቱንና ማመንዝሩን አስታውሷል። እርሱ ኬጢያዊው ኦርዮ የእርሱን ኃጢአት ይሸፍንለት ዘንድ እንዴት እርሱን ወደ ቤቱ ይሄድ ዘንድ እንዳባበለው አስታውሷል፤2ኛ ሳሙ· 11:10-11። ኦርዮ ግን ከእርሱ የተሻለ ጨዋ ሰው ነበረ። እርሱ ኦርዮ ምን እንደ ተፈጠረ እንዳያውቅ በውጊያው አውድማ ላይ እንዴት መገደል እንዳለበት አሚሯል። በእርግጥም ኦርዮን የገደለው እርሱ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ እርሱ ኦርዮን በማስገደሉ ምንም ግድ አልሰጠውም። ይህም ኦርዮ በግፍ ከተገደለ በኋላ ሰጦር አሰቃው ለኢዮአብ በላከው መልእክት ውስጥ ተረጋግጦአል፡- «· · · ሰይፍ አንድ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜም ያን ያጠፋልና፤ይህ ነገር በዓይንህ አይክፋ፤ከተማይቱን የሚወጉትን አበርታት፤አፍርሳትም፤· · ·» 1ኛ ሳሙ· 11:25።

የዳዊት ልቅሶ

ዳዊት አልቅሷል፤ያለቀሰው ግን ይቅርታን ለማግኘት ሳይሆን ይቅርታን ካገኘ በኋላ ነው!

እርሱ ንስሓውን አቅርቧል፤ንስሓው ደግሞ ኃጢአቱን ይቅር ብሎታል። ይሁን እንጂ ይህ ይቅርታ ኃጢአት መፈጸሙን ከጎሲናው አላጠፋበትም ጉዳዩም በእርሱ ዘንድ አልተጠናቀቀም፤ መንፈሳዊ ውጤቱ ኃጢአቱን ሊረሳ በማይችለው ሰው ላይ ተቀርጾ ቀርቷልና።

ነቢዩ ናታን ለዳዊት የኃጢአቱን ጥልቀት ዘርዝሮ በነገረው ጊዜ «· · · እግዚአብሔርን በድያለሁ· · ·» (2ኛ ሳሙ· 12:13) ስላለ እስቀድም ለፈጸመው ኃጢአቱ ይቅርታ ተቀብሏል። በዚህ ጊዜ ነቢዩ ናታን ለዳዊት እንዲህ ነበር ያለው፡- «· · · እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል፤አትሞትም፡።» 2ኛ ሳሙ· 12:13። ይህም ማለት እግዚአብሔር አምላክ ይህን ኃጢአትህን በልጄ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ያጠፋልህ ዘንድ አስተላልፎታልና ይቅር ትባላለህ፤ አትሞትምም ማለት ነው።

ታዲያ ዳዊት ያለቀሰው ለምንድር ነው?

እርሱ ይህን ሁሉ ኃጢአት ለመሥራት ታች ድረስ ዝቅ በማለቱና በዚህ ውጤት ምክንያት በጎዘን አልቅሷል።

እርሱ እግዚአብሔርን ስላስቆጣው አዝኗል። እርሱ ለንግሥና በተቀባ ጊዜ በእርሱ ላይ የወረደውን መንፈስ ቅዱስ አሳዝኗል። ትሕትናውን፣ ገጽሕናውን፣ ጽድቁንና ቅድስናውን ስላጣ አዝኗል። እርሱ ጨዋ ተፈጥሮውንና መንፈላዊ ሥልጣኑን አጥቷል።

ይቅርታን በተመለከተ ግን ኃጢአቱ ይቅር ተብሎለታል። ይሁን እንጂ በውስጡ «እንዴት ይህን ሁሉ ልታደርግ ቻልህ?! አእምሮዬ ወዴት ነበር የደረሰው?! ሕሊናዬስ ወዴት ነበር?!» የሚሉት ድምጾች ይጮኹበት ነበር። በመሆኑም ኃጢአቱ ሁልጊዜ በፊቱ ነበረ፤መዝ 51። ከእይታውም ሆነ ከትውስታው ፈጽሞ ሳይጠፋ ዘወትር የነበረውን መለኮታዊ ገጽታ እንዳጣው ያሳስበው ነበር፤ከመንፈስ ቅዱስ የተቀበለውን የንግሥና ቅባት በከብር አለመጠበቁንም ያሳስበው ነበር።

በመሆኑም አጥንቶቹ ታወኩ፤ነፍሱ ደግሞ እጅግ ታወከች።

† † †

እንዲህም አለ፡- «ሴሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ፤በዕንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ።» 6:6።

እርሱ አልጋውን በሴሊት እንጂ በቀን በዕንባው ያጠበው ለምንድር ነው?

እርሱ ቀን-ቀን በብዙ ጉዳዮች ተጠምዶ ነበር የሚውለው· · · እርሱ በንግሥና ሥራዎች፤በጦር ኃይሉ ሥራዎች፤በፍርድ ሥራዎች፤ ከሚቀርቡትና ከሚታወሙት ሰዎች ጋር ለመስማማት በሚያከሂዳቸው ሥራዎች ባተሌ ሆኖ ነበር የሚውለው። እርሱ በመንግሥቱ ጭንቀትም ባተሌ ሆኖ ስለሚውል ለኃጢአቶቹ ለማልቀስ ጊዜ አልነበረውም· · · ምናልባትም ይህ ጉዳይ በአሳቡ እንኳ ሳይመጣለት ይችል ይሆናል· · ·

ሴሊት ሲሆን ግን ራሱን ከሥራ ክበብ ውስጥ ሲያርቅ፤ ብቻውን ሲሆንና ለራሱ ጊዜ ሲሰጥ ኃጢአቶቹንና ዕንባዎቹን ያስታውሳል · · ·

† † †

ስለሆነም፡- ሴሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ፤በዕንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ ይላል።

ዳዊት የመኝታዬን ልብስ በዕንባዬ አርሳለሁ ቢለን ኖሮ ተቀባይነት ያለው ጉዳይ ይሆን ነበር፤እርሱ ያለን ግን አልጋዬን አጥባለሁ· · · መኝታዬንም አርሳለሁ ነው።

ይህ የሚያሳየን ዕንባው ማብቂያ የሌለው በመሆኑ የሚያርሰው የመኝታውን ልብስ ብቻ ሳይሆን አልጋው ራሱ በዕንባው ይታጠብ እንደ ነበር ነው· · · ይህ የተለየ ልቅሶ ነው፤ዕንባዎቹ ሰላምና ወሰን አልነበራቸውም· · · እያንዳንዱ የኃጢአቱ ዝርዝር ልቅሶ የሚፈልግ ነበረ፤በመኝታውም ላይ ዘወትር ኃጢአቱን በፊቱ ያየው ነበር፤መዝ 50።

† † †

እምን፤ዳዊት በሴሊት የሚያነባው ዕንባ ይህ ነው፤እርሱ «ልቅሶ ማታ ይመጣል፤» (መዝ 29:5) በማለት ተናግሯል።

እርሱ ከራሱ ጋር የሚያሳልፈው ጊዜ በሥራና ቃል በመግባት ባተሌ ከመሆን የራቀና የሰከነ ነበር· · · በጸሎትና በተመስጦ ውስጥ ሲገባ ኃጢአቶቹንና ዕንባዎቹን ያስታውሳል።

እናንተ የዳዊትን ልቅሶ ስታስታውሱ ራሳችሁን፡- እኔ እርሱ እንደሚያለቅሰው ስለ ኃጢአቶቼ አለቅሳለሁን?! ብላችሁ ጠይቁት።

† † †

ከዚህ በኋላ እርሱ እንዲህ ነው የሚለው፡-

«ዓይኔ ከቍጣው ዕንባ የተነሣ ታወከች፤ከጠላቶቼ ሁሉ የተነሣ አረጀሁ።»

በሌሎች ትርጓሜዎች «· · · ከኀዘን ዕንባ የተነሣ· · ·» ተብሎ ተተረጉሟል። ይሁን እንጂ ትርጉሙ ተመሳሳይ ነው። በእርሱ ላይ መከፋት ሲደርስ ወይም በራሱ ላይ ሲቆጣ ወይም የእግዚአብሔር ቁጣ ሊመጣበት ዐይኖቹ በዕንባ ይታጠባሉ።

ዕንባዎች

በቅዱሳን ውስጥ ስለ ዕንባዎች የተጻፉት ታሪኮች ብዙ ናቸው።

ታላቁ ቅዱስ አርሳኒዎስ የዓይኖቹን ሽፋሽፍት ያጣው አብዝቶ ስለሚያለቅስ ነበር። ይህ ታላቅ ቅዱስ ሰው መዝሙራትን በዕንባዎቹ

ያጥባቸው ነበር። እርሱ ሥራውን ሲሠራ ዕንባዎቹን ለመሰብሰብ ያስችለው ዘንድ በጉልበቶቹ ላይ ፎጣውን ይዘረጋ ነበር። ቅዱስ አርሳኒዎስ ሴሊቱን ሙሉ በጸሎት የሚያሳልፍ የጸሎት ሰው ነበረ። እርሱ አመሻሽ ላይ ፀሐይ ከጀርባው ስታዘቀዝቅ ለጸሎት የቆመ ጉጋት ላይ ተመልሳ በፊቱ ገጽ ላይ እስከምትወጣ ድረስ ይጸልይ ነበር። ታዲያ በዚህ ጊዜ ሁሉ ዕንባውን ያኽ ነበር· · ·

† † †

እኛ ግን ሊቆጠሩ የማይችሉ ብዛት ያላቸው ኃጢአቶችን ብንሠራም ምንም አናለቅስም።

እኛ ለራሳችን ኃጢአቶች ከማልቀስ ይልቅ የእኛ ባልሆኑት የሌሎች ሰዎች ኃጢአቶች ላይ ራሳችንን ባተሌ ስለምናደርግ ዕንባዎቻችንን ያጣናቸው ይመስለኛል።

ወይም ደግሞ እኛ ዕንባዎቻችንን ያጣናቸው ሌሎች ኃጢአቶችን በመፈጸም ባተሌዎች ስለሆንን ነው።

ልቅሶ ራሱን የቻለ ስፋ ርዕስ ስለሆነ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በቀላሉ ልንሸፍነው አንችልም· · ·

† † †

ልነግራችሁ የምፈልገው አስፈላጊና እውነት ነገር ግን ዳዊት እጅግ አብዝቶ ማልቀሱን ነው።

ዳዊት አብዝቶ አልቅሷል· · ·

ዳዊት አብዝቶ ያለቀሰ ሰው ነው· · ·

እርሱ እንዲህ ብሏል፡- «አመድን እንደ እህል ትሜአለሁና፤ መጠጤንም ከዕንባዬን ጋር ቀላቅያለሁና።» መዝ 101:9።

ይህም ማለት እርሱ ውኃ ለመጠጣት ብርጭቆ ሲይዝ ዕንባዎቹ በውኃ ላይ ስለሚወርዱ ከመጠጡ ጋር ይቀላቀላሉ· ማለት ነው።

ስሜታዊነቱ ምንኛ ታላቅ ነው!! እኛ ግን ኃጢአትን እንደ ውኃ እየጠጣን እንረሳዋለን።

ዳዊት ታላቅ ዕንባዎች ስለ ነበሩት ለእግዚአብሔር «ዕንባዬን እንደ ትእዛዝህ በፊትህ አኖርሁ።» (መዝ 55:8) ብሏል። ከዚህ

በተጨማሪም እንዲህ ብሎ ነበር፡- «እንባዬ በቀንና በሌሊት ምግብ ሆነኝ፡፡» መዝ 42:3፡፡

እርሱ በጾሙ ውስጥ ሲሆንም እንዲህ ብሏል፡- «ነፍሴን በጾም አስመረርኋት፤ለስድብም ሆነብኝ፡፡» መዝ 68:10፡፡ እርሱ በእግዚአብሔር ፊት እያለቀሰ እንዲህ ብሎታል፡- «አቤቱ፡- ጸሎቴን ስማ፤ጩኸቴንም አድምጥ፤ልቅሶዬንም ችል አትበልብኝ፤እኔ በምድር ላይ እንግዳ ነኝና፡፡» መዝ 38:12፡፡ ዳዊት ያሰቀሰው «በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ይሰቅማሉ፡፡» (መዝ 125:5) ስለ ተባለ ነው፡፡

† † †

ዳዊት በሕይወት ዘመኑ ሙሉ ለኃጢአቶቹ አልቅሷል፤ ልቅሶውን ፈጽሞ አቋርጦ አያውቅም ነበር. . .

እርሱ ልቅሶውን መቼ እንዳቆመ ታውቃላችሁ? ይህ ለእርሱ የሆነለት በዘላለማዊነት አፋፍና በምት አፋፍ ላይ ሲቆም ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ እንዲህ ነበር ያለው፡- «ነፍሴ ሆይ፡- ወደ ዕረፍትሽ ተመለሺ፤እግዚአብሔር መልካም አድርጎልሻልና፤ነፍሴን ከሞት ዓይኔንም ዕንባ ከመሰናክል አድኖአልና፡፡» መዝ 114:7-8፡፡

ነፍሴ ሆይ፡- በጭንቀት ከደከምሽ፣ በእንባ ከተጎዳሽ፣ ዐይኖችሽም በኀዘንና በሰቆቃ ካረጁ በኋላ ተመለሺ፡፡

† † †

ቅዱስ አርሰኔጶስ እስከ ሞቱ ድረስ ያለቅስ ነበር. . . የመሞቻው ሰዓት ሲደርስ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ፡፡ በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ «ምነው አባታችን! አንተም? አንተም ትፈራለህ እንዴ?» ብለው ጠየቁት፡፡

እርሱም እንዲህ አላቸው፡- «የዚህ ሰዓት አስቀያሚነት ምንኩስናን ከተቀበልሁበት ጊዜ እንስቶ እንዳደበኝ ነው. . .»

ክቡዱ አንዱ ደግሞ እንዲህ ብሎ ነበር፡- «እኔ ሦስት ነገሮችን እፈራለሁ፡- የሞት ሰዓት ደርሶ ነፍሴ ከሥጋዬ ስትለይ. . . በእውነተኛው ፈራጅ ዙፋን ፊት የምቆምበት ሰዓት ሲደርስ. . . ፍርዴን የምቀበልበት ሰዓት ሲደርስ. . .»

† † †

ዕንባዎች ሊወርዱ ግድ ነው፤ነፍስን ስለሚያጠራትና ከኃጢአት ስለሚያጥቧት፡፡

ታላቁ ነቢይ ዳዊት ምን እንዳለ ልብ በሉ፡- ዐይኔን ከእንባ አድኖአልና. . . ዐይኖቹ በዕንባ በማልቀስ ደክመዋል ማለቱ ነው. . .

እግዚአብሔር አምላክም በነቢዩ ኢዩኤል ላይ አድሮ እንዲህ ብሏል፡- «. . . በፍጹም ልባችሁ፤ በጾምም፤ በልቅሶምና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ፡፡» ኢዩ 2:12፡፡

እኛ ለድካሞቻችንና ለውድቀቶቻችን አልቅሰናል? ይሁን እንጂ እያንዳንዳችን በእኩለ ሌሊት ጸሎቶቻችን ውስጥ አንዳህ አያልን እንጸልያለን፡- «ጌታዬ ሆይ፡- አንተ ባለፈው ጊዜ ሰቢያች ኃጢአተኛ ሴት የዕንባ ምንጮችን እንዳደልሃት ለእኔም አድለኝ. . .» ሉቃ 7:38፡፡

በዕንባዎች ጉዳይ ላይ ያደረግሃቸትን ተመስጦ ላራዝምባችሁ አልፈልግም፤ታገናዝበበት ዘንድ በእንባ ዙሪያ አንድ መጽሐፍ አሳትሜላችኋለሁና. . .

መልሱ

አስቲ አሁን ወደ መዝሙር ስድስት እንመለስና ዳዊት እንዲህ ያለ እንባ ላይ ሲደርስ እግዚአብሔር አምላክ ኀዘኑን ከእርሱ ላይ አንስቶለታል፡፡ የዚህ መዝሙር መጨረሻ ከእጀግመሩ ጋር ሙሉ ለመሉ የተለየ ነው፡፡ እርሱ መልሱን (የእግዚአብሔርን) ስላወቀው እንዲህ ብሏል፡-

«ዓመፃን የምታደርጉ ሁሉ ከእኔ ራቁ፤እግዚአብሔር የልቅሶዬን ቃል ሰምቶአልና፡፡ እግዚአብሔር ልመናዬን ሰማኝ፤ እግዚአብሔር ጸሎቴን ተቀበለ፡፡»

ምናልባት እነዚህ ዓመፅን የሚያደርጉ ሰዎች በውድቀቱ የፌነጠዙ፣ እግዚአብሔር ያመጣበትን ቅጣት የተመለከቱና እግዚአብሔር እርሱን ትቶታል ብለው ያሰቡ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ!! ወይም ደግሞ ዓመፅን የሚያደርጉ ሰዎች ያላቸው ኀዘንንና ተስፋ መቁረጥን የሚያስከትሉ አሳቦች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እኛን በተመለከተ ግን እኛ በጸሎቶ ቻችን ውስጥ ዓመፅን የሚያደርጉ ሰዎች የምንላቸው የሚዋጉንን የኃጢአት አሳቦች ሁሉ ነው፡፡

እኔ ወደ እርሱ «አንተም አቤቱ፡- እስከ መቼ ድረስ ነው? አቤቱ፤ተመለስ ነፍሴንም አድናት፤ስለ ቸርነትህም አድነኝ፡፡» በማለት ስጮኽ እርሱ መልሱን ልመናዬን በመስማት ስለ ሰጠኝ ከእኔ ራቁ ብያቸዋለሁ፡፡

«ዓመፃን የምታደርጉ ሁሉ ከእኔ ራቁ፤. . .» የሚለው ዓረፍተ ነገር ሁለት ነገሮች አሉት. . .

በመጀመሪያ፡- እግዚአብሔር ጸሎቴን ስለ ሰማ እነርሱን ከእኔ አርቋቸዋል ማለት ነው፡፡ በሁለተኛ ትርጉሙ ደግሞ የሚጸልየው ሰው ዓመፃን የሚያመጡትን፣ የሚዋጉትንና ነፍሱን እጅግ የሚያስጨንቁትን አሳቦች መቃወሙን ያመለክታል፡፡

ዳዊት በሚጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር ለእርሱ የሚሠራለት ሥራ ይታወቀው ነበር. . .

እርሱ በመጸለይ ላይ እያለ እግዚአብሔር ጸሎቱን ጐዝንደ ለማውና መልስ እንደ ሰጠው አውቋል . . .

የተስፋ ብርሃን ወደ ልቡ ስለ ዘለቀ እና የኀዘን ደመና ስለ ተበተነ ከእንግዲህ በኋላ ዓመፃ ወይም ክፉ ሥራ እርሱን ለመዋጋት ኃይል አይኖረውም፡፡ ይልቁንም እነርሱን ከእርሱ ዘንድ የሚያርቅበትን ሥልጣን ስለ ታደለ እንዲህ ብሏቸዋል፡- ከእኔ ራቁ! . . . ከእኔ የምትርቁት ግን በእኔ ኃይል አይደለም፤ልመናዬን ድምፅ በሰማውና ጸሎቴን በተቀበላው በእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡ ለዚህ አምላክ እንዲህ ነው የምሰው፡-

«እግዚአብሔር ይነሣ፤ጠላቶቹም ይበተኑ፤የሚጠሉትም ከፊቱ ይሸሹ፡፡ ጢስ እንደሚበንን እንዲሁ ይብነኑ፤ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ፤እንዲሁ ኀጥአን ከእግዚአብሔር ፊት ይጥፉ፡፡»

የእርሱ ንስሓ ሙሉ የሆነው በልቅሶ ብቻ አይደለም፤ዓመፃን ከሚሠሩ በመራቅና እነርሱን በማራቅ ነው፡፡ በንስሓውና እግዚአብሔር ጸሎቱን በመቀበሉ ውስጥ ውሳጣዊ ሰላም አግኝቷል፡፡

† † †

ዳዊት፡- «እግዚአብሔር የልቅሶዬን ቃል ሰምቶአልና፡፡» ነው ያለው፡፡

እንባዎቹ ድምፅ ነበራቸው፡፡ እርሱ በሌላ መዝመሩ ውስጥ «አምላክ ሆይ፡- ልመናዬን ስማ፤ጸሎቴንም አድምጥ፡፡» (መዝ 60:1) ብሏል፡፡ በእርግጥም ዕንባዎች ማናቸውም ቃላት ከሚናገሩት ቋንቋ በላይ ስለሚናገሩ ውጤታማና አሳማኝ ናቸው፡፡

እግዚአብሔር ጸሎቴን ተቀበለ፡፡ ይህ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ልብ ውስጥ ስለ ገባ እርሱ ተቀብሎታል፡፡ ዳዊት ይህ ጸሎቱን እግዚአብሔር እንደ ተቀበለው አመኗል፡፡

በመሆኑም እንባዎቹ ወደ ደስታ ፀፀቱም ወደ ሐሴት ተለውጧል፡፡

እርሱ ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ታገለ የሚፈልገውን ነገር ከእርሱ ወስዷል፡፡

ዳዊት በዚህ መዝሙር (መዝ 6) መግቢያ ላይ «አቤቱ በቍጣህ አትቅሠፈኝ፤በመዓትህም አትገሥጸኝ፡፡» ብሏል፡፡ በዚሁ መዝሙር መደምደሚያ ላይ ደግሞ «እግዚአብሔር ልመናዬን ሰማኝ፣ እግዚአብሔር ጸሎቴን ተቀበለ፡፡» አለ፡፡ በዚህ በመደምደሚያው ላይ መደቆደልና ዕረፍት ነው የተሰማው፡፡

ጠላቶቼ ሁሉ ይፈሩ. . .

ዳዊት ይህን መዝሙሩን የሚያጠቃልለው በሚከተሉት ቃላት ነው፡-

«ጠላቶቼ ሁሉ ይፈሩ እጅግም ይኀስፉ፡ወደ ኋላቸው ይመለሱ፤በፍጥነትም ይፈሩ፡፡ ሃሴልያ፡፡»

ውስጣዊም ይሁኑ ውጪያዊ ጠላቶች አንተ (እግዚአብሔር) አሳፍረሃቸዋል፡፡ ይህን ደግሞ ጸሎቴን በመቀበልና ለልመናዬ መልስ በመስጠት አድርገኸዋል፡፡ አነዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ዳዊትን መቀበሉንና በእርሱ መደሰቱን የሚያመለክቱት ፍንጮች ናቸው፡፡ ስለሆነም ይፈሩ፤ወደኋላቸውም ይመለሱ፡፡

ይህ ደግሞ ዳዊት በሌላ መዝሙሩ ላይ ሳቀረበው ጸሎት መልስ ሊሆን ይችላል፡-

«ምልክትንም ለመልካም ከእኔ ጋር አድርግ፤የጠሉኝም ይዩ ይፈሩም፤አቤቱ፡- አንተ ረድተኸኛልና፤አጽንተኸኛልምና፡፡» መዝ 85:17፡፡

ዳዊት በመዝሙር 6 ውስጥ ያሳፈረው ጠላቶቹን ብቻ አይደለም፤ጠላቶቹን ሁሉ እንጂ፡፡ ምክንያቱም እርሱ በሌላ መዝሙሩ ውስጥ እንዲህ በማለት ተናግሯልና፡- «አቤቱ፡- የሚያስጨንቁኝ ምንኛ በዙ፤በኔ ላይ የሚቆሙት ብዙ ናቸው፡፡ ብዙ ሰዎች ነፍሴን፡- አምላክሽ አያድኑሽም አልዋት፡፡» መዝ 3:1-2፡፡ እነዚህ የሚፈነጥዙትና ተንኰል የሚያስቡት በፍጥነት ይፈሩ!!. . . ተመልሰው ይሂዱና እጅግ ይጨነቁ

እኔ ግን በእግዚአብሔር ሐሴት አደርጋለሁ. . .

እግዚአብሔር መልካም የሆነ ምልክትን አሳይቶኛልና. . .

እግዚአብሔር ልመናዬን ሰምቶአል ጸሎቴንም ተቀብሎኛልና...

ዳዊት ሆይ፡- ይህን ደስታና ሐሴት ስላገኘህ ብፁዕ ነህ።

በእውነትም ይህ አንተ እንደ ተናገርኸው ነው፡-

«የእልልታና የመድኃኒት ድምፅ በጻድቃን ድንኳን ነው፤. . .» መዝ 117፡15።

ሃሌሉያ።

ዳዊት መዝሙሩን የሚደመድመው «ሃሌሉያ» በሚለው ቃል ነው።

ብዛት ያላቸው የዳዊት መዝሙራት የሚጀምሩት ወይም የሚጠናቀቁት «ሃሌሉያ» በሚለው ቃል ነው። በጣም ታዋቂ የሆነው የንስሐ መዝሙር (መዝ 50) አንኳ የሚጠናቀቀው በዚህ ቃል ነው። «በቁጣህ አትቅሠፈኝ» የሚለውና አልጋውን በእንባው ያጠበበት መዝሙሩም የሚጠናቀቀው «ሃሌሉያ» በሚለው በዚህ ቃል ነው። «አቤቱ የሚያስጨንቁኝ ምንኛ በዙ፤. . .» የሚለው መዝ 3 እና «አቤቱ፡- እስከ መቼ ፊጽመህ ትረሳኛለህ?» ያሚለው መዝ 12 የሚጠናቀቁትም በዚሁ ቃል ነው። በነግህ ጸሎት ውስጥ ያሉት የዳዊት መዝሙራት በሙሉ መደምደሚያቸው ይኸው ቃል ነው።

ዳዊት ጸሎቱን በጎዝን ከጀመረ በኋላ የሚያጠናቅቀው በደስታና ሐሴት በማድረግ ነው።

ይህ ደግሞ ልክ መጽሐፍ ቅዱስ «የነገር ፍጻሜ ከመጀመሪያው ይሻላል፤. . .» (መክ 7፡8) በማለት እንደሚናገረው ነው። በመጀመሪያ እኛ ችግሮቻችንን ለእግዚአብሔር እናቀርባለን። መጨረሻው ደግሞ ለእነዚህ ችግሮች የሚሆነውን መፍትሔ ይዞልን ይመጣል።

በመሆኑም ዳዊት «ነፍሴም እጅግ ታወከች፤» በማለት ከጀመረ በኋላ ያጠናቀቀው በደስታና ሐሴት በማድረግ ነው. . . ይህ ደግሞ ለእኛ ሁሉ ትምህርት ነው።

በጎውን ሁሉ ለእኛ ያደረገና የሚያደርግ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን፤አሜን።

ከዚህ ቀደም በተርጓሚው ተተርጉመውና ተዘጋጅተው ለአንባቢያን የቀረቡ መንፈሳዊ መጻሕፍት፡-

1/ የተራራው ስብከት
2/ የጲያሳሩስ ውጊያዎች
3/ የነፍስ እርነት
4/ ህብታምና ደሀ
5/ የተስፋ ሕይወት
6/ መንፈሳዊው ሰው
7/ መንፈሳዊ ውጊያዎች
8/ መንፈሳዊው መንገድ
9/ የባሕታውያን አባቶች
10/ መንፈሳዊ እም
11/ እግዚአብሔርና ሰው
12/ መንፈሳዊ ቃሳትና ጥቅማቸው (ክ-1)
13/ ሊና (1ኛ መጽሐፍ)
14/ ቅድስት ድንግል ማርያም
15/ ትንሣኤ
16/ የሕይወት ልምድ
17/ ቅዱስ ትንሳኤ
18/መንፈሳዊ አነልግሎቶችና መንፈሳዊ አገልጋይ
19/መንፈስ ቅዱስና በእኛ ውስጥ ያለ ሥራው
20/ መንፈሳዊ ቃሳትና ጥቅማቸው (ክፍል-2)
21/ ዳዊም ምጽአት
22/ አሜሞር መንፈሳዊውያን ታሪኮች (1-100)
23/ የክርስቲያን ቤተሰብ
24/ የእግዚአብሔር ፍቅር

ከመጽሐፉ የተወሰደ

ጌቴሴማኒ ሰው በመጀመሪያ እጅግ የከፉ ኃጢአቶቹን በመናዘዝ ይጀምርና ንስሐ የሚገባው ሰው በመጀመሪያ ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ ሌሎች ሰዎች ነው። ‹‹ጸሎት በሕይወት ማዕበል ውስጥ መጠሪያ ወደብ፣ ማዕበል ለሚያንሳፈቻቸው መልሕቅ፣ የድህው ህብት፣ የባለጸጋው ድኅንነት፣ የታማሚው መዳኛ ወይም ጤና ተስፋ ያስትሳል። እንዲህ ባለው መንገድ ተነሣሒው ትስትናን ገንዘቡ ያደርጋል። ሉቃ 18፡13) የሚሉትን ቃላት መላልሶ ይኸው እግዚአብሔርን የያዘ መንፈሳዊ አባት በዚያው አስከትሎ ሊናገርም እንዲህ ማለቱ ነው። ጸሎት መጥፎ ነገርችን ያስወግዳል፣ መልካሙን ግን ይጠብቃል።›› ‹‹ጸሎት ኃጢአት የሚሠራ ሰውን እንደሚጠብቁት በማወቅ ተነሣሒው ጊዜ ከንስሐው ጋር ምንም ቅድነት የሌላቸው ታሪኮችን በመተረክ የዚህን ምሥጢር ክብርንና በመሆኑም ተነሣሒያኑ በሙሉ የዚህን ምሥጢር አስከትሎ ሲናገርም እንዲህ ማንነት የለሰበትም። በመንፈስ ቅዱስ ፊት መቆማቸውን ልብ ማለት አለብን። ንስሐ የሚገቡ ሰዎች ተስፋ እንደቆርጡ ካህኑ አነርሱን ማውገዝ ወይም ማዋረድ የለበትም። በእንጻሩም ካህኑ ተነሳሒያኑ ኃጢአቶችና ውድቀቶች ቢኖሩባቸውም እርሱ ለእነርሱ ብልገ፣ የማይከድና አነርሱን የሚወድ መሆን አለበት። ከንስሐ በኋላ ‹‹አምላክ ሆይ፡- አነን ኃጢአተኛውን ማረኝ!...›› (ሉቃ 18፡13) የሚሉትን ቃላት መላልሶ ይናገራቸዋል። ከዚህ በኋላ ካህኑ ከተቀመጠት ተነሥቶ በቀኝ እጁ የያዘውን መስቀል በተነሣሒው ቁንጮላት ላይ ያሳርፍና የሥርየቱን ጸሎት ይጸልይለታል።

❖❖❖

እግዚአብሔር በሕዝቡ ኃጢአት እጅግ በተቆጣ ጊዜ እርሱንና በቀይ ባሕር ውስጥ ...እግዚአብሔር በፈርዖን ላይ በተቆጣ ጊዜ እርሱንና በቀይ ባሕር ውስጥ አስጥሞአቸዋል፤ዘጸ 14:28። እግዚአብሔር አምላክ በቀሬ፣ በጻታንና በአሬርን ላይ ቁጣው በነደደው ጊዜ ምድር ተከፍታ እንደቆጣቸው አድርጓል፤ዘኁ 16:32። እኛም በየዕለቱ ኃጢአት እንሠራለን፣ ምናልባትም የእኛ ኃጢአት የእነዚህን ሰዎች ኃጢአት ሊመስል ይችላል። በዚህ ጊዜም ‹‹አቤቱ በቁጣህ አትቅሠፈኝ!...›› እያልን ወደ እርሱ እንጮኽለን። ጌታ ሆይ፡- እንተ በቁጣህ ብትተፋደን ማንም ሊድን አይችልም። በዐይደ እም ውስጥ ወደ እግዚአብሔር እንጻላህ እንዳለ አያልን እንጸልያለን። ‹‹አቤቱ ጌታ ሆይ፡- በአውነቱ አንተ ብትተፋደን ምንም ዓይነት በቁጣህ አትቅሠፈኝ።›› አለው።

ተሥዓት ፋና አሳተሚነት ኃ.የ.ተ.የ.ማኅበር
ስ.ት. 158 53 52
ቁጥር 35.00